አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረምረቃ መርሀግብር

# በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ ቅኝት የሥነጽሑፍ መሰረታውያንና የፎክሎር መግቢያ የሚያጠኑ ተማሪዎች የጥናት ጊዜ ምርጫና የውጤት ተዛምዶ ንፅፅራዊ ጥናት

በ
አባተ ጉልላት

ታህሳስ 2001 ዓ.ም.

በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ ቅኝት የሥነጽሑፍ መሰረታውያንና የፎክሎር መግቢያ የሚያጠኑ ተማሪያች የጥናት ጊዜ ምርጫና የወጤት ተዛምዶ ንፅፅራዊ ጥናት

በ

አባተ ጉልላት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ -ትምህርት
## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

[illegible] ______ ፊርማ

**አማካሪ**

[illegible] ______ ፊርማ

የውስጥ ፈታኝ

ብርሃኑ ቦጋለ (ዶ/ር) ______ ፊርማ

የውጭ ፈታኝ

# ምስጋና

በቅድሚያ ከጥናቱ ውጥን ጀምሮ እስከ መጨረሻው ጊዜ ድረስ ባለማሰለስና ባለመሰላቸት ሞያዊ አስተያየታቸውና እገዛቸው ላልተለየኝ ለአማካሪዬ ለዶ/ር አረጋ ኃ/ሚካኤል ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመቀጠልም በትምህርት ቆይታዬ ሳልቸገርና ሳልጨናነቅ በማበረታታት ከጎኔ ላልተለየችኝ ውድ ባለቤቴ ለወ/ሮ ወጋየሁ ፍስሀ ምስጋና ይገባታል፡፡

እንዲሁም ይህንን የትምህርት ፕሮግራም ጀምሬ እስከምጨርስ በሀሳብም ሆነ ሌሎች ድጋፎችን በመስጠት አብረውኝ የነበሩትን የሥራ ባልደረቦቼ ለመ/ር ጥላሁን ነጋሽ ለመ/ት ደብሪቱ ኃይሌ ለመ/ር ሰለሞን ተሾመ ለመ/ር ብርሃኑ አንዱዓለም ለወጣት አለማየሁ ፍስሀ መ/ር መስፍን ኃ/ማርያምና መ/ር መስፍን ጉልላት ታላቅ አክብሮት አለኝ፡፡

በመጨረሻም ጥናቴን ለማከናወን የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ-ምረቃ ፕሮግራምን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

# አጠቃሎ

ተማሪዎች በትምህርት ዓለም ውስጥ እያሉ የሚማሩትን ትምህርት በተመደበላቸው ጊዜ ማወቅና መገንዘብ ይኖርባቸዋል:: የተማሪዎቹ ብቃት ሊለካ የሚችለው ደግሞ በተያዘለት ፕሮግራም መሠረት በሚሠጣቸው ፈተና ወይም ምዘና ነው:: በፈተናው የሚያገኙት ውጤትም ካሉበት የክፍል ደረጃ ወደ ሚቀጥለው መሸጋገራቸውን የሚወስን ነው::

ለተማሪዎች ውጤታማ መሆንና አለመሆን የሚጠቀሱ በርካታ ምክንያቶች አሉ:: ለምሳሌ የአጠናን ዘዴያቸው፣የትምህርቱ አቀራረብ፣ የተማሪዎቹ ዳራዊ ዕውቀት፣ዕድሜያቸው፣ፆታቸው ወዘተ. ናቸው:: እነዚህን ሁሉ በአንድ ጥናት ውስጥ አካቶ መመርመሩ ደግሞ አመቺነት የለውም:: በመሆኑም የዚህ ጥናት ዓላማ በተማሪዎች የአጠናን ዘዴ ላይ ብቻ ያተኮረ ነው:: የአጠናን ዘዴ ሲባል ደግሞ በሁለት የጥናት ልምድ ባለቸው ተማሪዎች ላይ (ፈተና ሲደርስ ወይም ሲቃረብ በሚያጠኑና ከፈተና በፊት ማለትም ትምህርቱ እንደተጀመረ ጥናታቸውን በሚጀምሩ ተማሪዎች) ያነጣጠረ ነው:: በሌላ አባባል«የትኛው የአጠናን ዘዴ ውጤታማ ሊያደርጋቸው ይችላል?» የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚሞከር ነው:: እግረ- መንገዱንም ተማሪዎቹ ይሆነኛል ብለው የመረጡት የአጠናን ዘዴ ከውጤታቸው ጋር ማዛመድ እንዳለባቸው ያመለክታልና እንደመማር ብቃታቸው የራሳቸውን የመማር ወይም የጥናት መንገድ እንዲከተሉ ለማድረግ ጭምር ነው::

ጥናቱ በዋናነት ይዞት ለተነሳው ጥያቄ መመለስ ያስችል ዘንድ የተመረጠው የጥናት ዘዴ «ንጽጽራዊ የምርምር ስልት» ነው:: የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ ደግሞ የጽሁፍ መጠይቅና የቃለ- መጠይቅ ጥያቄዎች ናቸው:: በመጠይቆቹ አማካይነት የተሰበሰቡት መረጃዎች ደግሞ በአግባቡ ተቆጥረውና ተሰልተው በሠንጠረዥ አማካይነት በቁጥርና በመቶኛ ተደራጅተው ተመልክተዋል::

በዚሁ መሠረት የሚከተሉት ውጠቶች ተገኝተዋል::

- አብዛኞቹ ተጠኝዎች(75%) ያህሉ) የጥናት ጊዜ ምርጫ አላቸው
- ከጠቅላላ ተጠኝዎች (60%) ያህሉ) የጥናት ጊዜ ምርጫቸው ፈተና ከመድረሱ በፊት ሆኖ ተገኝቷል::
- ሁለቱንም የአጠናን መንገድ የተከተሉት ተማሪዎች በቁጥራቸው ይበላለጡ እንጂ የመረጡት የአጠናን ዘዴ ውጤታማ አድርጎአቸዋል::
- ፈተና ሲደርስ ማጥናትና ፈተና ከመድረሱ በፊት ማጥናት ከቋንቋ ትምህርቶቹ ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ የጎላ ሆኖ ባይገኝም እንደ አጠቃላይ ግን ፈተና ከመድረሱ በፊት ያጠኑት በአመዛኙ ውጤታማ ሆነው ተገኝተዋል::

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገፅ**


**ምዕራፍ አንድ**
መግቢያ
1.1 የጥናቱ ዳራ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1
1.2 የጥናቱ ዓላማ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5
1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6
1.4 የጥናቱ ወሰን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 7

**ምዕራፍ ሁለት**
የተዛማጅ ፅሑፎች ቅኝት
2.1 ተማሪዎች ለጥናት የሚመርጡት ጊዜ መቼ መሆን ይኖርበታል? . . . . . . . 8
2.1.1 ተማሪዎች ውጤታማ ለመሆን ዘወትር ማጥናት ይኖርባቸዋል . . . . . . . . . 8
2.1.2 ፈተና ከመድረሱ በፊት ማጥናት ውጤታማ ያደርጋል . . . . . . . . . . . 9
2.1.3 ፈተና ሲደርስ ውጤታማ ያደርጋል . . . . . . . . . . . . . . . . . 12
2.2 ተማሪዎች እንዴት ማጥናት አለባቸው . . . . . . . . . . . . . . . . 16
2.2.1 የጥናት ፕሮግራም በማዘጋጀትና በአግባቡ በመጠቀም . . . . . . . . . . 16
2.2.2 ለተማሪዎች የሚበጁ የጥናት ዕቅድ አዘገጃጀት ስልቶች . . . . . . . . . 18
2.2.3 ጥናትን በቡድን ማከናወን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 20
2.3 ተማሪዎች ስኬታማ ሊሆኑ የሚችሉበት ነገሮች . . . . . . . . . . . . . 21
2.4 ተማሪዎች ፈተናቸውን እንዴት መስራት ይኖርባቸዋል? . . . . . . . . . . 22
2.4.1 ለፈተና የሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች. . . . . . . . . . . . . . . . . 22
2.4.2 በፈተናው ዋዜማ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 22
2.4.3 በፈተናው ዕለትና በፈተናው ወቅት . . . . . . . . . . . . . . . . 24

**ምዕራፍ ሶስት**
የአጠናን ዘዴ
3.1 ተጠኚዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 25
3.1.1 የዩንቨርሲቲው አመራረጥ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 25
3.1.2 የተማሪዎች ናሙና አወሳሰድ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 25
3.1.3 የትምህርቶቹ አመራረጥ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 26
3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 26
3.2.1 የፅሑፍ መጠይቅ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 26
3.2.2 ቃለ መጠይቅ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 27
3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 27

**ምዕራፍ አራት**
የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ
4.1 የውጤት ትንተና . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 29
4.2 የውጤት ማብራሪያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 44

**ምዕራፍ አምስት**
የጥናቱ ውጤት መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳቦች
5.1 የጥናቱ ውጤት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 51
5.2 መደምደሚያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 53
5.3 የመፍትሔ ሀሳቦች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 55
አባሪዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 56-60
ዋቢ መጽሐፍት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 61

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ላይ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ አስፈላጊነትና የጥናቱ መጠነ-ስፋት በቅደም ተከተል ይቀርባሉ።

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ለተማሪዎች ውጤታማ ሆኖ መገኘት ዋነኛው መንገድ ጥናት ነው። ለዚህም ተግባር ራስን በፕሮግራም በመምራት ማጥናት አማራጭ የሌለው የዕለት ተዕለት ክንውን መሆኑን ለመረዳት ይቻላል።

በርካታ ፀሀፍት ተማሪዎችና ጥናት እጅና ጓንት መሆናቸውን ይስማሙበታል። Keeves (1992 418-435) እንደገለፀው፣ ጥናት ለተማሪዎች፣ ከክፍል ክፍል ለመዛወር እንደመሸጋገሪያ ድልድይ የሚቆጠርና በአንድ ነገር ላይ ውጤታማ የመሆን ማረጋገጫ ከመሆኑም በተጨማሪ ለወደፊቱ ህይወታቸው ብሩህነት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ይህም በመሆኑ ተማሪዎች በፈተናቸው ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ጥናትን ማዘውተር አለባቸው።

ተማሪዎች ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ በሚሰጣቸው ትምህርት ዙሪያ ያላሰለሰ ጥናት ካላካሄዱ ውጤታቸው ያማረ ሊሆን እንደማይችል ከወዲሁ መገመት ይቻላል። ጥናት ሲባል ደግሞ በዘፈቀደ የሚከወን ተግባር ሳይሆን ተጠቃሚ ሊያደርግ በሚችል መንገድ መሆን ይኖርበታል። ይህም የሚለካበት ያለምንም ስጋት ጥሩ ውጤት አስመዝግቦ ወደ ሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ መሸጋገር ይሆናል።

ጥናትና ተማሪነትን አጣምረው የሚመለከቱት ተመራማሪዎች ለሁለቱ መዛመድ ዋናው ምክንያት ፈተና መሆኑን ይስማሙበታል። ይህም በመሆኑ ተማሪዎች በተሰለፉበት ወይም በሌላ የሙያ መስክ ላይ በበቂ ሁኔታ መሳተፍ አለመሳተፋቸውን መመዘን የሚቻለው በተወሰኑ የትምህርት ጊዜያት ማብቂያ ላይ ወይም በየሴሚስተሩ አጋማሽ በሚሰጥ ፈተና ነው። ፈተና የተማሪዎች የጥናት እንቅስቃሴ በትክክል መከወን አለመከወኑ የሚረጋገጥበት መሳሪያ ነው።

ከላይ እንደምንረዳው ተማሪዎች በሚሰጣቸው ትምህርት ላይ ያላቸው ብቃት የሚመዘነው ቢያንስ በሴሚስተር አጋማሽ፣ ቢበዛ በሴሚስተር መጨረሻ ላይ በመሆኑ በዚህ ቆይታቸው የተማሩትን በመከለስና በማጥናት እራሳቸውን ለፈተና ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ለዚህም ዋነኛው መንገድ ተስማሚ የሆነ የአጠናን ዘይን መከተል ነው።

የቋንቋ ክህሎትን ማዳበር የሚቻለው በጥናት ብቻ ነው ብሎ መደምደም የማይቻል ነው፡፡ በተለይም በዝቅተኛ ደረጃ ማለትም በአንደኛ ደረጃና በሁለተኛ ደረጃ ላይ እንደትምህርቱ ዓይነትና ጥልቀት ሥርዓትን ጠብቆ በመናገር፣ ፋታ ሰጥቶ በማዳመጥ፣ ጊዜ ወስዶ በማንበብና በተደጋጋሚ ሳይሰለቹ በመፃፍ ቀስ በቀስ በቋንቋ በብቃት ለመጠቀምና ለመገልገል ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ በከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች ማለትም በኮሌጅና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚጠናው ቋንቋ የተለያየ ዘርፍ ተሰጥቶት በጥልቀተ መጠናት የሚጀምርበት ደረጃ በመሆኑ ጊዜና ቦታ ተመርጦለት በወጉ ሊጠና የሚችልበት መንገድ ሊኖር ይገባል፡፡

በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚሰጡት የቋንቋ ዘርፎች (Categories of Language Courses) ሁሉም በጥናት ብቻ ሊዳብሩ ይችላሉ ባይባልም ከነዚህ ኮርሶች ውስጥ ተመርጠው ጥናትን የሚሹ በመሆናቸው ለጥናቱ ትኩረት የተሰጣቸው ርዕሶች ሆነዋል፡፡

ሁሉም የትምህርት ዓይነት መሠረቱ ሳይንስ ነው፡፡ የራሱ የሆነ የአጠናን ዘዴንም ይጠይቃል፡፡ ሳይንሳዊ የሆኑ የአጠናን ዘዴዎችን መጠቀምንም ጭምር፡፡ በትምህርት ዓለም ተማሪዎች ትክክለኛውን የአጠናን ስልት ተከትለው ውጤታማ የሚሆኑበት አሠራር የተለመደ አይደለም፡፡ ይህም ማለት አብዛኛው የቋንቋ መምህራን የቋንቋ ትምህርቱን ማስተማር እንጂ ተተኳሪውን ቋንቋ የሚማሩበትን አቀጣጫ ወይም የአጠናን ዘዴ የሚያመለክቱበት አጋጣሚ እምብዛም ነው፡፡ መማርን መማር ይቻላልና ነው፡፡

Tyler et, al.(1987: 280-302) እንደሚሉት፣ የተማሪዎች ውጤታማ መሆን ወይም ማለፍና መውደቅ የሚወሰንበትና በመካከለቸውም ያለው ልዩነት የሚረጋገጥበት አንዱ ሚዛን ፈተና በመሆኑ ተማሪዎች በትምህርት ዓለም እስካሉ ድረስ ራሳቸውን ለፈተና ማዘጋጀት የማይቀርላቸው ነው፡፡ ነገር ግን የተለያዩ ተማሪዎች ራሳቸውን ለፈተና የሚያዘጋጁት በተለያየ መንገድ ወይም የአጠናን ዘዴ ነው፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች ፈተና ከመድረሱ በፊት ማጥናትን ሲመርጡ፣ የቀሩት ደግሞ ፈተና ከደረሰ በኋላ ወይም ሲቃረብ ማጥናትን ይመርጣሉ፡፡ በእነዚህ ሁለት ዓይነት የአጠናን ልምዶችን በሚከተሉ ተማሪዎች መካከል ደግሞ የውጤት ልዩነት መኖሩን ያመለክታሉ፡፡

ፀሀፍቱ እንደሚያስገነዝቡት፣ ተማሪዎች በፈተናቸው በሚያስመዘግቡት ውጤት ከአቻዎቻቸው ጋር ያላቸው ልዩነት የሚወሰንበትና በሚያገኙት ውጤት ሳቢያ ራሳቸውን የሚገመግሙበት አጋጣሚ እንደሆነ በአንፃሩም በየግላቸው የአጠናን ዘዴ

ከሚያገኙት ውጤት ጋር በማዛመድ ወደ ትክክለኛ የአጠናን መንገድ ራሳቸውን የሚያዘጋጁበት ዕድል ይፈጥርላቸዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች ከጥናታቸው ተጠቃሚ ለመሆን ይችሉ ዘንድ አመቺ ቦታንና ጊዜን በመጠቀም ለጥናታቸው ፕሮግራም በማውጣት ባግባቡ መጠቀም ይኖርባቸዋል። ይህም ማለት የጥናት ጊዜያቸውን በመከፋፈል ለየትምህርቱ የተሰጠውን ጊዜ ሳያባክኑና ሳያዛንፉ መጠቀም ተገቢ መሆኑን ያስገነዝበናል። ተማሪዎች ውጤታማ ለመሆን ሳይንሳዊ የጥናት ዘዴዎችን መጠቀም ተገቢ ነው። ለምሳሌ ስለሚጠናው የትምህርት ዓይነት አጠቃለይ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖር ማድረግ፣ የሚጠኑትን ይዘቶች በማገላበጥ መቃኘት፣ የተነበበውን በራስ አባባል ለማስታወስ መሞከር፣ መሠረታዊ ነጥቦችን በጥልቀት ማየትና ከተነበበው ውስጥ ማስታወሻ መያዝ ወዘተ. ስልቶችን በመገልገል የጥናት ልምድን ማዳበር ይጠቅማል።

በጥናት ወቅት ተማሪዎች ትኩረታቸውን መሰብሰብ ይገባቸዋል። ይህም ማለት አእምሮአቸው ወይም መንፈሳቸው ሳይረጋጋ በሚያነቡበት ወቅት ትኩረታቸውን ለማሰባሰብ አደናቃፊ ነገሮችን ማስወድ አለባቸው። ለምሳሌ እንደ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥርን እና ሌሎች ድምፆች ሁሉ መራቅ ይኖርባቸዋል። እንዲሁም ስሜታዊ ችግሮችን ለምሳሌ በሆነ ነገር መበሳጨት፣ መጨነቅና የመሳሰሉት ሲሆኑ ከእነዚህም ስሜታዊ የጥናት እንቅፋቶች ነፃ ለመሆን ገጠመኞቹን ለጓደኛ በማማከር፣ የችግሮቹን ምንጭ በመረዳት ለማቃለልና ነፃ ለመሆን መሞከር ነው።

የተማሪዎቹ ውጤታማ መሆን አለመሆንን በተመለከተ ደግሞ ተግባራዊነቱ የሚረጋገጠው በየክፍለ ትምህርቱ አጋማሽ ወይም ማጠቃለያ ፈተና ላይ በሚሰጠው ፈተና ነው። በመጨረሻ ያገኙት ውጤትም ተማሪዎቹ ስለፈተና አሠራር ያላቸውን ግንዛቤና በውጤታቸውም ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ ያመለክታል። ይሁን እንጂ የፈተና አሠራራቸው ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መመርመሩ ራሱን የቻለ አንድ የጥናት አቅጣጫ መሆኑን በማመን ለዚህ ጥናት ዓላማ የሚጠቅሙት ብቻ ተለይተው በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል።

እንደሚታወቀው ለተማሪዎች ውጤታማ መሆን አለመሆን በምክንያትነት የሚጠቀሱ በርካተ ምክንያቶች አሉ። እነዚህም የተማሪዎች ዳራ፣ የትምህርቱ አቀራረብ፣ መምህራን፣ ዕድሜና የፈተናው ዓይነት፣ ወዘተ. ናቸው። እነዚህን ሁሉ ተላውጠዎች በጥናቱ ውስጥ ማካተት ደግሞ ለምርምር አመቺ አይሆንም። ስለሆነም ጥናቱ ዓላማ አድርጎ የተነሳው የተማሪዎችን የአጠናን ዘዴ እና የሚማሩአቸውን ትምህርቶች የውጤታቸውን ተዛምዶ ነው። በጥናት ጊዜ ምርጫ ዙሪያ ሲተኮር ደግሞ ተማሪዎች ጥናታቸውን እንዴትና መቼ ማጥናት እንዳለባቸው መመርመር የግድ

አስፈላጊ ይሆናል። በዚህም መሠረት የጥናት ጊዜውን በሁለት አቅጣጫ ከፍሎ በማየት ፈተና ሲደርስ ወይም ሲቃረብና ፈተና ከመድረሱ በፊት የሚለው እሳቤ የጥናቱ አላማ (ትኩረት) ተደርጓል።

ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረው ሁሉም የትምህርት ዓይነቶች የየራሳቸው የአጠናን ዘዴ እንደሚፈልጉ ቢታመንም ለቋንቋ ትምህርት ተብሎ ለብቻው ሳይንሳዊ የአጠናን ዘዴን የሚያመለክት በፀሀፍት ምርምር የተደረሰበት ሥራ የለም። በዚህም ምክንያት እንደአጠቃላይ በጥናት ዘዴዎችና በጊዜ ምርጫ ላይ ያተኩሩ የተለያዩ የፀሀፍት ንድፈ ሀሳቦች በመኖራቸው ለዚህም ሥራ ወይም ጥናት አመቺ ይሆን ዘንድ ጊዜና ቦታ ተሰጥቶአቸው መጠናት የሚገባቸው ትምህርቶች ተመርጠዋል። እነዚህም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በአማርኛ ቋንቋ ሥር ራሳቸውን ችለው የቋንቋው የትምህርት ዘርፍ ሆነው በአሁኑ ሰዓት በመሰጠት ላይ ያሉትን ሶስት የትምህርት ዓይነቶችን (Course Types) ማለትምህ "የአማርኛ ቋንቋ ቅኝት"፣ "የስነጽሁፍ መሠረታዊያን"፣ እና "የፎክሎር መግቢያ" ጥናቱ እንዲያተኩርባቸው ተደርጓል። እነዚህ ተመርጠው ሊወሰዱ የቻሉት ከላይ እንደተገለፀው ጥናትን ስለሚሹና በአጠናን ዘዴ አጠቃቀም ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር በባህሪ ስለሚመሳሰሉ ነው።

በአንዳንድ ጥናቶች እነደተረጋገጠው፣ ተማሪዎች የተለያየ የአጠናን መንገድ የሚከተሉ መሆናቸውና የዚህም የጥናት ጊዜና ዘዴ ልዩነት በውጤታቸውም ላይ ተፅዕኖ ያደርጋል።

Finkel እና Crawtz (1968: 218-223) እንዳረጋገጡት፣ ፈተና ሲደርስ የሚያጠኑ ተማሪዎች የሚያስመዘግቡት ውጤት ፈተና ከድረሱ በፊት ከሚያጠኑ ተማሪዎች ውጤት ጋር ሲነፃር የጎላ ልዩነት እንዳለው ነው። ይህም የሚሆንበት ምክንያት ፈተና ከመድረሱ በፊት የሚያጠኑ ተማሪዎች በፈተና ወቅት የተረጋጉና አብዛኞቹ በራስ የመተማመን ስሜት ያላቸው በመሆናቸው ነው።

እንደምሁራኑ አስተያየት ተማሪዎች በፈተና ወቅት የሚታይባቸውን የመጨነቅና የመርበትበት ስሜት ጎዘበ መሆኑን ነው። ከልምድም እንደምንረዳው ተማሪዎች ፈተና እየተቃረበ በመጣ ቁጥር ከሚያጠኑበት ጊዜ ይልቅ በመጨነቅ ብቻ የሚያባክኑት ጊዜ ይበልጣል። ይህም የተማሪዎችን አስቀድሞ ያለመዘጋጀትንና ግዴለሽነትን ያመለክታል። ጭንቀትና ድንጋጤ ደግሞ ሊመልሱ የሚችሉትን ጥያቄ እንኳን በአብዛኛው እንዳያስታውሱት ያደርጋቸዋል።

ከላይ የተሰነዘረውን ብያኔ በተቃራኒው የሚመለከቱት ፀሀፍትም አሉ። ለምሳሌ Morgan (1969 515-534)፣ ፈተና ሲደርስ ማጥናት ውጤታማ ማድረጉን ጠቅሷል።

ይህም የሚሆነው የማስታወስ ችሎታ ይበልጥ የሚፈጥነው ለፈተና ጥቂት ቀናት ሲቀረው በሚደረግ ጥናት መሆኑን ያስገነዝባል።

የተማሪዎችን ውጤታማነት ከላይ ከተሰነዘሩት የጥናት ጊዜ ምርጫዎች አንፃር የማይመለከቱትም ፀሀፍት አሉ። የእነዚህም አስተያየት ከፈተና በፊት ማጥናትና ፈና ሲደርስ ማጥናት ለውጤታማነት እንደሚያበቃ ነው። ምክንያቱም የተማሪዎች የተለያየ የማስታወስና ነገሮችን የመንዘብ ችሎታቸው ስለሚለያይ የጥናት ጊዜ ምርጫ ከውጤታቸው ጋር ተዛምዶ የለውም ባይ ናቸው።

በአጠቃለይ ከፈተና በፊት ማጥናትና ፈተና ሲደርስ ማጥናት ከተማሪዎች ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ ወጥነት እንደሌለው ከላይ ከተሰነዘሩት ሀሳቦች መረዳት ይቻላል። ይህም የችግሩን እስካሁን እልባት ያለማግኘት የሚያመለክት በመሆኑ ለጥናቱ እነደመነሻ ሆኗል። በዚህም ምክንያት የተማሪዎች የጥናት ጊዜ ምርጫና የውጤታቸውን ተዛምዶ መመርመር የጥናቱ ትኩረት ሊሆን ችሏል።

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

ተማሪዎች በትምህርት ዓልም እስካሉ ድረስ የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶችን ማጥናት ይጠበቅባቸዋል። ከጥናታቸው ተጠቃሚ ለመሆን ደግሞ ትክክለኛውንና ሳይንሳዊ የአጠናን ዘዴ መከተል ይጠበቅባቸዋል። ይህ ካልሆነ ግን በውጤታቸው ላይ ተጽዕኖ ማሳረፉ የማይቀር ነው። ተማሪዎች ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውንና ገንዘባቸውን ለትምህርታቸው በማዋልና በመጨረሻም እንደዝንባሌያቸው ውጤታማ ሆነው ለቁምነገር መብቃት ዋነኛ ዓላማቸው ነው። በመሆኑም ይህንን ምኞታቸውን እውነት ለማድረግ የመማርን ጥበብ ማወቅ ተገቢ ነው።

የተማሪዎች ዕውቀትን የመቀበል ብቃት ወይም የመማር ችሎታ የተለያየ መሆኑን ቢታመንም ይህን የተለያየ የመማር ብቃታቸውን አስቀድሞ በመገንዘብ ለራሳቸው ተስማሚ የሆነውን የአጠናን ስልት መከተል ደግሞ አማራጭ የሌለው መንገድ ነው። ምንም እንኳን የቋንቋ ክህሎት በጥናት ብቻ እንደማይዳብር ቀደም ሲል የተጠቀሰ ቢሆንም በዩኒቨርሲቲና በኮሌጅ ደረጃ እንደማንኛውም የትምህርት ጊዜና ቦታ ተሰጥቷቸው ሊጠኑ የሚችሉ የትምህርት ዓይነቶች እንዳሉ በማመን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚሰጡት ትምህርቶች ስፋትና ጥልቀት ስላላቸው በትምህርቶቹ ዙሪያ ተማሪዎች በቂና ተመጣጣኝ ዕውቀት ሊኖራቸው ስለሚገባ ጥናትና ምርምር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

በመሆኑም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ጥናት የሚያስፈልጋቸው ሶስት የትምህርት ዓይነቶች ተመርጠዋል። እነዚህም ትምህርቶች "የአማርኛ ቋንቋ ቅኝት"፡ "የስነጽሁፍ

መሠረተውያን"ና "የፎክሎር መግቢያ" ናቸው። የዚህ ጥናት ተቀዳሚ ዓላማም በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ አማርኛን በዋናነት የሚያጠኑ የዲግሪ ተማሪዎችን በመውሰድ በተጠቀሱት የትምህርት ዓይነቶች ላይ የጥናት ጊዜ ምርጫቸውንና የውጤት ተዛምዶአቸውን መመርመር ነው። ተዛምዶውንም ለማረጋገጥ ተገቢና ግልጽ የሆኑ ጥያቄዎች በጽሁፍና በቃለ-መጠይቅ አማካይነት ተዘጋጅተው ተጠኝዎች ምላሽ እንዲሰጡ ተደርጓል።

በዚህም መሠረት ጥናቱ የሚከተሉት ዋነኛና ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፤የጥናቱ ዋንኛ ዓላማ

- ፈተና ሲደርስ ወይም ሲቃረብ የሚያጠኑትንና ከፈተናበፊት ጥናታቸውን የሚጀምሩትን ለይቶ በማወቅ የአጠናን ዘዴያቸውና ልምዳቸው ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መመርመር ሲሆን፤ ዝርዝር ዓላማዎቹ ደግሞ:-
- ተማሪዎቹ የየራሳቸው የጥናት ጊዜ ምርጫ እዳላቸውና እንደሌላቸው ለመረዳት፤
- ተማሪዎቹ ይሆነኛል ብለው የመረጡት የአጠናን ዘዴ በውጤታቸው ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ተረድተው ውጤታማ የሚያደርጋቸው የጥናት ዘዴ እንዲከተሉ ለማድረግ፤
- የአጠናን ዘዴ ለተማሪዎች ውጤት ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ መሆን ምክንያት ሆኖ ከተገኘ ተገቢውን መንገድ እንዲከተሉ ለማድረግ፤
- ተማሪዎች ከጥናታቸው ተጠቃሚ የሚሆኑበት መሠረታዊ የጥናት ዘዴዎች እንዲከተሉ ለማድረግና፤
- የተጠቀሱት የቋንቋ ትምህርቶች የተለያዩ ፀሐፍት ለአጠቃላይ ትምህርቶች የሰጡት የጥናት ጊዜ ምርጫ ብያኔ ተግባራዊ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ነው።

## 1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት

የተለያዩ ፀሐፍት በጥናት ዘዴና ውጤታማነት ላይ የሰነዘሩት አስተያየት በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ለሚሰጡት የአማርኛ ቋንቋ ዘርፍ ለሆኑት ለአማርኛ ቋንቋ ቅኝት፤ ለስነጽሁፍ መሠረታውያንና ለፎክሎር መግቢያ ጠቃሚና አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው።

በሀገራችን የመማር-ማስተማሩ ተግባር የሚከውነው በሥርዐተ ትምህርቱ ላይ ተመስርቶ ትምህርቱን ከማቅረብና ተማሪዎች እንዲቀበሉት ከማድረግ ባሻገር የተማሪዎችን የመማር አቅም በመለየት እንደተማሪዎቹ ዳራና የማስታወስና የመረዳት

ችሎታ ባለመሆኑ ጥናቱ የመማር ብልሀትንም በተጨማሪ እንዲተኮርበት ያመላክታል ተብሎ ይገመታል። በመሆኑም ተማሪዎች ከአጠናን ልምድ ማጣት የተነሳ በፈተና ወቅት ሲጨነቁ፣ ሲርበተበቱና ሲዋከቡ ይስተዋላል። ጥናቱ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚሰጡትን የአማርኛ ቋንቋ ዘርፎች (ኮርሶች) ተገቢውን የአጠናን ዘዴ ተከትለው እንዲያጠኑና ይህንንም ከውጤታቸው ጋር በማነፃፀር እንደተማሪዎቹ የመማር አቅምና የመረዳት ችሎታ መምህራንም የሚጠበቅባቸውን ምክር ድጋፍ እንዲሰጡ እገዛ ያደርጋል።

ተማሪዎች በፈተና ወቅት ሊገጥሟቸው የሚችሉትን ችግሮች አስቀድሞ በመጠቆም በፈተና ወቅት የመረጋጋትና በራስ የመተማመን ዕድል እንዲኖራቸው ያግዛል። ተማሪዎችም በሚያኙት ዝቅተኛ ውጤት የተለያዩ ሰበቦችን ለመፍጠር የመማርን ብልሀት ያሸታል ተብሎ ይታመናል።

ተማሪዎች ከፈተና በፊትም ሆነ ፈተና ሲደርስ አጥንተው በውጤታቸው ላይ ለውጥ የማያመጡ ሆነው ከተገኙ ሌሎች የመማር ብልሀቶችን እንዲፈትሹ መንገድ ይሰጣል። በመጨሻም የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ለቀጣይ ጥናቶች የተወሰነ እገዛ ይሰጣል ተብሎ ይታመናል።

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

ለተማሪዎች ውጤት መለያየት ከፈተና በፊት ወይም ፈተና ሲደርስ ማጥናት ብቻውን እንደምክንያት መወሰድ እንደሌለበት ይታመናል። ሌሎች ጉዳዮችም ለምሳሌ እንደ ዳራዊ ዕውቀት፣ የቤተሰብ ሁኔታ፣ የፈተናው ባህሪ፣ ዕድሜ፣ ፆታና የመሳሰሉት ተላውጠዎች ተጠቃሽ ናቸው። ይሁን እንጂ እነዚህን ሁሉ ተለውጦዎች በዚህ ጥናት ውስጥ ለመዳሰስ የጊዜና የገንዘብ አቅምን ይጠይቃል። በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ጥናቱ አላከተተም።

የዚህ ጥናት የትኩረት አቅጣጫም ለተማሪዎች ውጤት መለያየት በምክንያትነት ሊጠቀስ የሚገባውን የአጠናን ዘዴና የውጤታቸውን ተዛምዶ በመመርመር ቀዳም ሲል የተጠቀሱት የአማርኛ ቋንቋ የትምህርት ዘርፎችን ከፈተና በፊት አስቀድሞ በማጥናት ወይም ፈተና ሲደርስ በማጥናት ውጤታማ መሆን አለመሆናቸውን ላይ ብቻ ያለመ ነው።

# ምዕራፍ ሁለት
# የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

## 2.1 ተማሪዎች ለጥናት የሚመርጡት ጊዜ መቼ መሆን ይኖርበታል?

በተማሪዎች የጥናት ጊዜ ዙሪያ በርካታ ፀሀፍት አስተያየት ቢሰነዝሩም ከውጤታቸው ጋር በተዛመደ መልኩ የሰጡት ብያኔ ይለያያል። ይህም በመሆኑ ለአሰራር ያመች ዘንድ እንደምሁራኑ አስተየየትና የሀሳብ ተዛምዶ በምድብ ከፋፍሎ መመልከቱ ተገቢ ነው። ስለሆነም በተማሪዎች የጥናት ጊዜ ምርጫና በውጤት ተዛምዶ ላይ የተሰጡት አስተያየቶች በሚከተለው መንገድ ቀርበዋል።

### 2.1.1 ተማሪዎች ውጤታማ ለመሆን ዘወትር ማጥናት ይኖርባቸዋል

Finkel እና Crawtz (1968: 372-396) እንደሚያስገነዝቡት ተማሪዎች በትምህርት ዓለም እስካሉ ድረስ ጥናት በየዕለቱ እነደሚከናወነው ማንኛውም ተግባር ሁሉ ህይወታቸውን በሙሉ መከወን እንደሚገባውና የሚያጠኑበት ጊዜ የተገደበ መሆን የለበትም።

እንደምሁራኑ አገላለጽ፣ ጥናት ማለት በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ብቻ ተከውኖ አበቃለት የሚባል ሥራ ሳይሆን ከዚህም ባለፈ መከናወን ይኖርበታል። ይህም ማለት ከትምህርት ቤት ውጭም ሊታሰብ ይገባል ማለታቸው ነው። ምክንያቱም የሚመጣውን ፈተና በሚገባ ሠርቶ ለማለፍ፣ ተወዳድሮ ሥራ ለመያዝ ለሌሎችም ክንውኖች ወሳኝነት ያለው መሆኑን የሚያመላክት ነው።

Norman (1997: 216) ተማሪዎች ለትምህርታቸውም ሆነ ለጥናታቸው ሰፊ ጊዜ መስጠት እንዳለባቸው በመጠቆም ለትምህርታቸውም ሆነ ለጥናታቸው አብዛኛውን ጊዜያቸውን መስዋእት ካላደጉ ተማሪ ሊባሉ እንደማይችሉ በማስገንዘብ አጠናናቸውም ከትምህርት ዓይነቶች ብዛትና ስፋት እንዲሁም ከይዘታቸው ጥልቀት ብዛት አኳያ ብዙ እንዲሰሩ ይጠበቃል በማለት ታብራራለች።

ከፀሀፍቱ የተሰነዘሩት ሀሳቦች የሚያስገነዝቡን ተማሪዎች በትምህርት ተግባርላይ ከተሰማሩበት ዕለት ጀምሮ ሳያሰልሱና ሳይዘናጉ ማጥናት የሚጠበቅባቸውና አብዛኛውን ጊዜያቸውን ለጥናታቸው ማዋል እንዳለባቸው ነው። ይህም ለፈተና ዝግጁ እንዲሆኑ ከማድረጉም በላይ ውጤታቸውም የሰመረ እንዲሆን ያግዛቸዋል። ከዚህም

በተጨማሪ የአጠናን ስልቶችንም በመጠቆም የሚማሩአቸውን የትምህርት ዓይነቶች ብዛት ከግምት ውስጥ ማስገባት ይገባል:: ይህም ማለት የትምህርቱ ይዘቶች የሚኖራቸውን ስፋትና ጥልቀት አስቀድሞ በመረዳት ቅድሚያ መስጠት የሚገባውና የማይገባውን ለይቶ በማወቅ በቅደም ተከተል መከወን ያለበት ተግባር መሆኑን ያመለክታል::

እንደ Ball (1969:283) አባባል በግሞ ተማሪዎች በትምህርታቸው ወጤታማ እንዲሆኑ ከፈለጉ አመቱን በሙሉ መደበኛ በሆነ መልኩ ማጥናት የሚጠበቅባቸው መሆኑን ነው:: በተመሳሳይም Morgan (1968: 515-534) ከላይ የተሰነዘረውን ሀሳብ በመጋራት ተማሪዎች በዕቅድ የተደገፈ የአጠናን ልምድ መከተል እንዳለባቸውና ይህም ዕቅድ ለቀናት፣ ለሳምንታት ፣ለወራትና ለሴሚስተር ብሎም እስከ ዓመቱ ማብቂያ ድረስ የሚቀጥል መሆን እንዳለበት ያስገነዝባል::

ከላይ የተሰነዘረው ሀሳብ ቀደም ሲል ከተሰጠው አስተያየት ጋር ማለትም «ተማሪዋች ዘወትር ማጥናት አለባቸው» ከሚለው ሀሳብ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ቢገኝም ጥናት በዘፈቀደ የሚከወን ተግባር ያለመሆኑን በተጨማሪ ለመጠቆም መሞከራቸው ነው:: ይህም ጥናት በኘሮግራም መተግበር እንዳለበትና የኘሮግራሙ አዘገጃጀትም በጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት መሆን እንዳለበት ይመክራሉ:: በእቅድ ያልተደገፈ ሥራ ከግብ እንደማይደርስ ሁሉ ተማሪዎቹም በትምህርት ህይወታቸው ጥናትን ለነገ ሳይሉ የዕለት ተዕለት ተግባራቸው ያደርጉ ዘንድ አስተያየት ሰጥተዋል:: የሚያዘጋጁት የጥናት ኘሮግራምም ከዕለት እስከ ዓመት ያለውን የትምህርት ቀናት በመሸንሸን መሆኑን ነው::

## 2.1.2 ፈተና ከመድረሱ በፊት ማጥናት ውጤታማ ያደርጋል

ፈተና ከመድረሱ በፊት አስቀድመው የሚያጠኑ ተማሪዎች ውጤታቸው የሰመረ መሆኑን የሚያጠናክሩና ጠቀሜታውን አጉልተው የሚያሳዩ ምሁራን አሉ:: ከእነዚህም መካከል፡- Webb (1987: 220-227) ፣በእንግሊዝና በጃማይካ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ ያካሄደው ጥናት እንደሚያመለክተው በእንግሊዝ አገር ከሚገኙት ተማሪዎች መካከል በአብዛኛው ወጤታማ ሆነው የተገኙት ፈተና ከመድረሱ በፊት ያጠኑት ተማሪዎች ናቸው:: ለዚህም አስተዋጽኦ ያደረገላቸው ተማሪዎቹ ጥሩ የአጠናን ዘዴዎችን በመከተል ራሳቸውን ከወዲሁ እንዲያዘጋጁ በመሞከራቸው ነው:: ፈተና ከመድረሱ በፊት ማጥናት በራስ የመተማመንን፣የመረጋጋትንና ሌሎች ስሜቶችንም ጭምር ማለትም ከፈተና ጋር የሚዛመዱ ስሜቶችን ስለሚፈጥርላቸው የበለጠ ውጤታማ

ናቸው በማለት ቄብ ያስገነዝባል። እንዲሁም Smith (1990:105) እና Chan (1994)፣ ፈተና ከመድረሱ በፊት ማጥናት ወይም የሚያጠኑ ተማሪዎች አብዛኞቹ በራስ የመተማመን ስሜት ያላቸው ናቸው በማለት ከላይ የተሰጠውን አስተያየት ያጠናክራሉ።

የፀሀፍቱ አስተያየት የሚያስገነዝበን ፍሬ ሀሳብ በአብዛኛው ውጤታማ ሆነው የሚገኙት ተማሪዎች ፈተና ከመድረሱ በት ያጠኑት እንደሆኑ ነው። ይህ ደግሞ በፈተና ወቅት ዘወትር በተማሪዎች ላይ የሚከሰተውን የፍርሀት፣ የጭንቀትና የመርበትበት ስሜት በማጥት ፈተናቸውን በተረጋጋና በራሳቸው በመተማመን እንዲሰሩ ያግዛቸዋል። አስቀድሞ ያላጠናም ተማሪም ፈተናው እየተቃረበ በመጣ ቁጥር ጭንቀቱ እየጨመረ በመሄዱ ምክንያት ቀሪ ጊዜውን ለንባብ ሊጠቀምበት አያስችለውም። ሌላው ልንገነዘበው የሚገባን ጉዳይ በእንግሊዝ ሀገር የሚገኙት ተማሪዎች ውጤታማ ለመሆን የበቁት ከፈተና በፊት እንዲያጠኑ መመከራቸው የጠቀማቸው ሆኖ መገኘቱን ነው። ይህ ደግሞ የመምህራን ድርሻ መሆኑ ነው፡ ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው መምህራን ከማስተማር ሥራው ባሻገር የመማርን ብልሀት በተጓዳኝ ማመላከት እንዳለባቸው ነው።

Svaz (1982: 215-312) እንደሚያብራራውም፣ ፈተና ከመድረሱ በፊት የሚያጠኑ ተማሪዎች ውጤታማ መሆናቸውን ነው። አስቀድመው የሚያጠኑ ተማሪዎች ያጠኑትን ለመከለስና ከትምህረቱ ጋር የማዛመዱ የማጣቀሻ መጽሀፍትን ለመመልከት በቂ ጊዜ ይኖራቸዋል። ፈተና በደረሰ ሰዓትም የሚሰሩት ሥራ ውጥረት የበዛበት ስላልሆነ በራስ የመተማመን ስሜታቸው ከፍተኛ ይሆናል። ከዚህም በላይ ፈተና ከመድረሱ በፊት የሚያጠኑ ተማሪዎች የትኛውን የጥናት ዓይነት ከየትኛው የትምህርት ዓይነት ማስቀደም እንዳለባቸው ጠንቅቀው ያውቃሉ። እንደነዚህ ያሉት ተማሪዎች ሊጠየቁ የሚችሉትን ጥያቄ ጭምር አስቀድመው የመገመት ችሎት ያላቸውና የት የት ቦታም ላይ በትኩረትና በጥልቀት ማጥናት እንዳለባቸው የተገነዘቡ ናቸው።

Keeves (1992: 418-435) ከላይ የተሰነዘረውን አስተያየትበመጋራት አንድ ተማሪ በሚያጠናበት ወቅት ሊጠየቅ የሚገባውን ጥያቄ አስቀድሞ መገመት ይኖርበታል ይላል።

የምሁራኑ አገላለጽ ፈተና ከመድረሱ በፊት የሚያጠኑ ተማሪዎች ለፈተና የሚያግዟቸውን ሌሎች ተግባራትን ለምሳሌ ክለሳን የማጣቀሻ መጽሀፍት ማንበብን፣ አስቀድሞ የተጠየቁ የፈተና ወረቀቶችን ለመመልከት፣ ወዘተ. ሁሉ ለመቃኘት በቂ ጊዜ ሊያተርፉ የሚችሉ በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ያስገነዝቡናል። እነዚህን

አጋዥ ሐሳቦች አስቀድመው ከአጠኗቸው ትምህርቶች ጋር አጣምሮ መጠቀም መቻል ደግሞ ለጥሩ ውጤት የሚያበቃ ከመሆኑም በላይ በተተኳሪው ትምህርት ዙሪያ የጠለቀ ዕውቀት እንዲኖራቸው ያግዛቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ደግሞ ፈተና ሲቃረብ የሚያጠኑ ተማሪዎች ለፈተና በቀራቸው አጭር ጊዜ የተነሳ ጥናታቸው ከውጥረት ጋር የተያያዘ በመሆኑ የቱን ይገፍ የቱን ልልቀቀው በሚል ሳቢያ ሥራቸው ሁሉ የመጨነቅና የመርበትበት ስሜት ይታይበታል፡፡ ጭንቀት ደግሞ የሚያውቁትን ያህል እንኳን እንዳይሞክሩ ስለሚያደርግ ተጽዕኖው የበረታ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ አስቀድመው የሚያጠኑ ተማሪዎች በቂ ጊዜና የመረጋጋት ስሜት ስለሚታይባቸው የሚያጠኑትን የትምህርት ዓይነት በምን መንገድ እንደሚያጠኑ ቀድመው የመወሰን ችሎታ እንዳላቸውና ይህም ለውጤት እንደሚያበቃቸው በሚያደርጉት መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ ሲጠየቁየሚችሉትን ጥያቄ ሁሉ አስቀድመው የመተንበይ ችሎታንም ያስገኝላቸዋል የሚል ነው፡፡

ፈተና ከመድረሱ በት የሚያጠኑ ተማሪዎች በራስ የመተማመንና የመረጋጋት ዕድል እንደሚያስገኝላቸውና ይህም በውጤታቸው ላይ አዎንታዊ ጎን ያለው መሆኑን ቀደም ሲል ምሁራኑ ቢያስገነዝቡም ይህንኑ የመረጋጋትና በራስ የመተማመን ስሜትን አሉታዊ በሆነ መልኩ የተመለከቱት ፀሀፍት አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል Morgan (1968) አንዱ ሲሆን የሚከተለውን ይላል፤

> ፈተና ከመድረሱ በት የሚያጠኑ ተማሪዎች ምንም እንኳን በራስ የመተማመን ስሜታቸው ከፍተኛ ቢሆንም ከመጠን ያለፈ በራስ የመተማመን ሁኔታ ደግሞ ሁሉ ጊዜ ተማሪዎችን ውጤታማ ያደርጋል ማለት አይቻልም፡፡ ይህ ከፍተኛ የሆነ በራስ የመተማመን ስሜት በቀጣይ ሥራቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድርባቸዋል፡፡

Ball (1985) ከፈተና በፊት የማጥናትን አሉታዊ ጎን ሲገልፅ፣ አንድ ተማሪ አስቀድሜ አጥንቻለሁና ሁሉን ነገር አውቃለሁ እያለ በተረጋጋ ቁጥር "አላውቅም" የሚል ስሜት ስለማያድርበት ድንገት በፈተናው ላይ የማያውቀው ነገር ሲገጥመው የሚፈጥረብተ ድንጋጤና አለመረጋጋት ቀድም ሲል የነበረውን በራስ የመተማመን ስሜት ይንደዋል ይላል፡፡

ፀሀፍቱ ፈተና ከመድረሱ በፊት ማጥናት ከፍተኛ የሆነ የመረጋጋትና በራስ የመተማመን ስሜት በተማሪዎች ላይ መፍጠሩን ሁሉም ይስማሙበታል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ከፍተኛ በራስ የመተማመንና የመረጋጋት ስሜት ደግሞ ከሌሎች

ተማሪዎች በተሻለና በላቀ ሁኔታ አውቃለሁ ወይም ተዘጋጅቻለሁ የሚል ስሜት ያሳድራል፡፡ ይህም ራሱን እስከመካብ ሊያደርሰው ይችላል፡፡ በዚህ ስሜት ተሞልቶ ወደ ፈተና አዳራሽ የገባ ተማሪ ደገሞ ፈተናውን በሚሰራበት ጊዜ በአጋጣሚ ከእሱ እሳቤና ዝግጅት ወጣ ባለ መልኩ የማያውቀው ጥያቄ ቢገጥመው መረጋጋቱ ወዲያውኑ ወደ ጭንቀትና ድንጋጤ ስለሚቀየር እንደተጠበቀው ለጥሩ ውጤት ሊበቃ የማይችል ይሆናል፡፡ ችግሩ የገጠመው ፈተናውን ገና ሲጀምር ከሆነ ደግሞ ቀሪውን ፈተና በተረጋጋ ሁኔታ ለመስራት ስለማይችል ተጽዕኖ የከፋ እንደሚሆን ለመረዳት ይቻላል፡፡

Webb (1987:220-227) ፈተና ከመድረሱ በፊት ማጥናት አብዛኛው የእንግሊዝ ተማሪዎችን ምንም እንኳን ውጤታማ ሊያደርጋቸው እንደሚችል ቢገምትም፣ የሚያጠኑበት ጊዜ ድግግሞሽ የበዛበትና ዘወትራዊ በመሆኑ ተማሪዎቹ እንደሚሰለቹና ይህም ትምህርቱን አምርረው እንዲጠሉት ያደርጋቸዋል ይላል፡፡

ይህ ምሁር ፈተና ከመድረሱ በፊት ማጥናት ለጥሩ ውጤት የሚያበቃ መሆኑን ቢያምንበትም፣ አስተያየቱን በሌላ መልኩ እንደተገነዘበው እንረዳለን፡፡ ተማሪዎቹ አስቀድመው በማጥናት ለፈተና እንዲዘጋጁ የተመከሩ በመሆኑ ይህ ዘወትራዊ የሆነ አሠራር ደግሞ ተማሪዎቹን ሊያሰለች ስለሚችል ጉዳትም እንዳለው አመልክቷል፡፡ የፀሀፊው አስተያየት አስቀድመው እንዲዘጋጅ መምከራቸውን ሙሉ በሙሉ የተቃወመው አይደለም ጉትጎታው እሱ የጠቀሳቸውን ችግሮች ማለትም መሰልቸትና ጥላቻን እንዳያስከትሉ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል እንደማለት ነው፡፡

በአጠቃለይ በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የተመለከትናቸው የተለያዩ ተመራማሪዎች አገላለጽ የሚያስገነዝበን፣ ተማሪዎች ከፈተና በፊት አጥንተው ለፈተና ቢዘጋጁ ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉ መሆኑን እንደሚስማሙበት ነው፡፡ የጥናቱ ስልት የሚያስከትለውን ተማሪዎች ጎናዊ ጉዳትም አስቀድሞ በመገንዘብ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸው ያመለክታል፡፡

### 2.1.3 ፈተና ሲደርስ ማጥናት ውጤታማ ያደርጋል

ተማሪዎች ለፈተና የሚዘጋጁበት ጊዜ ይለያያል፡፡ በመሆኑም አንዳንዶቹ ፈተና ሲቃረብ ጥናታቸውን የሚጀምሩ አሉ፡፡ ይሁን እንጂ የዚህ ዓይነቱን ልምድ በሚጠቀሙት ተማሪዎች ላይ ምሁራን የሰጡት አስተያየት በሁለት የተከፈለ ነው፡፡ ይህም ማለት አዎንታዊና አሉታዊ ጎኑን ማብራራት ነው፡፡ ሁለቱም ጎራዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በቅድሚያ ፈተና ሲደርስ ማጥናት አዎንታዊ ጎን አለው ብለው ከሰጡት አስተያየት እንጀምር፡፡ Morgan (1968: 135-141) እንደሚለው፣ የማስታወስ ችሎታ ይበልጥ የሚፋጠነው ለፈተና ጥቂት ጊዜያት ሲቀረው በሚደረግ ጥናት ነው፡፡ ተማሪዎች የመፈተኛ ሰዓታቸው እየተቃረበ በመጣ ቁጥር እያንዳንዱን ሰኮንድ በአግባቡ ስለሚጠቀሙበት ውጤታማ ይሆናሉ ይላል፡፡

ከተሰነዘረው አስተያየት የምንረዳው ቁምነገር ተማሪዎች አስቀድመው በማጥናት ለፈተና ቢዘጋጁ ከጊዜ መርዘምና ቆይታ አንፃር ያገኙት ግንዛቤ ሊዘነጋ ስለሚችል ነው፡፡ እንዲሁም ለመፈተን የቀራቸው ጊዜ እያጠረ በመጣ ቁጥር ቀሪ ሰዓቶቸውን ሳያሰልሱ በጥንቃቄ ሊጠቀሙበት ስለሚችሉ ለውጤት ሊያበቃቸው ይችላል፡፡ ይህ አስተያየት ደግሞ የየተማሪዎችን የግል ችሎታ የሚጠይቅ ይመስላል፡፡ አንዳንዱ ተማሪ አንዴ የተረዳውን ነገር ምንም እንኳን ቆይቶ ቢጠየቅ የማይዘነጋው ሲሆን አንዳንዱ ደግሞ ነገሮችን የማስታወስ ችሎታው የወዲያውኑ በመሆኑ አንፃራዊ በሆነ መልኩ ማየት ተገቢ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች ለፈተና የቀራቸው ጊዜ ረጅም ከሆነ ጊዜ አለኝ በሚል ሳቢያ ሊዘናጉ ስለሚችሉ እንደነዚህ ዓይነት ባህሪ ላላቸው ተማሪዎች የአጭር ጊዜ ጥናት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

በሌላ በኩል Webb (1987: 220-227) የላይኛውን ሀሳብ በመጋራት የሚከተለውን ይላል፡፡ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ማለትም በእንግሊዝኛ በጃማይካ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መካከል በተካሄው ጥናት የእንግሊዝ ተማሪዎች ከፈተና በፊት አጥንተው አጥጋቢ ውጤት ሲያስመዘግቡ የጃማይካ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ግን ፈተና ሲደርስ ያጠኑት ተማሪዎች ውጤታማ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይህንንም በመረጃ ያረጋገጠው ውጤት መሆኑን ዌብ ያስገነዝበናል፡፡ የትዕግስት (1998: 38) የጥናት ውጤት እንደሚያስገነዝበንም፣ ፈተና ሲደርስ አጥንተው ለፈተና የተቀመጡት ተማሪዎች ውጤታቸው የተሻለ ሆኖ እንደተገኘ ታስገነዝባለች፡፡

ከሁለቱም ፀሀፍት የጥናት ውጤት እንደምንገነዘበው፣ ፈተና ከመድረሱ በፊት የሚያጠኑት ተማሪዎች ውጤታማ ሆነው እንደተገኙ ሁሉ ፈተና ሲደርስ ያጠኑትም ውጤታማ ሆነው መገኘታቸውን ነው፡፡ ይህ አስተያየት ደግሞ ስለሁኔታው በጥልቀት እንድናስብና እንድንመራመር የሚገፋፋ ጉዳይ ነው፡፡ ምናልባትም ከፈተና ጊዜ ምርጫ ባሻገር የምንመለከታቸው ሌሎች ተላውጦዎች እንዳሉ የሚያመለክት ነው፡፡ ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረው፣ የትምህርቱ ዓይነት፣ የተፈናው ባህሪ፣ የተማሪዎች ዕድሜ፣ ፆታ፣ ዳራ፣ ወዘተ. ጭምር መፈተሽ ያለባቸው ይመስላል፡፡

በአጠቃለይ ፈተና ሲደርስ የሚያጠኑ ተማሪዎች ውጤታማ የሚሆኑበት ምክንያት እንደፀሀፍቱ አባባል ቀኑ እያጠረ በመጣ ቁጥር ጊዜያቸውን ሳያባክኑ

በአግባቡ እንደሚጠቀሙበትና በጥናቱና በፈተናው ዕለት ቅርርብ የተነሳ ያጠኑትን ሳይዘነጉት ለማስታወስ ስለሚረዳቸውና የአጠናን ልምዳቸውም የወዲያውኑነት ባህሪ ስለላው ቶሎ በሥራ ላይ በማዋል ይጠቀሙበታል የሚል ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፈተና ሲደርስ ስለሚያጠኑ ተማሪዎች የተሰነዘሩትን አሉታዊ ብያኔዎች እንመልከት፡፡

Slavin (1997: 458-510)፣ ፈተና ሲደርስ የሚያጠኑ ተማሪዎች ወዲያው ያነበቡትን ነገር በደንብ ሳያብላሉ በተጨማሪ የሚያነቡት ሌላ ነገር መጥቶ ግጭት ይፈጥርባቸዋል፡፡ የሚያነቡትን ነገር ለማዋሀድ በቂ ጊዜ ስለሌላቸው በፈተና ላይ ሁሉም ነገር ህልም ይሆንባቸዋል፤ ሥራቸው ሁሉ ቅጽበታዊ ይሆናል፡፡ ጥናት ደግሞ ከመቅጽበት የሚያከናውኑት ተግባር ሳይሆን ሰፊ ጊዜና ትዕግስትን የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ፈተና ሲደርስ በማጥናት የሚገኝ ሳይሆን በሂደት የሚመጣ ነው፡፡ ስለዚህም ፈተና ሲደርስ የሚያጠኑ ተማሪዎች ውጤታቸው የሰመረ አይደለም ትላለች፡፡

እንደ Slavin (1997: 215) አገላለጽ፣ ፈተና ሲደርስ የሚያጠኑ ተማሪዎች ውጤታማ ሲሆኑ የማይችሉት ለፈተና የቀራቸው ጊዜ ማጠርን በዋናነት በመጥቀስ ነው፡፡ ጥናታቸው ቅጽበታዊ በመሆኑ ያነበቡትን ነገር በሚገባ አጣጥሞ ለመገንዘብ ወይም የሚያነቡትን ነገር በጥልቀት ለመመርመር ዕድል ስለሌላቸው ነው፡፡ የሚያነቡት ነገር ብዛትና ለፈተና የቀራቸው ጊዜ ማጠር ከሚፈጥርባቸው ጫና የተነሳ አንዱ ሀሳብ ከሌላው ሀሳብ ጋር እየተደባለቀ ግጭት ስለሚፈጥርባቸው ያነበቡትን ነገር በሚባ ማስታወስ እንደማይችሉም ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም የጊዜ እጥረቱ በፈጠረባቸው ጫና የተነሳ ፈተናውን በእርግጠኝነት ወስኖ መመለስ ይሳናቸዋል፡፡ ስለዚህ ጥናት የወዲያውኑ ክንዋኔ ሳይሆን ሰፊ ጊዜ ተሰጥቶ በእርጋታ የሚሰራ ሥራ ነው፡፡

እነ Svaz (1982) እና Mohan (1993) እንደሚሉት ፈተና ሲደርስ የሚጠኑ ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ውጤታማ መሆን እንደማይችሉና አጠናናቸው ጥ...ፊያ የበዛበት መሆኑ አንደኛው ምክንያት ሲሆን ሌላው ደግሞ አለመረጋጋትን የሚያስከትል መሆኑ ነው፡፡ ፈተና ሲደርስ የሚያጠኑ ተማሪዎች ጥናታቸውን ከየት ጀምረው የት መጨረስ እንዳለባቸው ስለማያውቁ በዚህም ሳቢያ አጠናናቸው ያዝ ለቀቅ አይነት በመሆኑ አንዱንም ሳይጨብጡት ወደ መፈተኛ አዳራሽ መግባታቸው ትልቅ ችግር ያስከትልባቸዋል፡፡

ከላይ ከተሰጠው ሀሳብ የምንገነዘበው የአጠናን ዘዴው የሚያስከትለው ጥድፊያን ነው፡፡ ጥድፊያ ደግሞ አለመረጋጋትንና ጭንቀትን ያስከትላል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ተዋክበውና ተጠበው የሚሠሩት ወይም የሚያጠኑት ለጥሩ ውጤት አያበቃቸውም፡፡ ምክንያቱም ለፈተና የቀራቸው ጊዜ አጭር መሆኑና የትምህርቶቹ ብዛት ተደራራቢ

ጫና ስለሚፈጥሩባቸው ሁሉንም ለማዳረስ ሲሉ አብላልተውና አጣርተው አያነቡትም። ስለዚህ ተማሪዎች ስለእያንዳንዱ ትምህርት በቂ ግንዛቤ ሳይኖራቸው ማለትም ራሳቸውን በሚገባ ለፈተና ሳያዘጋጁ የመፈተኛ ሰዓታቸው ይደርሳል። ፈተናውን መስራት እንደጀመሩም የማይመልሱት ጥያቄ ሲገጥማቸው ጭንቀታቸው ይበረታል። በመጨረሻም የተሰጣቸው ጊዜ ይገባደዳል። በዚህም ሳቢያ ከአጠናን ዘዴያቸው የተነሳ ብቻ ውጤታቸው አጥጋቢ ሊሆን አይችልም።

በተጨማሪም Fishman (1986: 169-176) እንደሚያብራሩት፤ፈተና ሲደርስ የሚያጠኑ ተማሪዎች በማንኛውም ፈተና ወቅት ይጨነቃሉ። የሚጨነቁትም « እንዴት ብዬ ፈተናውን ተጠንቅቂ ልስራ?» በሚል ሳይሆን « እንዴት ብዬ ፈተናውን እንደነገሩ ሰርቼ ልጨርሰው» የሚል ነው ይላል።

አባባሉ ተማሪዎቹ ፈተናውን በሚሰሩበት ወቅት ለጥናታቸው ሰፊ ጊዜ ካለመስጠታቸው የተነሳ ጭንቀቱ የሚፈጥርባቸው የግዴለሽነት ስሜት እንደነገሩ ሰርተው ለመገላገል ሲሞክሩ መስተዋሉን ነው። በመሆኑም እያንዳንዱን ጥያቄ በጥንቃቄ ሲሰሩ አይታዩም። ይህ ለፈተናው የሚያሳዩት የግድየለሽነት ስሜት ደግሞ በመጨረሻ የትምህርት ፍላጎታቸውን ከመሸርሸሩም በላይ በትምህርቱም ላይ ጥላቻ ያሳድርባቸዋል። ቀደም ሲል ከተሰነዘሩት አስተያየቶች ወጣ ባለ መልኩ ሀሳብ የሰነዘሩ ፀሀፍትም አሉ።

Curley et al. (1987: 324-343) እንዳብራሩት፤ተማሪዎች የሚመዘኑበት መመዘኛ አንድ ዓይነት እስከሆነ ድረስ በየራሳቸው መንገድ ቢያጠኑም እንኳን በውጤት ረገድ የጎላ ልዩነት አያሳዩም፤ምክንያቱም የአጠናን ዘዴ መለያየት ከውጤት ጋር ብዙም ግንኙነት ስለሌለው ነው ይላሉ።

ከአባባሉ እንደምንረዳው ተማሪዎች የአጠናን ልምዳቸው የተለያየ ሊሆን እንደሚችል ማለትም በሚመቻቸው መንገድ ጥናታቸውን ቢያከናውኑም የሚፈተኑት ፈተና ተመሳሳይ እስከሆነ ድረስ በውጤታቸው ላይ ተጽዕኖ አለማሳደሩን ነው። ይህም እያንዳንዱ ተማሪ ነገሮችን የሚገነዘብበት መንገድ የተለያየ መሆኑን የሚያስገነዝብም ጭምር ነው።

በተጨማሪም Thomas et al. (1987:344-364) ሲገልፁ፣የተማሪዎች ውጤታማ መሆንና አለመሆን ጉዳዩ በቀጥታ ከአጠናን ልምድ ጋር ተዛማጅነት እንዳለውና ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ የሚችሉት ቀድመው የሚያጠኑ ተማሪዎች መሆናቸው ቢያምኑበትም አንድ በጠቅላላ ዕውቀት ምዘና ላይ የተካሄደን ጥናት ጠቅሰው እንዳስፈሩት፣ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ ከጥናት ልምድ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙ ነት የለውም ይላሉ።

ተመራማሪዎቹ ያስገነዘቡን የተማሪዎች ውጤት ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ መሆን የሚወሰነው በሚፈተኑት የፈተና ዓይነት የሚወሰን መሆኑን ነው። ይህም ማለት ፈተናው በሚማሩት ትምህርት ላይ የሚያተኩር ከሆነ ከአጠናን ልምዳቸው ጋር እንደሚያያዝና የፈተናው ዓይነት ጠቅላላ ዕውቀትን የሚመለከት ከሆነ ደግሞ

ከፈተና በፊትም ሆነ ፈተና ሲደርስ ቢዘጋጁም በውጤታቸው ላይ ተፅዕኖ አያሳድርም የሚል አንድምታ አላቸው።

## 2.2. ተማሪዎች እንዴት ማጥናት አለባቸው?

### 2.2.1 የጥናት ፕሮግራም በማዘጋጀትና በአግባቡ በመጠቀም

አቡሽ (1998፣16-20) በአንድ ወቅት መምህርትና በኋላም የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት የሰነዘሩትን ሀሳብ ጠቅሶ እንዳብራራው፣«ህይወትህን መቆጣጠር ካሻህ ፣ጊዜን መቆጣጣር ይኖርብሀል»፣ የሰዓትህ አለቃ መሆን ስትፈልግ መጀመሪያ ዓላማና ዕቅድ ሊኖርህ ይገባል። እነዚህንም በተግባር አዋልክ ማለት ጊዜን ተቆጣጠርከው ማለት ነው» ብሏል።

«ጊዜ ወርቅ ናት» የሚለው የአበው አባባል እውነትነት እንዳለውና እንዲያውም ጊዜን በገንዘብ መግዛት ባለመቻሉ ከወርቅም በላይ መሆኑንና በገንዘብ ሊተመን እንዳማይቻል ያስገነዝበናል። የእያንዳንዳችን የህይወት ምዕራፍ የተከፋፈለው በጊዜ እንደሆነ ሁሉ፣ጊዜ የህይወታችን ሁነኛው ክፍል እንደሆነ በመረዳት ለጊዜ ክብር መስጠት ይኖርብናል። ይህም ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ነው። ጊዜ ለተማሪዎች እስትንፋሳቸው ናት። ተማሪዎች ጊዜያቸውን በስነስርዓት በመከፋፈል ሳይጨነቁና የተጣበበ የጊዜ ሁኔታ ሳይገጥማቸው እያንዳንዷን ሰዓት በተግባር ላይ ማዋል ይኖርባቸዋል።

ጊዜን በእቅድ መምራት ብዙ ጥቅሞችን ያስገኛል። በመሆኑም ተማሪዎች ጊዜያቸውን በእቅድ በመከፋፈል የሚጠቀሙበት ከሆነ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያገኛሉ፤

/www. Iss. stthomas.edu/study guides/

- ለጥናት በከፍተኛ ሁኔታ ሊነሳሱ ይችላሉ፣
- የማይወዷቸውን የትምህርት ዓይነቶች እንዲወዷቸው ይሆናሉ፣
- ሁሉንም ትምህርቶች በኩልና በሚገባ እንዲያጠኗቸው ይሆናሉ፣
- ጥናትን አሰልቺ ወይም እንደሥራ መቁጠር ሳይሆን ፊልምና ትያትር ወይም ኳስ ጨዋታ እንደመመልከት ይዝናኑበታል፣
- የትምህርት ክለሳ ፕሮግራማቸው ትክክለኛና ያልተዛባ ከመሆኑም በላይ ባጭር ጊዜ ውስጥ ያጠኑትን እንዲረዱት ይረዳቸዋል፣
- አእምሮን ነፃና ለጥናት የተዘጋጀ ያደርጋል፣
- የጥናት ሰዓት የእረፍት ጊዜን በሚገባ እንዲጠቀሙት ይረዳቸዋል፣
- የጥናት ሰዓትን ከማህበራዊ ግንኙነቶች ጋር የተመጣጠነ ስለሚያደርገው በጥናት ውጤታማ እንዲሆኑ ይረዳል፣
- የጥናት ጊዜንና የመዝናኛ ጊዜን ለይተው እንዲረዱና ባአግባቡ ሁሉንም እንዲጠቀሙበት ይመራቻዋል፣

- ማንኛውንም የዕለት ዕለት እንቅስቃሴያቸውን በመምራት ሁሉም ነገር በታቀደለት ጊዜ እንዲከናወን ስለሚረዳ ከመጨነቅ ያድናቸዋል፣
- በማንኛውም የዕለት ተዕለት እንቅስቃቂያችን በሰዓት ለመገኘት ይጠቅመናል፤ እንዲሁም አስፈላጊ ቀጠሮዎችንና ግዴታዎችን እንዳንረሳ በማስታወሻነት ይረዳናል።
- በማንኛውም ሰዓት«ጊዜን በከንቱ እያባከንኩ ነው ወይስ በእርግጥ በአግባቡ እየተጠቀምኩበት ነው?» ብለን ራሳችንን መጠየቅና መልስ መስጠት እንጀምራለን።

ተማሪዎች የጥናት ጊዜ እቅዳቸውን ካዘጋጁ በኋላ በቀን ውስጥ ሊከውኑ የሚችሉትን ሌሎች ተግባራትንም ጭምር በሠንጠረዥ በማዘጋጀት የጊዜ አጠቃቀማቸውን መልሰው መመርመር ይገባቸዋል። ሲበን (1997፣64-67) እቅድን መልሶ ለመመርመር የሚከተሉትን ጥያቄዎች እራሳቸውን መጠየቅ እንደሚገባቸው ይጠቁማል። ግምገማው በሳምንታዊ እቅድ ላይ የተመሠረተ ነው፤

ከላይ ከተሰጠው አስተያየት መረዳት እንደምንችለው በመጀመሪያ ተማሪዎች መዝግበው የያዟቸውን ሳዓታት ድምር ከሳምንቱ ሰዓታት ላይ መቀነስ እንዳለባቸውና ከዚህ የተረፉ ሰዓታት ካሉ በምን ላይ እንዳዋሏቸው ራሳቸውን በመጠየቅ ለጥናታቸው በቂ ጊዜ መመደባቸውን መረዳት ነው። ይህም አንድ ተማሪ በተለይ በከፍተኛ ትምህርት ስያንዳንዱ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለቆየበት ሰዓት ውጭ ሁለት ሰዓታት የጥናት ጊዜ እንደሚያስፈልጉት ያስገነዝባል ለምሳሌ ተማሪው አንድ የትምርህርት ዓይነት በሳምንት ሶስት ሰዓታት በክፍል ውስጥ ቢማር ይህንኑ ትምህርት በሳምንት ውስጥ ለስድስት ሰዓታት ያህል ለማጥናት ማቀድ ይኖርበታል ማለት ነው።

እንዲሁም ተማሪዎች ለመዝናናት የሚያስፈልጉትን ወይም የሚያባክኑትን ጊዜ አስቀድሞ መረዳት እንዳለባቸው በመረዳት ይህም ያላግባብ የሚባክነውን ጊዜ ለጥናት ቢውል ፍሬያማ ሊያደርገው ይችላልና ነው። ዘወትር ጊዜያቸውን የሚወስድባቸውን ለምሳሌ ሱስ ሊሆኑ የሚችሉ ልዩ ልዩ ጨዋታዎች፣ኳስ ጨዋታ፣ ቴሌቭዥን መመልከት ወዘተ. . . ከሆኑ ከትምህርታቸው ሊያዘናጉ የሚችሉ መሆናቸውን መረዳት ይገባል።

እንዲሁም ተማሪዎች ለእንቅልፋቸውና ለአመጋገባቸው በቂና የተወሰነ ጊዜ መመደብ ይኖርባቸዋል፡ ብዙ ሰዎች ለጥናት ወይም ለመዝናናት ጊዜ ሲያንሳቸው ከእንቅልፍ ጊዜያቸው ላይ ቀንሰው ስለሚጠቀሙ በቂ እንቅልፍ ያለማግኘት ደግሞ በቀጣይ የጥናት ጊዜአቸው ላይ ተጽኖ ስለሚኖረው ነው።

በመጨረሻም አለ አግባብ የሚደረጉ ጉዞዎች ለጥናት ሊውሉ የሚችሉ ጊዜያትን ሊያባክኑ ስለሚችሉና ዘወትር በከንቱ የሚባክኑትን ሰዓታት ለማስታወስና ለማሰብ መሞከሩ ተገቢ ነው ምክንያቱም ተማሪዎች እነዚህን ሰዓታት ሁሉ ለጥናታቸው ቢያውሉት ውጤታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ ከወዲሁ መገመት

አያዳግትም። በአጠቃላይ ተማሪዎች በእርግጠኝነት ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉት በሳምንት ውስጥ ያሉትን ሰዓታት እንደአስፈላጊነታቸው ለተለያዩ ተግባራት በመከፋፈል ረገድ ሲያደርጉ የሚገባቸውን ጥንቃቄና ለየትኛውም ተግባር ቅድሚያ መስጠት እንዳለባቸው ያስገነዝባል።

### 2.2.2 ለተማሪዎች ማበጁ የጥናት እቅድ አዘገጃጀት ስልቶች

ተማሪዎች የጥናት ፕሮግራማቸውን ሲያዘጋጁ በሚከተሉት የጥናት ስልቶች በተጨማሪ መጠቀም እንዳለባቸው አቡሽ (1998: 17-18) እና ስማቸው (1990: 9-12) የሚከተሉት ነጥቦችን ይጠቁማሉ

- መጀመሪያ እያንዳንዱን ሰዓት ለጥናት ለማዋል መጣጣር፤
- ከማታ ይልቅ የቀን ሰዓት መጠቀም።
- ወደ ክፍል ከማምራት በፊት በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ የሚሰጠውን የትምህርት ዓይነት ላዩን አንብቦ ወደ ክፍል መግባት።
- የትምህርት ክፍለ ጊዜውን እንደጨረሱ በቀጥታ ስለተማሩት ትምህርት ክለሳ ማድረግ።
- በቅድሚያ መነበብ የሚገባውን የትምህርት ዓይነቶች መምረጥና ሁሉንም የትምህርት ዓይነቶች በየቅደም ተከተል ለማንበብ ፕሮግራም መያዝ።
- እጅግ የተንዛዙ ማስታወሻዎችን አለመጠቀም፤ በተቻለ መጠን አጠር አጠር አድርጎ በራስ ቋንቋ በመያዝ ማንበብ።
- እንቅልፍ በሚመጣበት ሰዓት በቀጥታ መተኛት ይገባል።

ከእንቅልፍ ጋር እየታገሉ ማንበብ በፍፁም አይደገፍም፣ ጥሩ ውጤት ለማምጣትም አይረዳም። ንቁ በሚሆኑበት ሰዓት ደግሞ የተቋረጠውን ጥናት ማንበብ በጣም ጠቃሚ ነው። ሁኔታው ከተማሪ ተማሪና እንደየትምህርት ዓይነ‍ት ቢወሰንም ተማሪዎች በቀን ምን ያህል ጊዜ ማንበብ እንደሚችሉ ማወቅ አለባቸው። በተቻለ መጠን ግን ለአንድ ሰዓት የክፍል ውስጥ ትምህርት የሁለት ሰዓት ጥናት ያስፈልገዋል። ሰዓትም ለጥናትና ለእረፍት በሚገባ መከፋፈል በአማካይ ለአንድ ሰዓት ጥናት አስር ደቂቃ ማረፍ ይቻላል። የእንቅልፍን ሰዓት በምንም አይነት አለማዛባት። በቀን ስምንት ሰዓት መተኛት ይገባል። በቂ እንቅልፍ ያገኘ አእምሮ ደግሞ በአጭር ጊዜ ብዙ ነገር ለመስራት ያስችላል። ለጥናት፣ ለእረፍት እንዲሁም ለመኝታ ከታቀደው ሰዓት ውጪ የተወሰኑ ሽርፍራፊ ጊዜያት ማትረፍ ጠቃሚ ይሆናል። ይኸም አንዳንድ ሁኔታዎች ሲጎድሉ በመሙላትና ረጅም የጥናት ጊዜ ሲያስፈልግ ይጠቅማሉ። በአጠቃላይ ለጥናት ብቻ ሳይሆን ለእለታዊ እንቅስቃሴም እቅድ ማውጣት ህይወትን በትክክለኛው መንገድ ለመምራት ያስችላልና በታቀደው መልኩ መጠቀም ተገቢ ነው።

ከአባባሉ እንደምንረዳው የጥናት ፕሮግራምን አዘጋጅቶ በብልሀት መጠቀም መቻልን የሚያስገነዝብ ሲሆን ስልቱ ፕሮግራማቸውን ተግባራዊ ሲያደርጉና ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አቅጣጫ ከማሳየት ባሻገር ለፈተና ምን ያህል ጊዜ ሲቀራቸው ማጥናት እንዳለባቸው በግልፅ የሚያስገነዝብ አይደለም፡ ይሁን እንጂ ከአንዳንድ አስተያየቶች ለመረዳት እንደምንችለው ተማሪዎች ጥናታቸውን ሳያሰልሱ ማጥናትና መትጋት እንዳለባቸው ለመረዳት ይቻላል::

ከዚህም በተጨማሪም ሊበን (1997) ስለዕቅድ ዝግጅትና ጊዜ አጠቃቀም የሚከተለውን ይለናል:: እያንዳንዱ ሰው በህይወቱ ወቅት የጊዜ ባንክ አለው:: ሁል ጊዜ ጧት ጧት ለቀኑ 1440 ደቂቃዎች ለግሶን ሁል ጊዜ ማታ ማታ ያልተጠቀምንበትን ሁሉ ይሰርዘዋል፤ አንድም ደቂቃ አያሳድርልንም፤ አያስቀምጥልንም:: በየቀኑ ግን እንደ አዲስና ሙሉውን ጊዜ እንድንጠቀምበት ይሰጠናል:: በዛ ቀን የተፈቀደልንን መጠቀም ካልቻልን የራሳችን ኪሳራ ነው፤ወደ ኋላ መመለስ አይቻልም በማለት ከነገም ላይ ዛሬ መጠቀም እንደማንችልና ዛሬ የተሰጠንን ዛሬ ብቻ ልንጠቀምበት መሞከር እንዳለብን ያስገነዝበናል:: ይህም በመሆኑ ቀኑ ሳያመልጠን ከዛሬ ላይ ብዙውን ለመጠቀም መሞከር ብልህነት ነው::

www. Iss. Stthomas edu/study guides/ የሚለው ድረ-ገጽ እንደሚያመለክተን የዕቅድ ዝግጅትና የጊዜ አጠቃቀምን በተመለከተ ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም በእጃችን ላይ ካለው ሰዓት አብዛኛውን ለሥራ በማዋል ውጤታማ መሆን እንደሚቻል የሚያስገነዝብ ነው:: ጊዜን በአግባቡና በእቅድ ለመጠቀም የባህርይ ለውጥ እስኪዋሀደንና የጊዜ አጠቃቀም ችሎታ የዘወትር ልምድ እስኪሆነን ድረስ ጠንካራ የሆነ ራስን የመቆጣጠርና ግለሥርዓትን ይጠይቃል፤ይህም ያወጣነውን ዝርዝር ዕቅድ ወደ ተግባር ለመቀየር ካልተንቀሳቀስን የጊዜ ሰንጠረዥ ብቻውን ዋጋ ቢስ መሆኑን ያመላክተናል::

ውጤታማ የጊዜ አጠቃቀም ሚዛናዊ መሆን ይገባዋል:: የተዋጣለት ዕቅድና የጊዜ አጠቃቀም ብቻ አንድን ሰው ጎበዝ ተማሪ ወይም ሠራተኛ ሊያሰኙት አይችሉም:: ምክንያቱም በጣም ጥቃቅን በሆኑ ዝርዝር ዕቅድና ድርጊቶች ላይ በማተኮር ብቻ ዋና ዋና ተግባራት ሊረሱ ይችላሉና ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ደካማ የእቅድና የጊዜ አጠቃቀም ችሎታ አንድን ሰው ዋጋ ቢስ አያደርጉትም:: እንዲያውም አንዳንድ ብሩህ ሰዎች ባላቸው የጊዜና የገንዘብ አያያዝ ችሎታ ማነስና ልምድ የተነሳ ሁል ጊዜ«አንድ ቀንና አንድ ብር ሲያንሳቸው» ይታያሉ:: ስለሆነም የጊዜ አጠቃቀም ዕቅድ የሚያስፈልገን ለህይወታችን መሠረት ያለው አቋም ለመስጠትና የህሊና ዕረፍት ለማግኘት ነው:: በተመሳሳይ ሁኔታ ተማሪዎች ለጥናትም ሆነ ለተጓዳኝ ተግባሮቻቸው ያላቸውን ጊዜ በዕቅድ የሚጠቀሙ ከሆነ፣ድርጊቶችን በተገቢው ጊዜ ለመጨረስ በተለይም በአንድ ጊዜ በተለያዩ ጉዳዮች በተጠመድን ወቅት ያለንን ውስን ጊዜ በአግባቡ ከፋፍለን በመጠቀም በሥራ መብዛትና በጊዜ እጥረት ምክንያት ከሚመጣው ጫናና ጭንቀት ሊድኑ ይችላሉ::

በመጨረሻም የተማሪዎች የጊዜ አጠቃቀም ማቀጃዎች በአራት ዓይነት ተከፍለው ሊዘጋጁ ይችላሉ፡፡ እነዚህም፡-

- የክፍለ -ዓመት/የሴሚስተር ወይም የሩብ ዓመት/
- ወርሃዊ
- ሳምንታዊ እና
- ዕለታዊ ናቸው፡፡

የሴሚስተር ወይም የሩብ ዓመት እና ወርሃዊ ማቀጃዎች ታላላቅና በርቀት ቀድመን ልናውቃቸው የምንችላቸውን ድርጊቶች ለመመዝገብ ሲረዱን ሳምንታዊና ዕለታዊ እቅዶች ደግሞ መደበኛ ድርጊቶችን፣ መለስተኛ ፈተናዎችንና የቤት ሥራዎችን፣ ወዘተ ለመመደብ ይውላሉ፡፡ በአጠቃላይ የጊዜ ዕቅድና አጠቃቀም ችሎታ በዳበረ ቁጥር ሰዎች ግዴታዎችን ለመወጣት በጊዜ ማጠር ወይም ከዛሬ ነገ እሰራዋለሁ በማለት ሳይሰሩ በሚሰነብቱ ሥራዎች የተነሳ የሚመጣውን የአዕምሮ መወጠርና መረበሽ ይቀንሳል፡፡

## 2.2.3 ጥናትን በቡድን ማከናወን

እንደ ሊበን (1997፣186-190) አበሹ (1998:54-61) እና www. Uga-edu/dael groups አገላለጽ፣የጋራ ዝንባሌ ያላቸው ተማሪዎች በጋራ ሆነው በማንበብ፣በመጠያየቅ፣በመወያየትና በማስረዳት የተሻለ እንደሚያስታውሱ የተገነዘቡ ናቸው፡፡ ይህ የሚመሠርቱት የጥናት ቡድንም በግል ጥናት ወቅት የሚያጋጥሟቸውን አስቸጋሪ ጥያቄዎች ተረዳድተው ለመፍታትና የተለያዩ የጥናት ዘዴዎች ለመለዋወጥ /ለስማረዳቸው መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

ይህም በመሆኑ የጥናት ቡድን የሚከተሉት ተጨማሪ ጥቅሞች እንዳሉት እነዚሁ አጥኝዎች ጠቁመዋል፤

የሚማሩት ትምህርት አስደሳች መልክ እንደሚኖረውና የተማሪዎች ባህሪ የተለያየ እንደመሆኑ በተለይም በክፍል ውስጥ ጥያቄ ለመጠየቅ ለሚያፍሩ ወይም ደግሞ የመጠየቅ አጋጣሚ ለሌላቸው ተማሪዎች ጥሩ ዕድል ስለሚፈጥርላቸው ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በግል ጥናት ወቅት ሳይገባቸው የቀሩትን ሀሳቦችና ሳይያዙ የታለፉ ማስታወሻዎችን ከሌሎች የቡድን አባላት በቀላሉ ለማግኘት ስለሚያግዛቸው ነው፡፡

የቡድን ጥናት ለመማማር አጋጣሚና ልምድን ይሰጣል፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎች መልዕክት የማስተላለፍ፣ በንቃት የማዳመጥንና በአትኩሮት የመቆየት ችሎታን ስለሚያዳብር ነው፡፡ የችግር አፈታት ዘዴዎችንም ሂደቶችን መማማር የሚያስችል የጥናት ዘዴ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ የቡድን ጥናት ግላዊ ስነ- ስርዓትን ፣ መቻቻልን ፣መረዳዳትንና መከባበርን ወዘተ. በማዳበር ለወደፊቱ ማለትም በሥራ ዓለም በተለይም በቡድን ስራ ላይ የሚያስፈልጉ ችሎታቸውን በማዳበር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም በጋራ ሆኖ አስፈላጊ ዕርዳታዎችን ከመምህራቸው

ወይም ከሌላ አካል ወይም ቦታ ለማግኘት ለምሳሌ ቃለ-መጠይቅና ትምህርታዊ ጉብኝት ለማድረግ፣ወዘተ አስቸጋሪ አይሆንባቸውም፡፡

በአጠቃላይ የጥናት ቡድን ለማንኛውም ተማሪ የሚስማማ ላይሆን እንደሚችል ማወቅ እንደሚገባቸውና ይህም አስቸጋሪ ለሚሆንባቸው ተማሪዎች በራሳቸው መንገድና ስልት እንዲያጠኑም ጭምር ተመራማሪዎቹ ያስገነዝባሉ፡፡

## 2.3 ተማሪዎች ስኬታማ ሊሆኑ የሚችሉበት ተጨማሪ ነገሮች

ውጤታማነትን በተመለከተ ተማሪዎች ትክክለኛ የአጠናን ዘዴን ተጠቅመው ከጥናታቸውም ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ እንዲረዱ ከማድረግ ባሻገር ተማሪዎችን ለጉብዝና የሚያበቁ ተጨማሪ ሀሳቦችን ለንዘረዋል፡፡

www.harvaid west lake. Com/students/study skills/ እና ሊበን (1997፣38-42) ተማሪዎች ስኬታማ የሚሆኑበትን ብልሀቶች ሲያብራራ ሁሉም ተምሮ በፈተናው አስደሳች ውጤት እንዲያመጣ ይመኛል፡፡ ይህንን ምኞት ከሞላ ጎደል ለማሳካት በቅፅበት ተነስቶ ማጥናት መጀመር ሳይሆን ተማሪው በቅድሚያ መሠረታዊ የሆኑ የአስተሳሰብ ለውጦችን ማድረግና አንዳንድ ዘዴዎችን መጠቀም ይገባዋል፡፡ በመሆኑም ውጤታማ ለመሆን የሚከተሉትን ምክሮች አቅርቧል፤

- ዓቢይ የወደፊት ዓላማና ፅኑ ፍላጎት ይኑርህ፣
- ለጥናት አመቺ ቦታ፣ ጊዜና ሁኔታ ቀድመህ ለማዘጋጀት ሞክር፣
- የጥናት ጊዜ አጠቃቀም ዕቅድ ዝርዝር መርሀግብር ይኑርህ፣
- ንቁና ዝግጁ ሁን፣
- የራስህን የአጠናን ዘዴዎች ዕወቅ፣
- ጥናትን ልምድ አድርገው፣
- ኃይል ሰብስብ (ምግብ፣እንቅስቃሴ ፣ዕረፍትና እንቅልፍ)
- እርዳታ ለመጠየቅ አትፍራ፣ድክመትህ የት ላይ እንደሆነ ለማወቅ ሞክር ፣
- በራስህ መተማመንን አዳብር፣ቢዘገይም ጥረትህ እንደሚሳካ እመን ፣
- አቅድህ የጀመርከውን ነገር ለመጨረስ አታወላውል፡፡

ከላይ በቅደም ተከተል የተዘረዘሩት ሀሳቦች የሚያስገነዝቡን ፍሬሀሳብ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተገኝተው ፈተናቸውን ከማለፈ ባሻገር ላቅ ያለ ራዕይ ሊኖራቸው እንደሚገባና ከሁሉ በፊት ለትምህርታቸው ቅድሚያ የሚሰጡም ከሆነ ለጥናት የሚመች መደበኛ ሥፍራ፣ጊዜና ሁኔታ ማመቻቸት እንደሚገባቸው ነው፡፡ ጥሩ ዕቅድ በማዘጋጀት ዕቅዱንም ወደ ተግባር የሚለወጡት የሳምንትና ዕለታዊ ዝርዝር መርሀግብር በማውጣት ከክፍል የመቅረት ልምድ እንዳይኖራቸው፣ከትምህርት በፊት ስለሚማሩት ነገር ቀድመው ማየትና ከትምህርት በኋላም ወዲያው ፈጣን የሆነ ክለሳ ማድረግ ወሳኝ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች በፈተና መቃረቢያ ሰሞን ብቻ ቀንና ሌሊት ያለዕረፍት ለማጥናት ከመሞከር አስቀድመው ለጥናታቸው የተወሰኑ ሰዓታት መድበው የማጥናት ልምድ እንዲያዳብሩና በትምህርትም ሆነ በጥናትና በፈተና ወቅት አቅም በፈቀደ መጠን በቂና ተመጣጣኝ ምግብ መመገብ፣በቂ የዕረፍትና የእንቅልፍ ጊዜ እንዲያገኙ በማስገንዘብ አካልንና አእምሮን የሚያዳክሙና የሚጎዱ ነገሮችን ከመውሰድ መቆጠብ ይገባችዋል። እንዲሁም ተማሪዎች ሁልጊዜ ያልገባቸውን ነገር ከመጠየቅ ሳይቆጠቡ በፅናት መስራት አለባቸው። የሚሰሩት ነገር ሁሉ ሲጀምሯቸው ሊከብዷቸው እንደሚችሉና መሳሳትም እንደሚኖር አውቆ ከፈፀሟቸው ስህተት በመማር ስህተቱን ላለመድገም መምከርና የሚፈልጉትን ነገር እስኪያገኙ ድረስ ደጋግመው መሞከር እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ ነው።

## 2.4 ተማሪዎች ፈተናቸውን እንዴት መስራት ይኖርባቸዋል?

### 2.4.1 ለፈተና የሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች

www. Southwestern. Edu/academic/ እናwww Harvard west lake. Com /stidemts/ የሚለው ድረ-ገጽ እንደሚያስገነዝበን የፈተና ዝግጅት የሚጀመረው በመጀመሪያ የትምህርት ቀን ነው። የዓመቱን ወይም የክፍለ ዓመቱን መርሀ ትምህርት በጥንቃቄ በመመልከት የፈተና ሳምንቶችና ዕለታት መቼ እንደሆኑ፣ስንት ፈተናዎች እንዳሉና ፈተናዎቹ ከአጠቃላይ (100%) ስንት እጁን እንደሚይዙ በዝርዝር በዕቅድህ ማስታወሻ ላይ ማስፈር እንደሚገባን ነው።

ተማሪዎች በዕቅዳቸው ላይ የክለሳ ጊዜያቸውን እንዲያሰፍሩና ለፈተና ዝግጅት ክለሳ ወሳኝ እንደሆነ ያስገነዝባል። ክለሳ ሁል ጊዜ ከክፍል ትምህርት በኋላ ቢዘገይ በሀያ አራት ሰዓት ጊዜ ውስጥ መደረግ አለበት እንዲሁም በጥናትና በክለሳ ጊዜያት የሚያውጧቸው የተጨመቁና የተቋጩ ቁልፍ ቃላት ሀረጎችና ማስታወሻዎች በጥንቃቄ ከማስታወሻ ደብተሮቻቸው ጋር በማስቀመጥ ሊጠቀሙበት ይገባል።

ከዚህም በተጨማሪ ስለ ጥያቄዎቹ አቀራረብና አይነት ቀድመው መምህራቸውን መጠየቅ እንዳለባቸው፣ያለፉ የፈተና ጥያቄዎች ለማግኘት ቢሞክሩ ፣ ክለሳቸውን በተቻለ መጠን ከፈተናው ዕለት አንድና ሁለት ቀናት ቀደም ብለው ማጠናቀቅ እንደሚገባቸው አብራርቷል።

### 2.4.2 በፈተናው ዋዜማ

የስነልቦና ጥናት ተመራማሪዎች እንደሚመክሩት፣ ፈተናን በብቃት ለመስራት ከሚያግዙት እጅግ ጠቃሚ ስልቶች ውስጥ በፈተና ዋዜማ ወቅት ራስን ከማስጨነቅ መቆጠብ ነው። አቡሽ (1998፣ 76-180) ፣ ሲበን(1997፣ 193-196) እና ኑሪያና ተስፋዬ (1993፣ 52-62)

እንደ ፀሀፍቱ አገላለጽ ተማሪዎች ፈተና አንድ ቀን ሲቀረው መጨነቅ እንደማይገባቸውና ለዚህም የሚከተሉትን በተግባር ላይ እንዲያውሉ ይመክራሉ፤

- በፈተናው ዋዜማ ሌሊት ጥሩ እንቅልፍ ተኛ፣
- ከመተኛትህ በፊት ለሁለት ሰዓታት ማጥናትህን አቁም፣
- በዚህም ሰዓት ራስህን አዝናና፣
- ጧት ከአንድ ሰዓት በፊተ ቀደም ብለህ ተነስ፤

በማለት የመረጋጋት ስሜት እንዲፈጥሩ ያስገነዝባሉ። ስኬታማ ተማሪዎች ጥሩ ውጤት ሲያገኙ «እኔ ታታሪና ጎበዝ ተማሪ ነኝ። ብዙ ጥሬያለሁና ለዚህም ነው የተሳካልኝ» ሲሉ ካልተሳካላቸውና ጥሩ ውጤት ሳያገኙ ሲቀሩደግሞ «ፈተናው ከባድ ነበር፤እኔም በቂ ዝግጅት አላደረግሁም፤በዚህ ላይ ደግሞ በጥሩ ሁኔታ ያልተዘጋጀሁባቸው ጥያቄዎች መጠየቁ ያጋጣሚ ነገር ነው» ይላሉ። መውደቅን የሚፈሩ ተማሪዎች ደግሞ ውድቀት ሲያጋጥማቸው «ደደብ ነኝ፣ለትምህርቱ ተስጥዖ የለኝም» ሲሉ ውጤታማ ከሆኑ ግን «ፈተናው ቀላል ነበር፤እኔም እድለኛ በመሆኔ አለፍኩ» ይላሉ።

በአጠቃላይ ስኬታማ ተማሪዎችና ውድቀትን የሚፈሩ ተማሪዎች የሚለያዩበት ዋናው ነገር ስኬትና ውድቀታቸውን የሚያዩበትና የሚገልፁበት መንገድ ነው፤በመሆኑም ተማሪዎች ፀለምተኛ አስተሳሰብና አመለካከት እንዳይኖራቸው ይገባል። ምክንያቱም ይህን መሰል አስተሳብ ወደ ውድቀት የሚመሩ ሌሎች እንደ ፍርሀትና ተስፋ መቁረጥን የመሳሰሉ ተላውጦዎችን ያስከትላሉና ነው።

የሚፈሩና ፀለምተኛ አስተሳሰብ ያለባቸው ተማሪዎች የሚከተሉት ባህርያት ይታይባቸዋል፤(www. Csbsju .edu/acadamicadvising/እና lake. Com /students/ www. Harvard west

- በውስጣቸው ከራሳቸው ጋር የሚያደርጓቸው ንግግሮች በአብዛኛው ተስፋ አስቆራጭ አድካሚና ራስን ዝቅ የሚያደርጉ ናቸው።
- የሚታያቸው ውስጣዊ (የሀሳብ) ስዕሎችና «ፊልሞች» ብዙ ጊዜ «የፈሩት ነገር» ሲደርስ የሚያሳይ ነው።
- የማየቅዷቸው ነገሮች ከአቅማቸው ጋር የማይመጣጠኑ በጣም ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ ግቦች ይሆናሉ። ከፍተኛው ግብ ያልተሳካው «ከባድ ስለሆነ» የሚል ምክንያት ይሰጧቸዋል። ከአቅም በታች የሆነው ደግሞ ያለችግር ይጨረሳል።
- በፍላጎት ማጣት፣በፍርሀትና በተስፋ መቁረጥ ስሜት ይሰቃያሉ። ውድቀትን መካድ ወይም በሌላ (ለምሳሌ በህብረተሰቡ) ማሳበብ የመሳሰሉትን ባህሪያት ያሳያሉ።
- ተስማሚ ያልሆነ መፍትሄዎችን ወይም የመማሪያና የጥናት ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። አትኩሮታቸው በያዙት ተግባር ላይ ሳይሆን ወደ ሌላ ይዞራሉ።

- ዕውቀታቸውን የሚፈትን ነገር ይሸሻሉ። ራሳቸውን ለመፈታተንም ሆነ በሚያውቁት ሰው ወይም ጓደኛ ለመፈተን ይፈራሉ። ከፈተና ይቀራሉ፣ከሰው ይርቃሉ ወይም ይታመማሉ።
- በፈተና ወቅት የተደናገጡ፣በቀላሉ መልኩ የሚጠፉባቸው፣ብዙ ጊዜ በጥሩ ሁኔታ ያልተዘጋጁና በችሎታቸው ሊያገኙት ከሚችሉት በታች መጥፎ ውጤት የሚያገኙ ናቸው።

ይህም በመሆኑ እነዚህ ተማሪዎች ብዙ ጊዜ ያሉበትን ሁኔታ ለመቀየርና እጣ ፈንታቸውን ራሳቸው መለወጥ እንደማይችሉ አድርገው የሚያምኑ ናቸው።

## 2.4.3 በፈተናው ዕለትና በፈተና ወቅት

ተማሪዎች በፈተናው ዕለት በጧት (አንድ ሰዓት ቀድመው) ከእንቅልፋቸው መነሳት፣ጥሩና ቀለል ያለ ቁርስ መመገብ፣የክለሳ ማስታወሻቸውን አንዴ ገረፍ፣ገረፍ ማድረግና ለፈተናው የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች መያዝ ይገባቸዋል። አቡሽ(1998፣172-178) ፣ሲበን (1997: 196) እና ኑሪያና ተስፋዬ (1993፣ 52-62)

የዐሀፍቱ አባባል ተማሪዎች በፈተናው ዕለት በቂ ጊዜ እንዲያገኙ አርፍደው መነሳት እንደሌለባቸውና በቂና ተመጣጣኝ ሀይል እንዲያገኙ በተገቢው መንገድ ቁርሳቸውን መመገብ እንዳለባቸው፣ለማስታወስና ጥልቁን የአንጎል ክፍል ዝግጁ ለማድረግ በፈተናው አሰጣጥ ፕሮግራም መሰረት (በቅደም ተከተል) ለመከለስ መሞከርና በመጨረሻም ለፈተናው የሚያስፈልጉ ነገሮችን እንደ እርሳስ፣ እስክሪብቶ፣ላጲስ ወዘተ. የመሳሰሉት መያዝ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ። ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ባልተሟሉ ወይም ተግባራዊ ካልሆኑ ፍርሀትና ድንጋጤ ስሜቶችን በመፍጠር በፈተናው ላይ መረጋጋት እንዳይኖር የሚያደርጉ ናቸው። በመጨረሻም ተማሪዎቹ በፈተና አዳራሹ አካባቢ ቀድመው እንዲደርሱ፣ፈተናው ያን ያህል የአለም መጨረሻ እንዳልሆነ ማሰብና ቢወድቁም እንኳን ማሻሻል እንደሚችሉ አድርገው ራሳቸውን እንዲያጠነክሩ፣ በዚህ ወቅትም ለማጥናት እንዳይሞክሩና ራሳቸውን ዘና ለማድረግ ከፈተናው ውጭ ስለሌላ አስደሳች ነገር ማሰብ እንዳለባቸው ይመክራሉ።

ፈተናው ሲጀመር ሊያተኩሩባቸው የሚገቡ ነጥቦች የሚከተሉትን ይመስላሉ።

- ለፈተናው የተሰጠውን ሰዓት ማወቅ (ለመረዳተ መሞከር)፣
- መቀመጫቸው ምቹ መሆን አለመሆኑንና በቂ ብርሃን ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣
- የፈተናውን ትዕዛዝ (መመሪያ) በሚገባ አንብቦ መረዳትና የጥያቄው ወረቀት በትክክል መድረስ አለመድረሱን ማረጋገጥ፣
- ሁሉንም ጥያቄዎች አንዴ ገረፍ ገረፍ አድርገው ማንበብ፣
- ቀላል ጥያቄዎችን ምልክት በማድረግ በቅድሚያ መስራት፣
- ቀጥሎ ከባድ ጥያቄዎችን መስራት፣

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

ለዚህ ጥናት የተመረጠው የአጠናን ዘዴ ንጽጽራዊ የምርምር ሥልት ነው።

## 3.1 ተጠኝዎች

### 3.1.1 የዩኒቨርሲቲው አመራረጥ

የዩኒቨርሲቲው አመራረጥ ምክንያት ለጥናቱ ዓላማ ግብ መምታት አመቺና አስተማማኝ ይሆናል ተብሎ የተመረጠው የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት እንደሚታወቀው የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአማርኛን ቋንቋ በዋናነት ማስልጠን ከጀመረ ረጅም ጊዜ በመሆኑና ጥናቱም የሚያተኩርባቸውን ትምህርቶች ማለትም የስነጽሑፍ መሰረታዊያን፣ የአማርኛ ቋንቋ ቅኝትና የፎክሎር መግቢያን በዘመኑ የሚሰጡ መሆናቸውን አስቀድሞ ስለተረጋገጠ ነው።

### 3.1.2 የተማሪዎች ናሙና አወሳሰድ

ጥናቱ የሚመለከታቸው በ1999 ዓ.ም. በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ፋክሊቲ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ የሶስተኛ አመት የአማርኛ ቋንቋ ቅኝት፣ የስነጽሑፍ መሰረታዊያንና የፎክሎር መግቢያን የሚያጠኑ ተማሪዎችን ነው። የተጠኝዎች ቁጥርም 120 (አንድ መቶ ሃያ) ሲሆን ከእነዚህም መካከል 58 (ሃምሳ ስምንቱ) ወንዶች እና 62 (ስልሳ ሁለቱ) ሴቶች ተማሪዎች ናቸው።

ቀደም ሲል ለጥናቱ ታላሚ የነበሩት የማሪዎች ቁጥር ከላይ የተጠቀሰው ቢሆንም በአጋጣሚ ሆኖ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በዘመኑ የነበሩት እነዚሁ ብቻ በመሆናቸው ሁሉም እንዳሉ ተወስደዋል። ከዚህም በተጨማሪ ጾታን በማማከል በቁጥር 20 (ሃያ) የሚሆኑ ተማሪዎች ለቃለመጠይቅ ተመርጠዋል። እነዚህ ተማሪዎች የተመረጡትም በተራ እጣ ናሙና (Simple random sampling) ዘዴ ነው።

### 3.1.3 የትምህርቶቹ አመራረጥ

የትምህርቶቹ (Courses) አመራረጥ ምክንያት በተደጋጋሚ እንደተጠቀሰው የጥናቱ ትኩረት የተማሪዎችን ያጠናን ዘዴንና የውጤታቸውን ተዛምዶ መመርመር ነው። በመሆኑም የሚመረጡት የትምህርት አይነቶች በባህሪያቸው ጥናት የሚያስፈልጋቸው ሆነው መገኘት ይኖርባቸዋል። ስለዚህ ተማሪዎች በቂ ጊዜ ወስደውና አምቺውን የአጠናን ዘዴ በመከተል ከጥናታቸው ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ መከተል ስለሚኖርባቸው ነው። ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶችና ለጥናቱ አመቺነት ሲባልም በዩኒቨርሲቲው የአማርኛን ቋንቋ በዋናነት የሚያጠኑ የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች የሚያጠኗቸው ሶስት ትምህርቶች (Courses) ማለትም፣ የአማርኛ ቋንቋ ቅኝትን፣ የስነጽሑፍ መሰረታዊያንና የፎክሎር መግቢያን በመውሰድ ነው።

## 3.2 የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎች

### 3.2.1 የጽሑፍ መጠይቅ

የጥናቱን ዋነኛ አላማ መሰረት በማድረግ ያማርኛ ቋንቋ ቅኝትን የስነፅሑፍ መሰረታዊያንና የፎክሎር መግቢያን የሚያጠኑ ተማሪዎች የአጠናን ዘዴአቸውን በመመርመር ያጠናን ልምዳቸውንና እራሳቸውን ለፈተና የሚያዘጋጁበትን መንገድ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ለዚህም ሲባል ከተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው የጽሑፍ መጠይቅ ነው።

የጽሑፍ ጥያቄዎቹም በሁለት ምድብ የተከፈሉ ናቸው። በምድብ አንድ ስር የሰፈሩት ጥያቄዎች የተማሪዎችን የአጠናን ዘዴና የውጤታቸውን ተዛምዶ ለመረዳት እንዲቻሉ ሆነው የተዘጋጁ ናቸው። በምድብ ሁለት የተዘጋጁት ጥያቄዎች ደግሞ ተማሪዎች ለፈተና የሚይደርጉትን ዝግጅትና የፈተና አሰራር ልምዳቸውን ለመገንዘብ እንዲቻሉ ሆነው የተደራጁ ናቸው።

የጥያቄዎቹ አዘገጃጀትም አጫጭርና ግልጽነት ያላቸው በመሆናቸው ተጠኝዎች በቀላሉ ምላሽ እንዲሰጡ የሚያስችሉ ናቸው። የጽሑፍ መጠይቆቹ የተዘጋጁት በክለሳ ድርሳኑ ከተገኙ መረጃዎች አንጻር ሲሆን በምድብ አንድ ስር በጠቅላላው አስራ ሰባት (17) ጥያቄዎች ይገኛሉ። ከእነዚህም ውስጥ አስራ አራት (14) ያህሉ ምርጫ ሰጪ (ዝግ) ጥያቄዎቹ ሲሆኑ፣ ሶስት ጥያቄዎች ደግሞ ነጻ አስተያየት ለመስጠት እድል የሚሰጡ (ክፍት) ጥያቄዎች ናቸው። ምርጫ ሰጪ (ዝግ) ጥያቄዎቹ አራት የስምምነት ደረጃዎች ያላቸው ሲሆን ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ

የተቀመጡ ማለትም «በጣም እስማማለሁ» ፣ «እስማማለሁ»፣ «ለመወሰን እቸገራለሁ» እና «አልስማማም» የሚሉ ናቸው ። የመጠይቆቹ አስረጫጨትና አሞላልን በተመለከተ ተጠኝዎቹ በዩኒቨርሲቲው አዳራሽ ወስጥ በቂና ምቹ ሁኔታ በተፈጠረበት አጋጣሚ ከተቀመጡ በኋላ የጥናቱን አላማ በግልጽ በመረዳት ነው። በዚህም መሠረት ተማሪዎቹ በሙሉ ፍቃደኝነት ላይ በመመስረት ለጥያቄዎቹ ምላሽ በመስጠት ምላሹም ወዳያው ተሰብስቧል።

ሶስት /3/ አስተያየት የሚሹት ክፍት ጥያቄዎች ደግሞ ተማሪዎቹ ከምርጫ ሰጪ /ዝግ/ ጥያቄዎቹ ባሻገር የተለያዩ ሐሳብ ወይም አጠናን ዘዴ እንዳላቸው ለመረዳት ያስችል ዘንድ ታስበው የተዘጋጁ ናቸው። በመሆኑም ተጠኚዎች ሀሳባቸውን ለማስፈር የሚያስችሉ በቂ ክፍት ስፍራ ተሰጥቶአቸዋል።

### 3.2.2 ቃለ መጠይቅ

ከፁሁፉ መጠይቆች በተጨማሪነት የመምህሩን የማስተማር ዘዴ ለየትምህርት አይነቶቹ የተሰጡት የማስተማሪያ ሰአት (Credit hour) ከይዘቱ ጋር ያለውን ምጣኔና እንዲሁም የትምህርቱን አቀራረብ ለመገንዘብ እንዲቻል ወዘተ. አስቀድሞ ለመረዳት የሚያስችሉ ሆነው የተደራጁ ናቸው። በመሆኑም ለቃለመጠይቁ የተዘጋጁት ጥያቄዎች ብዛት 10 /አስር/ ናቸው ። የጥያቄዎቹም አደረጃጀት ግልፅነት ያላቸውና ለጥናቱ ጠቀሜታ ይሰጣሉ ተብለው የተገመቱ ናቸው። ለቃለ መጠይቁ የተመረጡት ተማሪዎችን ብዛት 20/ሀያ/ ናቸው አመራረጡም ፆታን ባመጣጠነ መልኩ 10/አስር/ ወንዶችና 10/አስር/ ሴቶች ተማሪችን በተራ የዕጣ ናሙና ( Simple random sampling) አመራረጥ ዘዴ ነው። የተመረጡት ተማሪዎችም በተረጋጋና በተሟላ ሁኔታ ምላሻቸውን ለመስጠትችለዋል።

### 3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ለጥናቱ ስኬታማነት ይበጃሉ ተብለው የተዘጋጁ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሁሉ በተጠያቂዎች መሟላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ በአጠቃላይ ቆጠራ በማካሄድ ሁሉም ተጠያቂዎች ምላሽ መስጠታቸው ተረጋግጧል። ቀጥሎም ተማሪዎቹ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ እንደተመሳሰሎውና ልዩነቱ በመወሰድ በወገን በወገኑ በማደራጀት ለቀማ ተካሂዶአል። በዚሁ መሰረት የተገኘው ውጤት በይፋ በመለየት በቁጥርና በመቶኛ ተሰልቷል። ነፃ አስተያየት የሚሹ ጥያቄዎች ተጠኚዎች የሰጡትን ምላሽ በሀሳብ የሚመሳሰሉት በአንድ ወገን የማይመሳሰሉትን ደግሞ በሌላ

ወገን በመልቀምና በማደራጀት ለጥናቱ የሚበጁት መረጃዎች በአግባቡ በመለየት ተወስደዋል፡፡

ምንም እንኳን ቁጥራቸውም በጣም ጥቂት የሆኑ ተማሪዎች ክፍት ቦታውን ሳይሞሉ ቢተውትም፣ ከጠቅላላው ተጠኚዎች ብዛት አንጻር ሲታይ የተሰጡት ምላሾች በቂ መረጃ ለማግኘት የሚያስችሉ በመሆናቸው ከአብዛኛዎቹ ተጠኚዎች የተገኘው ምላሽ ለጥናቱ ጠቀሜታ ሲውል ችሎዋል፡፡

በቃለመጠይቆች አማካኝነት የተገኙ ምላሾች ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሰጡትን ምላሽ በአይነትና በይዘታቸው ተደራጅተው ከተጠቀሙ በኃላ ለጥናቱ ጠቀሜታ ይውላሉ ተብለው የተገመቱት መረጃዎች በተፈላጊው ሁኔታ በመመለሳቸው በአስተማማኝነት ተወስደዋል፡፡

ተጠኚዎቹ በቃለመጠይቆቹ አማካኝነት የቀረቡላቸውን ጥያቄዎች ሲመልሱ ሶስቱም የትምህርት አይነቶች (Courses) ማለትም የአማርኛ ቋንቋ ቅኝት፣ የሰነጹሑፍ መሰረታዊያንና የፎክሎር መግቢያን መሠረት ባደረገ መልኩ ነው፡፡ ይህም ማለት ለእያንዳንዱ ጥያቄ ሶስት ሶስት ምላሾች ይጠበቅባቸዋል ማለት ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

በዚህ ክፍል ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑትንና ከተጠኝዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች መሠረት ያደረጉ የውጤት ትንተናና ማብራሪያዎች በቅደም ተከተል ተደራጅተው ቀርበዋል፡፡

### 4.1 የውጤት ትንተና

እንደሚታወቀው ጥናቱ ትኩረት አድርጎ የተነሳው የተማሪዎችን የጥናት ጊዜ ምርጫና የውጤታቸውን ተዛምዶ በንፅፅር መመርመር ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ለጥናቱ አመቺነት ሲባል በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሶስት የአማርኛን ቋንቋ የትምህርት ዘርፎች ማለትም «የአማርኛ ቋንቋ ቅኝትን» ፣ «የሥነጽሁፍ መሠታውያን» እና «የፎክሎር መግቢያ» የሚማሩትን ተማሪዎች በተጠኝነት በመምረጥ ነው፡፡ በመሆኑመ የተጠኝዎችን የጥናት ጊዜ ምርጫ ለመረዳት በሚያስችል መልኩ የጽሁፍ መጠይቅ ተዘጋጅቶ ቀርቦላቸው ምላሽ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ ተጠኝዎቹ የሰጡት ምላሽ ከተሰጧቸው አራት አማራጮች ውስጥ አንዱን በመምረጥ በመሆኑ በቀረቡላቸው ጥያቄዎች ዙሪያ በቂ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የተሰጡትንም ምላሾች እንደአመቺነቱ በጥንቃቄ ቆጠራ በማካሄድ ውጤቱ በቁጥርና በመቶኛ ተሰልቶ በቅደም ተከተል ቀርቧል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበላቸው ጥያቄ ተማሪዎቹ የየራሳቸው የጥናት ጊዜ ምርጫ እንዳላቸው ወይም እንደሌላቸው ለመረዳት የሚያስችል ነው፡፡ በዚሁ መሠረት የጥናት ተተኳሪ ከሆኑት 120 ተማሪዎች ውስጥ ብዛታቸው 90 የሚሆኑት ጥናታቸውን የሚያጠኑበት ጊዜ እንዳላቸውና 18 ያህሉ ደግሞ ከተሰጣቸው አማራጭ መልሶች ውስጥ «ለመወሰን እቸገራለሁ» የሚለውን የመለሱ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ቀሪዎቹ አስራ ሁለት ተማሪዎች ግን ለጥናታቸው የሚያውሉት የተለየ ጊዜ እንደሌላቸው አመልክተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከተገኘው አሀዝ የምንረዳው ከጠቅላላው ተጠኝዎች ውስጥ አብዛኞቹ ማለትም 75% የሚሆኑት የጥናት ጊዜ ምርጫ እንዳላቸው የሚያመለክት በመሆኑ ጥናቱ አስተማማኝ መሆኑን ከወዲሁ መገመት ተችሏል፡፡

በመቀጠልም የተማሪዎችን የጥናት ጊዜ ምርጫ ለማወቅ ተጠኝዎች በሰጡት ምላሽ በጽሁፍ መጠይቁ ላይ ቆጠራ ተካሂዶ የዚህም ስሌት በቁጥርና በመቶኛ(%) ስሌት ተመልክቷል፡፡ ይህም ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ አንድ፣ የተማሪዎች የጥናት ጊዜ ምርጫ በቁጥርና በመቶኛ ስሌት

| የጥናት ጊዜ ምርጫ | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት |
|---|---|---|
| ፈተና ከመድረሱ በፊት የሚያጠኑ | 77 | 64% |
| ፈተና ሲደርስ የሚያጠኑ | 39 | 32.5% |
| ለመወሰን እቸገራለሁ | 4 | 3.3% |

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው ከጠቅላላ ተጠኝዎች ፈተና ከመድረሱ በፊት የሚያጠኑት በቁጥር 77፣በመቶኛ ስሌት ደግሞ 64 ያህሉ መሆናቸውን እንገነዘባለን፡፡ ፈተና ሲደርስ የሚያጠኑት ደግሞ በቁጥር 39 በመቶኛ ስሌት ደግሞ 32.5% ያህሉ ናቸው፡፡ ከስሌቱ መረዳት እንደቻልነው ፈተና ከመድረሱ በፊት የሚያጠኑት በቁጥር የሚበልጡ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይህም የሚያመለክተን ምንም እንኳን የተማሪዎቹ የጥናት ጊዜ ምርጫ ቢለያይም አብዛኞቹ ሁለቱንም የአጠናን መንገድ እንደሚከተሉ ነው፡፡ ከጠቅላላ ተጠኝዎች የጊዜ ምርጫዎች የተካተቱት 116 ያህሉ ናቸው፡፡ ቀሪዎች 4 ያህሉ ደግሞ በጽሁፍ መጠይቁ ከተሰጣቸው ምርጫዎች አንዱ «ለመወሰን ያስቸግረኛል» የሚለውን የመለሱ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይህም የሚያመለክተን ጥናታቸውን ከሁለቱ የጊዜ ምርጣ ሌላ አማራጭ እንዳላቸው ወይም ደግሞ እንደአስፈላጊነቱ በሁለቱም የአጠናን ስልት የሚጠቀሙ ናቸው ለማለት ይቻል ይሆናል፡፡ ለዚህም አስተማማኝ ምላሽ ለማግኘት ክፍት ጥያቄ ተዘጋጅቶላቸው ሀሳባቸውን በአጭሩ እንዲሰነዝሩ ተደርጓል፡፡

በአማራጭ ከተሰጧቸው ምላሾች ውጭ ነፃ በሆነ መንገድ ሀሳባቸውን በአጭሩ እንዲገልፁ ዕድል መሰጠቱ ከአማራጮቹ ውጭ የተለየ የአጠናን ልምድ እንዳላቸው ፍንጭ እንዲሰጥ ታስቦ ነው፡፡ ይህንኑ ምላሻቸውን ደግሞ በየአንቀፁ ለማብራራት አመቺነት ስለሌለው ለግንዛቤ ያመች ዘንድ በተናጠል ወይም ለብቻው አሰባስቦ ማቅረቡ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ወደፊት በቅደም ተከተል ተቀናጅቶ ይቀርባል፡፡

ቀደም ሲል ተማሪዎቹ የጥናት ጊዜ ምርጫ እንዳላቸውና በአማራጭ ከተሰጣቸው የጥናት ጊዜ ውስጥ ደግሞ ፈተና ከመድረሱ በፊት የሚያጠኑት ተማሪዎች በቁጥር በርካታ እንደሆኑም ተረድተናል፤ይሁን እንጂ የጥናቱ ዋነኛ ዓላማ ተማሪዎቹ ይበጀናል ብለው የመረጡት የጥናት ጊዜ«ውጤታማ አድርጓቸዋል ወይስ አላደረጋቸውም?» የሚለው ዐቢይ ጥያቄ መመለስ ሲችል ነው፡፡ በዚህም መሠረት ፈተና ከመድረሱ በፊት አጠናለሁ ያሉትም ሆነ ፈተና ሲደርስ አጠናለሁ ብለው የመለሱት ውጤታቸውን በንጽጽር እንዲያመለክቱ የጽሁፍ መጠይቅ ቀርቦላቸው ምላሽ

እንዲሰጡ ዕድል ተሰጥቷቸዋል፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱን የጊዜ ምርጫ የመረጡትን ተማሪዎች በውጤታቸው አንጻር «ጠቅሞኛል» ወይም «አልጠቀመኝም» በማለት ያመለከቱትን ምላሽ በየአንፃራቸው በቆጠራ በመሰብሰብ የተገኘው የስሌት ውጤት በሚከተለው መንገድ በሠንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

**ሰንጠረዥ ሁለት፣ የተማሪዎች የጥናት ጊዜ ምርጫ ከውጤታቸው ጋር ሲነፃፀር**

| ተማሪዎች ጥናታቸውን የሚያከናውኑበት ጊዜ | የተጠኝዎች ጠቅላላ ብዛት | ውጤታማ ነኝ | | ውጤታማ አይደለሁም | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት |
| ፈተና ከመድረሱ በፊት | 77 | 72 | 93.5% | 5 | 6.4% |
| ፈተና ሲደርስ | 39 | 21 | 53.8% | 18 | 46% |

በሰንጠረዡ ከተመለከተው አሀዝ እንደምንረዳው ፈተና ከመድረሱ በፊት ማጥናት ከሚያዘወትሩ ተማሪዎች በቁጥር 72 የሆኑት የጥናት ጊዜ ምርጫዬ «ውጤታማ አድርጎኛል» ብለው ሲመልሱ 5 ያህሉ ግን ውጤታማ አላደረገኝም በማለት አመልክተዋል፡፡ እንዲሁም « ፈተና ሲደርስ አጠናለሁ» የሚሉት ተጠኝዎች ደግሞ በቁጥር 21 ያህሉ የጥናት ጊዜ ምርጫዬ ውጤታማ አድርጎኛል በማለት ሲመልሱ የቀሩት 18 ያህሉ ደግሞ «ውጤታማ አላደረገኝም» ሲሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህም የሚያመላክተን ተጠኝዎቹ ምንም እንካን የየራሳቸው የጥናት ጊዜ ምርጫ ቢኖራቸውም የተወሰኑት ከውጤታቸው ጋር በንፅፅር አለመመልከታቸውን ነው፡፡ ይሁን እንጂ የተገኘው አሀዝ እንደሚያመላክተን ደግሞ አብዛኞቹ ፈተና ከመድረሱ በፊት ማጥናትን የመረጡት የጥናት ጊዜ ምርጫቸው ውጤታማ እንዳደረጋቸው ነው፡፡ ፈተና ሲደርስ የሚያጠኑት ተጠኝዎች በውጤታማነታቸው አስቀድመው ከሚያጠኑት ጋር ሲነፃፀር ተጠቃሚ ያልሆኑት በልጠው ይገኛሉ፡፡

ለተማሪዎች ውጤታማ መሆን የጥናት ጊዜ መርጦ መጠቀም ብቻውን በቂ እንዳልሆነ ወይም ለውጤት እንደማያበቃ በተደጋጋሚ ለመጥቀስ ተሞክሯል፡፡ ይህም ማለት ከጥናት ጊዜ አወሳሰን ባሻገር ለውጤታማነት የሚያበቁ ክንውኖች እንዳሉና እነዚህንም ሳያዛንፉ በአግባቡ መጠቀሙ ተገቢነቱ የማያከራክር ነው፡፡ ተስማሚና ምቹ የሆኑ ሳይንሳዊ የአጠናን ዘዴዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተጠኝዎችን የአጠናን ዘዴዎች ማወቅ ይቻል ዘንድ በተለያዩ ምሁራን የተሰጡትን አስተያየቶች የአጠናን ዘዴዎች ማወቅ በጽሁፍ መጠይቃቸው ውስጥ በማካተት ምላሽ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

ምንም እንኳን የጥናቱ ዓላማ የተማሪዎችን የጥናት ጊዜ ምርጫና የውጤታቸውን ተዛምዶ መመርመር ቢሆንም ጥናታቸውን ከፈተና በፊትም ሆነ ፈተና ሲደርስ ቢያከናውኑ «ጊዜ» ለሚለው በቂና አስተማማኝ ሀሳብ ለመሰንዘር ይቻል ዘንድ

እንዲሰጡ ዕድል ተሰጥቷቸዋል፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱን የጊዜ ምርጫ የመረጡትን ተማሪዎች በውጤታቸው አንጻር «ጠቅሞኛል» ወይም «አልጠቀመኝም» በማለት ያመለከቱትን ምላሽ በየአንፃራቸው በቆጠራ በመሰብሰብ የተገኘው የስሌት ውጤት በሚከተለው መንገድ በሠንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

**ሰንጠረዥ ሁለት፣ የተማሪዎች የጥናት ጊዜ ምርጫ ከውጤታቸው ጋር ሲነፃፀር**

| ተማሪዎች ጥናታቸውን የሚያከናውኑበት ጊዜ | የተጠኝዎች ጠቅላላ ብዛት | ውጤታማ ነኝ | | ውጤታማ አይደለሁም | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት | በቁጥር | በመቶኛ ስሌት |
| ፈተና ከመድረሱ በፊት | 77 | 72 | 93.5% | 5 | 6.4% |
| ፈተና ሲደርስ | 39 | 21 | 53.8% | 18 | 46% |

በሰንጠረዥ ከተመለከተው አሀዝ እንደምንረዳው ፈተና ከመድረሱ በፊት ማጥናት ከሚያዘወትሩ ተማሪዎች በቁጥር 72 የሆኑት የጥናት ጊዜ ምርጫዬ «ውጤታማ አድርጎኛል» ብለው ሲመልሱ 5 ያህሉ ግን ውጤታማ አላደረገኝም በማለት አመልክተዋል፡፡ እንዲሁም « ፈተና ሲደርስ አጠናለሁ» የሚሉት ተጠኝዎች ደግሞ በቁጥር 21 ያህሉ የጥናት ጊዜ ምርጫዬ ውጤታማ አድርጎኛል በማለት ሲመልሱ የቀሩት 18 ያህሉ ደግሞ «ውጤታማ አላደረገኝም» ሲሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህም የሚያመላክተን ተጠኝዎቹ ምንም እንኳን የየራሳቸው የጥናት ጊዜ ምርጫ ቢኖራቸውም የተወሰኑት ከውጤታቸው ጋር በንፅፅር አለመመልከታቸውን ነው፡፡ ይሁን እንጂ የተገኘው አሀዝ እንደሚያመላክተን ደግሞ አብዛኞቹ ፈተና ከመድረሱ በፊት ማጥናትን የመረጡት የጥናት ጊዜ ምርጫቸው ውጤታማ እንዳደረጋቸው ነው፡፡ ፈተና ሲደርስ የሚያጠኑት ተጠኝዎች በውጤታማነታቸው አስቀድመው ከሚያጠኑት ጋር ሲነፃፀር ተጠቃሚ ያልሆኑት በልጠው ይገኛሉ፡፡

ለተማሪዎች ውጤታማ መሆን የጥናት ጊዜ መርጦ መጠቀም ብቻውን በቂ እንዳልሆነ ወይም ለውጤት እንደማያበቃ በተደጋጋሚ ለመጥቀስ ተሞክሯል፡፡ ይህም ማለት ከጥናት ጊዜ አወሳሰን ባሻገር ለውጤታማነት የሚያበቁ ክንውኖች እንዳሉና እነዚህንም ሳያዛንፉ በአግባቡ መጠቀሙ ተገቢነቱ የማያከራክር ነው፡፡ ተስማሚና ምቹ የሆኑ ሳይንሳዊ የአጠናን ዘዴዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተጠኝዎችን የአጠናን ዘዴዎች ማወቅ ይቻል ዘንድ በተለያዩ ምሁራን የተሰጡትን አስተያየቶች የአጠናን ዘዴዎች ማወቅ በጽሁፍ መጠይቃቸው ውስጥ በማካተት ምላሽ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

ምንም እንኳን የጥናቱ ዓላማ የተማሪዎችን የጥናት ጊዜ ምርጫና የውጤታቸውን ተዛምዶ መመርመር ቢሆንም ጥናታቸውን ከፈተና በፊትም ሆነ ፈተና ሲደርስ ቢያከናውኑ «ጊዜ» ለሚለው በቂና አስተማማኝ ሀሳብ ለመሰንዘር ይቻል ዘንድ

ከአጠናን ጊዜና ቦታ አንፃር የተጠኝዎችን ልምድ ማወቁ ለጥናቱ ስኬታማነት እገዛ እንደሚያደርግ አስቀድሞ በመገመት ነው:: ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ ሳይንሳዊና ተማሪዎችን ለስኬት ያበቃሉ ተብሎ የተሰነዘሩት እሳቤዎች በተማሪዎች ዘንድ መለመድ አለመለመዳቸው በራሱ ለጥናት ጊዜ ምርጫቸውና ብሎም በውጤታቸው ላይ የጎላ ተፅዕኖ እንዳለው ለመገንዘብ ይቻላልና ነው::

በመሆኑም ተጠኝዎች በቀረቡላቸው ጥያቄዎች ላይ ምላሽ ይሰጡ ዘንድ አራት ያህል አማራጮች ተሰጥቶአቸዋል:: የተማሪዎቹ ምላሾች በየፈርጁ ቆጠራ ሲካሄድ ለአስራር ያመች ዘንድ «በጣመ እስማማለሁ» እና «እስማማለሁ» ብለው የመለሱትን አንድ ላይ በመቁጠር «ለመወሰን ያስቸግረኛል» እና «አልስማማም» ብለው የመለሱትን ለየብቻ በመቁጠር የተጠኝዎችን ምላሽ በየታ በመለየት እደሚከተለወ በሰንጠረዥ መልክ ለማቅረብ ተሞክሯል::

ሰንጠረዥ ሶስት፣ የተማሪዎች የአጠናን ዘዴ ምላሽ በቁጥርና በመቶኛ ስሌት::

| የጥናት ዘዴዎች | በጣም እስማማለሁ (እስማማለሁ) | | | | ለመወሰን እቸገራለሁ | | | | አልስማማም | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | % | ወ | ሴ | ድ | % | ወ | ሴ | ድ | % |
| የግል የጥናት ፕሮግራም አለኝ | 35 | 46 | 81 | 67.5 | 14 | 15 | 29 | 24- | 4 | 6 | 10 | 8.3 |
| የጥናት ፕሮግራሜን በአግባቡ እጠቀማለሁ | 27 | 39 | 66 | 55 | 17 | 20 | 37 | 30.8 | 8 | 9 | 17 | 16 |
| አስቀድሜ ያጠናሁትን እከልሳለሁ | 39 | 49 | 88 | 73.3 | 9 | 10 | 19 | 15.8 | 7 | 6 | 13 | 10.8 |
| የማጠቀሻ መፃህፍትንና አስቀድሞ የተሰጡ ፈተናዎችን እመለከታለሁ:: | 27 | 38 | 65 | 62.5 | 14 | 16 | 30 | 25 | 13 | 12 | 25 | 20.8 |
| የማጠናው ጧት ጧት ነው | 7 | 14 | 21 | 17.5 | 18 | 23 | 41 | 34 | 28 | 30 | 58 | 48.3 |
| የተማርኩትን ከክፍሉ ጊዜው በኋላ እከልሳለሁ | 18 | 24 | 42 | 35 | 19 | 25 | 44 | 36.6 | 18 | 16 | 44 | 36.6 |
| ከጓደኞቼ ጋር በቡድን አጠናለሁ:: | 31 | 38 | 69 | 57.58 | 8 | 18 | 26 | 21.6 | 12 | 13 | 25 | 20.8 |

ከላይ ያለው ሰንጠረዥ እንደሚያመለክተን ተጠኝዎች ከጥናታቸው ተጠቃሚ ለመሆን የአጭርና የረጅም ጊዜ ፕሮግራም ማዘጋጀት አለማዘጋጀታቸውን ተጠይቀው ከጠቅላላ ተጠኝዎች ውስጥ በቁጥር 81 ያህል የሚሆኑት ለጥናታቸው ብለው ያዘጋጁት ዕቅድ እንዳላቸው ሲያመለክቱ 29ኙ ደግሞ «አልስማማም» የሚለውን በመመለሳቸው ጭራሽ ለጥናታቸው ፕሮግራም እንደሌላቸው አመልክተዋል:: ከላይ ከተሰጠው

አህዝየምንገነዘበው ከተጠኝዎቹ አብዛኞቹ ማለትም ከጠቅላላ 67.5% የሚሆኑት ጥናታቸውን በፕሮግራም እንደሚያከናውኑ መረዳት ይቻላል።

የጥናት ፕሮግራም ማውጣትም ብቻውን ውጤታማ አያደርግም የወጣውን ፕሮግራም ሳያዛቡና ሳያዛንፉ ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ነው። በመሆኑም ያዘጋጁትን የጥናት ዕቅድ ከመተግበር አንፃር ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ በቁጥር 66 ወይም ከጠቅላላ ተጠኝዎች 55% የሚሆኑት በአግባቡ እንደሚጠቀሙ አመልክተዋል።

ሳይንሳዊ የአጠናን ዘዴዎች ናቸው ተብለው ከተገመቱት መካከል ተማሪዎች አስቀድመው ያጠኑትን በክለሳ መልክ ደግሞ መመልከትና እንዲሁም በየዕለቱ የተማሩትን ሳይዘገዩ ወይም ከክፍለ-ጊዜው በኋላ መመልከቱ ከጥናታቸው ተጠቃሚ እንደሚያደርጓቸው በተደጋጋሚ ይመከራሉ። በዚህ ዙሪያ የተማሪዎቹን የአጠናን ዘዴ ለመረዳት በቀረቡላቸው ሁለት ጥያቄዎች ምላሻቸውን ሰንዝረዋል። በዚሁ መሠረት ከጠቅላላ ተጠኝዎች ውስጥ በቁጥር 88 የሚሆኑት አስቀድመው ያጠኑትን እንደገና በክለሳ መልክ መመልከት እንደሚችሉ፤ 19 ተጠኝዎች ደግሞ «ለመወሰን እቸገራለሁ» ብለዋል። ቀሪዎቹ 13 ተማሪዎች «አልስማማም» በማለታቸው «ክለሳን» እንደማይጠቀሙ ያመለክታል። ለተጠኝዎቹ ከቀረቡላቸው የመልስ አማራጮች መካከል «ለመወሰን እቸገራለሁ» ብለው ምላሽ የሰጡትን ትክክለኛ ምክንያት መረዳት ያስቸግራል። ሆኖም ለዚሁ እንደመፍትሄ ያገለግላል ተብሎ አስቀድሞ የተገመተውን ክፍት ጥያቄ በማዘጋጀት የተለየ የአጠናን ዘዴ እንዳላቸው አጭርና ግልጽ የሆነ አስተያየት በጽሁፍ እንዲያሰፍሩ ዕድል ተሰጥቶአቸዋል። ይህንኑ አስተያየት በሚቀጥሉት ገፆች ላይ የሀሳቦቻቸውን ጭምቅ በቅደምተከተል ተደራጅተው ይገኛሉ።

ተማሪዎችን ውጤታማ የሚያደርጉ ቀደም ሲል የጠቀስናቸው መንገዶች ብቻ አይደሉም። በክፍል ውስጥ የተማሩትን ብቻ ማጥናት ለውጤት አያበቃም። ክፍል ውስጥ የተማሩትን ትምህርት ሊያጠናክሩ የሚችሉና ስለሚያጠኑት ትምህርት (course) በቂና አስተማማኝ ዕውቀትና ግንዛቤ ይኖራቸው ዘንድ ይህንኑ ሊያጠናክሩ የሚችሉና በትምህርቱ ዙሪያ በተለያዩ ፀሀፍት የተፃፉ የማጣቀሻ መጻሕፍትን በተጨማሪነት መጠቀሙ ጥናታቸውን ውጤታማ ያደርግዋል። ይህንኑ ልምዳቸውን ለመረዳት ያስችል ዘንድ ለቀረበላቸው የጽሁፍ ጥያቄ ምላሽ መረዳት እንደተቻለው ከጠቅላላ ተጠኝዎች መካከል በቁጥር 65 የሚሆኑትና 54% ያህሉ የማጣቀሻ መፃፍትን እንደሚጠቀሙ ሲያመለክቱ፤ 30 ያህሉ ወይም ደግሞ«ለመወሰን እቸገራለሁ» የሚለውን አማራጭ በመመለሳቸው ለሚያጠኑት ትምህርት(course) ምንም አይነት የማጣቀሻ መጽሐፍት እንደማይጠቀሙ አመልክተዋል። ይሁን እንጂ አብዛኞቹ ተጠቃሚ መሆናቸውን ለመረዳት አያዳግትም።

ከጥናት ተጠቃሚ መሆን የሚቻልበት ሌላው መንገድ ደግሞ ተማሪዎች ጥናታቸወን መቼ ማጥናት ይኖርባቸዋል? የሚለው ጥያቄ በአግባቡ መመለስ ሲኖርበት ነው። በርካታ ፀሀፍት ከጥናት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችለወ ጊዜ ጧት ጧት ለተወሰነ ጊዜ ማጥናት መሆኑን ያስገነዝባሉ። በዚህ ዙሪያም የተማሪዎችን

የጥናት ጊዜ ለመረዳት በቀረበላቸው ጥያቄ መሠረት ከጠቅላላ ተጠኝዎች መካከል በቁጥር 21 የሚሆኑት ብቻ ጥናታቸውን ጧት ጧት እንደሚያከናውኑ ለመረዳት ሲቻል፣41 ያህሉ ደግሞ የጥናታቸውን ወቅት በትክክል ለማወቅ ወይም ለመወሰን ተቸግረዋል:: ቀሪዎቹ 58 ሚሆኑት ደግሞ ጧት ጧት ማጥናትን የማይመርጡ ሆነው ተገኝተዋል:: ይህም አሀዝ የሚያመለክተን አብዛኞቹ ተጠኝዎች መቼ እንደሚያጠኑ በቂ ግንዛቤ የሌላቸው ይመስላል::

ጥናትን በቡድን ማከናወን በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ይመከራል:: በዚህ የአጠናን ልምድ ዙሪያ የተጠኝዎችን ልምድ ለመረዳት በተደረገው ጥረት የጥናቱ ተተኳሪ ከሆኑት ተማሪዎች ውስጥ በቁጥር 69 የሚሆኑት ጥናታቸውን በቡድን እንደሚያከናወኑ ሲገልፁ፣26ቱ ደግሞ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ሲቸገሩ ወይም ለመወሰን ሳይችሉ ቀርተዋል:: ቀሪዎቹ 25 ተጠኝዎች ደግሞ በቡድን ማጥናትን እንደማይስማሙበት በግልጽ አመልክተዋል:: ይሁን እንጂ አብዛኞቹ ተማሪዎች ማለትም 57.5% የሚሆኑት በቡድን ማጥናት ውጤታማ ማድረጉን በመረዳት ሊጠቀሙበት እንደቻሉ ከሰጡት መረጃ መረዳት ይቻላል::

በአጠቃላይ ምሁራን ሳይንሳዊ የአጠናን ዘዴዎች ናቸው ብለው ያስፈሯቸውን ተገቢና ትክክለኛ የአጠናን መንገዶች ተከትለው ጥናታቸውን የማያከናውኑት ተማሪዎች አብዛኞቹ አስቀድመው በመረዳትም ሆነ በልምድ ተጠቃሚ እንደሆኑ መረጃው ያመለክታል:: ነገር ግን ፀሀፍቱ ከስነዘሯቸው መንገዶች «ጧት ጧት » ማጥናትን እንደልምድ ወይም ጠቃሚነቱን የተረዱት ጥቂት ወይም 17.5% ብቻ በመሆናቸው አአስተያየቱ ያፈነገጠ ሆነው ተገኝተዋል::

የተማሪዎችን የጥናት ጊዜ ምርጫና ዘዴ አስመልክቶ በጽሁፍ መጠይቁ ላይ ምርጫ ከቀረቡላቸው ጥያቄዎች በተጨማሪ ሶስት ክፍት ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋ በነዚሁ ጥያቄዎች ፊት ለፊት ሀሳባቸውን በአጭሩ እንዲያሰፍሩ ተደርጓል:: በዚሁ መሠረት ለጥያቄዎቹ የሰጡትን ምላሽ በተናጠል በመመልከተና ተመሳስሎ ያላቸውን በአንድ ላይ በማደራጀት እንደሚከተው ቀርበዋል::

1ኛ ውጤታማ ለመሆን እንዴትና መቼ ማጥናት ይኖርብሃል (ይኖርብሻል) ለሚለው ጥያቄ በአጭሩ አብራራ /አብራሪ/::

ለዚህ ጥያቄ ከጠቅላላ ተጠኝዎች ቁጥራቸው 58 የሆኑት ተማሪዎች ጥናታቸውን ፕሮግራም በማውጣትና ትምህርቱ ሳይጠራቀም ከስር ስሩ በማንበብ ውጤታማ መሆን ይቻላልና ገና ትምህርቱ እንደተጀመረ ጊዜ ሳይሰጡ ማንበብ ተገቢ መሆኑን አመልክተዋል::: ከዚሁ ሀሳባቸው በተጨማሪነት የሰጡት አስተያየት ቢኖር፣ትምህርቱ እየጨመረ በመጣ ቁጥር ከመብዛቱ የተነሳ አስጨናቂና አድካሚ በመሆኑ ትምህርቱ ከተጀመረበት ዕለት አንስቶ ሳያሰልሱ ማጥናትና መዘጋጀት እንደሚኖርባቸው ገልፀዋል::

የጥናት ጊዜያቸውን በተመለከተ ደግሞ ምንም እንኳን የተወሰኑት ተማሪዎች ወቅቱን በግልጽ ማስፈር ባይችሉም ምላሽ የሰጡትን ተጠኝዎች ማለትም ቁጥራቸው

38 ያህል ወይም 31.6% ሌሊት ሌሊትና ጧት ጧት ማጥናት ውጤታማ እንዳደረጋቸው ሲያብራሩ፣ እንዲያውም የሚያጠኑበትን ጊዜ ወስነው ከሌሊቱ 9 ሰዓት እስከ 12 ሰዓት በማለት ያመለከቱም አሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በጣም የተወሰኑት ተማሪዎች ደግሞ ለሁሉም ትምህርት እኩል ዋጋ በመስጠትና ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ (ጊዜ ሳይመርጡ) ዘወትር ማጥናት እንዳለባቸው ሲመልሱ፣ ቁጥራቸው ከአስር የማይበልጡ ተማሪዎች ደግሞ ጥናታቸውን በቡድን ወይም ከጓደኞቻቸው ጋር በማጥናት ውጤታማ እንደሆኑ አመልክተዋል፡፡ በሌላ በኩል ቁጥራቸው 26 የሚሆኑት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተማሩትን ከክፍለጊዜው በኋላ እንደሚያጠኑና ያልገባቸውን ነገር ደግሞ ጠይቆ መረዳት እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡

በሚማሩት ትምህርት (course) ማለትም በአማርኛ ቋንቋ ቅኝት፣ በስነ-ጽሁፍ መሰረታውያንና ፎክሎር መግቢያ ዙሪያ የበለጠ ዕውቀት ለማግኘት የማጣቀሻ መፃህፍትን እንደሚጠቀሙ የገለፁት ከ15 የማይበልጡ ተማሪዎች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በመጨረሻም በጣም የተወሰኑ ተማሪዎች ጥናታቸውን ባመቻቸው ጊዜ ሁሉ እንደሚያጠኑና በክፍል ውስጥ መምህሩ ሲያስተምር በጥሞና ከመከታተል ጀምሮ ከስር ከስሩ በማጥናት ፈተና ሲቃረብ አስቀድመው ያጠኑትን በክለሳ መልክ እንደሚመለከቱት አብራርተዋል፡፡

ከላይ የሰፈሩትን ምላሾች አጠቃለን ስንመለከታቸው፣ ተጠኚዎቹ ለቀረበላቸው ክፍት ጥያቄ የሰጡት አስተያየት በጽሁፍ መጠይቁ ላይ በአማራጭ ከተሰጣቸው አማራጮች ያልወጡ ናቸው፡፡ ወጣ ያሉት ምላሾች ጥናታቸው እንደትምህርቱ ዓይነት ሊወሰን መቻሉ፣ ቤተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ማጥናታቸውና ማታ ማታ ቤተመፃህፍት አጠናለሁ የሚሉት ናቸው፡፡

2ኛ የመረጥከውን (ሽውን) የጥናት ጊዜ እንድትወስን (ኚ) ያደረገህ (ሽ) ሌላ አካል አለ? ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የማከተለውን ይመስላል፡፡

ለዚህ ጥያቄ ከጠቅላላ ተጠኚዎች ቁጥራቸው 87 የሚሆኑት «የለም» የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከሰጡት መልስ መረዳት የምንችለው በየተኛውም ደረጃና አጋጣሚ ሁሉ ተማሪዎች ትምህርታቸውን መቼና እንዴት ማጥናት እንዳለባቸው የሚገልፅላቸው አካል አለመኖሩን ነው፡፡ ቀሪዎቹ ተማሪዎች ማለትም«አዎ» የሚለውን ምላሽ ሰጥተው የመከሩቸው አካል ደግሞ አንዳንዶቹ ቀደም ሲል ከነበሩት ተማሪዎች በመስማትና ጥቂቶቹ ደግሞ ልምዱን ከተማሩ ወንድሞቻቸው ወይም ቤተሰቦቻቸው እንደተመከሩ ገልፀዋል፡፡ ከላይ የተሰጡት ምላሾች በዋናነት ሲወሰዱ በተጨማሪነት አስተያየት የሰጡ ተማሪዎችም አጋጥመዋል፡፡ እነዚህም ምላሳች «የራሴ ምርጫ ነው» የሚወው ይበዛል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተሰጠወ አሀዝ የሚያስገነዝበን አብዛኞቹ ተማሪዎች ጥናታቸወን የሚያከናውኑት በልምድ እንጂ ሳይንሳዊ በሆነ የአጠናን ዘዴዎች ላይ ተመስርተው እንደማያጠኑ መረዳት ይቻላል፡፡ በጣም ጥቂት የሆኑት እንኳን «ምክር

ተሰጥቶናል » ያሉት በመምህሩን ሳይሆን በሌሎች አካሎች መመከራቸወን መመልከት ይቻላል፡፡

3ኛ ተማሪዎች ውጤታማ ለመሆን ትምህርታቸውን እንዴት ማጥናት አለባቸው ትላለህ (ትያለሽ?)፡፡ ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ቀደም ሲል በቁጥር አንድ ጥያቄ ላይ እደተጠቀሰው ተጠኛዎቹ ለዚህ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ በምርጫ ጥያቄው ላይ ከተሰጡት አማራጮች የተለዩ ሆነው አልተገኘም፡፡ ይህም ማለት አብዛኛው ተማሪዎች ጥናታቸውን ፈተና ከመድረሱ በፊትና አስቀድመው ማጥናት እንዳለባቸው መልሰዋል፡፡ የጥቂው መንፈስ ግን ቀዳም ሲል በአማራጭ ከተሰጣቸው የአጠናን ዘዴዎቻ የተለየ መንገድ እንዳላቸው ለመረዳት ይቻል ዘንድ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ የሰጡት ምላሽ ግን "ከፈተና በፊት" የሚል ነው፡፡ ጥያቄውን በውል የተገነዘቡት ጥቂት ተማሪዎች ግን የተለየ የአጠናን ዘዴያቸውን አመልክተዋል፡፡ የእነዚህምተማሪዋች ምላሽ፡-

- ጥናቴን የምማረው የትምህርት አይነት ይወስነዋል፣
- በክፍል የተማርኩትን ባገኘሁት አጋጣሚ አጥንቼ ባልገባኝ ተጨማሪ ማጣቀሻ መፀሀፍትን እጠቀማለሁ፣
- ለትምህርቱ በተሰጠው ክፍለጊዜ (Credit HourS} መጠን አጠናለሁ፣
- በቂ እንቅልፍና ዕረፍት ካገኘሁ በኋላ ዘወትር ፀጥታ ባለበት ቦታ አጠናለሁ፣
- የትምህርቱን አጠቃላይ ይዘት አስቀድሜ ለማወቅ ጥረት በማድረግ ወደፊት የምንማረውን ቀድሜ ለማንበብ እሞክራለሁ፣
- ስለምማረው ትምህርት አጠቃላይ ባህሪና ስለ መምህሩ አቀራረብ እና ስለሚያወጣው ፈተናም አስቀድሜ ሀሳብ (Information) ለማሰባሰብ በዚያ መሰረት እራሴን አዘጋጃለሁ፣ እና
- በሳምንት የተማርኩትን ቅዳሜና እሁድ አንድ ላይ አጠናለሁ፡፡ የሚሉት ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተሰጡት ምላሾች የምንረዳው ተማሪዎቹ የየራሳቸው የአጠናን ልምድ እንዳላቸውና እነዚህም የጥናት ዘዴዎች በአብዛኛው በምሁራንም የሚመከሩ የአጠናን ስልቶች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ተጠኝዎቹ በተሰጣቸው ክፍት ጥያቄዎች ላይ የሰጡት ወይም የሰነዘሩት አስተያየት በምርጫ ከተሰጣቸው የአጠናን ዘዴና የጊዜ አጠቃቀም ብዙም ያልራቁ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

በተደጋጋሚ እንደተገለፀው የጥናቱ ዋነኛ ዓላማ የተማሪዎችን የአጠናን ዘዴና ውጤታቸውን ተዛምዶ በንፅፅር መመርመር ቢሆንም ተማሪዎች ስለፈተና ያላቸው አመለካከትና አሰራርም ከሌሎች ተጎዳኝ ሁሉ በእጅጉ ከርዕሱ ጋር የተቆራኘ በመሆኑ

ይህንኑ የተማሪዎች አመለካከት ለመረዳት ምሁራን ስለፈተና ባህሪና አሠራር ከሰጡት አስያየት ወይም እሳቤ አንፃር የተዘጋጁ የፁሁፍ መጠይቆች ቀርበውላቸዋል፡፡ በመሆኑም ለጥያቄዎቹ የሰጡት ምላሾች ለጥናቱ ካላቸው ጠቀሜታ አንፃር ተደራጅተው መቅረብ ስላለባቸው በሚከተለው መንገድ በሰንጠረዥ ቀርበዋል

<u>ሰንጠረዥ አራት</u>፡- ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ቅኝት፣በስነ-ፁሑፍ መሰረታዊያንና ፋክሎር መግቢያ ላይ ስለፈተና አዘገጃጀትና አቀራረብ ያላቸውን ግንዛቤ የሚያመለክት

| የጥያቄ ዓይነት | በጣም እስማማለሁ | | | እስማማለሁ | | | ለመወሰን እቸገራለሁ | | | አልስማማም | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| ፈተና ሲቃረብ እጨነቃለሁ | 7 | 9 | 16 | 14 | 20 | 34 | 11 | 12 | 23 | 27 | 20 | 47 |
| ጥያቄዎችን አስቀድሜ እተነብያለሁ | 20 | 11 | 31 | 21 | 29 | 50 | 11 | 16 | 27 | 5 | 7 | 12 |
| ፈተናዬን የምሰራው ተረጋግቼና በራሴ በመተማመን ነው | 39 | 40 | 79 | 13 | 16 | 29 | 3 | 4 | 7 | 2 | 3 | 5 |
| መረጋጋቴና በራስ መተማመኔ ውጤታማ አድራጎኛል | 50 | 54 | 10 4 | 3 | 4 | 7 | 4 | 2 | 6 | 1 | 2 | 3 |
| በፈተና ዋዜማእራሴንዘና አደርጋለሁ | 20 | 27 | 47 | 16 | 13 | 29 | 13 | 15 | 28 | 8 | 8 | 16 |
| መመሪያዎችና የጥያቄዎች ብዛትበቅድሚያ አጤናለሁ | 35 | 38 | 73 | 15 | 21 | 36 | 3 | 4 | 7 | 2 | 2 | 4 |
| ለፈተናው በተሰጠው ሰአት በአግባቡ እጠቀማለሁ | 24 | 30 | 54 | 24 | 24 | 48 | 8 | 7 | 15 | 1 | 2 | 3 |
| ልመልሰው የማልችለው ጥያቄ ሲገጥመኝ እደነግጣለሁ | 14 | 20 | 34 | 6 | 15 | 21 | 6 | 16 | 22 | 30 | 13 | 43 |
| የሚቀሉኝን ጥያቄዎች በቅድሚያ እሰራለሁ | 34 | 41 | 75 | 12 | 13 | 25 | 3 | 2 | 5 | 7 | 8 | 15 |
| ፈተና በተቃረበ ቁጥር ጊዜዬን በአግባቡ እጠቀማለሁ | 40 | 42 | 82 | 13 | 15 | 28 | 4 | 4 | 8 | 1 | 1 | 2 |

ከላይ በሰንጠረዡ የተመለከተው አሀዝ የሚያመለክተን ተማሪዎች ስለፈተና ያላቸውን የአሰራር ልምድን ለማወቅ የሚያስችለን ነው፡፡ በመሆኑም በፈተና ወቅት መጨነቅ አለመጨነቃቸው የሚያመለክተን ከጠቅላላ ተጠኝዎች ብዛታቸው 50 የሚሆኑት ወይም 41.6% የሚሆኑት መጨነቃቸውን ሲያመለክት ቁጥራቸው 47 የሚሆኑና 39% ደግሞ ጭራሽ አለመጨነቃቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ እንዲሁም 81 ያህሉ ወይም 67.5% የሚጠየቁትን ጥያቄ አስቀድሞ ሊተነብዩ የሚችሉ ናቸው፡፡ በፈተና ወቅት እራስን የማረጋጋት እና በራስ በመተማመን የሚሰሩት 108 ወይም ከጠቅላላ ተጠኝዎች 90% ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በዚህም ውጤታማ መሆናቸውን መረጃ ያመለክታል፡፡

በፈተና ዋዜማ እራሳቸውን የማረጋጋት ልምድ ያላቸው ተማሪዎች በቁጥር 76 ወይም 63.3% መሆናቸውን ለመረዳት ችለናል፡፡ ተማሪዎች ፈተናቸውን መስራት ወይም መመለስ ከመጀመራቸው በፊት በቅድሚያ መመሪያዎችንና የጥያቄዎችን ብዛት መመልከትን ልምድ ያደረጉ 190 ያህሉ ወይም 90.8% ናቸው፡፡ ከዚሁ ጥያቄ ተነጥሎ ሲታይ የማይገባቸውን ጥያቄ ማለትም ለጠቅላላ ፈተናው የተሰጣቸውን ሰአት በመቆጣጠር ሊጠቀሙበት የሚችሉት ደግሞ 102 ያህሉ ወይም 85% ሆነዋል፡፡

በፈተና ወቅት ድንገት ሊመልሱት የማይችሉት ጥያቄዎች ሲገጥማቸው የሚጨነቁበትና የሚደነግጡበት 55 ያህሉ ወይም ከጠቅላላ ተጠኝዎች ከፊሎቹ መሆናቸውን ለመረዳት ሲቻል ፣ በመሆኑም ከተሰጧቸው ወይም ከቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሚቀሏቸውን ሊመልሱት የሚችሉትን ብቻ መርጠው የመስራት ልምድ ያላቸው ተማሪዎችስ 100 ያህሉ ወይም 38.3% ናቸው፡፡ በመጨረሻም ፈታና እየተቃረበ በመጣ ቁጥር ጊዜያቸውን በአግባቡ ሊጠቀሙበት የሚችሉት 110 ያህሉ ወይም 91.6% መሆናቸውን ከላይ የተመለከትነው መረጃ ያመለክታል፡፡

ባጠቃላይ ከላይ በዝርዝር በየታ ለይቶ የሚያመለክተን መረጃ በጉዳዩ ዙርያ የተለያዩ ምሁራን እንደሚያስፈልግ ካስቀመጡት እሳቤ አንፃር የቀረበላቸውን የጽሁፍ ጥያቄ የሚስማማቸውን በመምረጥ ሁሉም ሊመልሱት መቻላቸውን እንረዳለን፡፡ ሆኖም በአጠቃላይ ስንመለከተው ተማሪዎቹ የሰጡትን ምላሽ በአብዛኛው መስፈርቶቹ የሚስማማቸውን እና ከፈተና አሰራር አኳያ የሚጠቀሙበት መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን በቁጥር 1 እና 8 የቀረበላቸውን ጥያቄ አስመልክቶ የሰጡቱት ምላሽ ቁጥራቸው ወደ ግማሽ የሚጠጉት የማይስማሙት መሆኑን አመልክተዋል፡፡

በመጨረሻም በዚሁ የጽሑፍ ጥያቄ ስር ነፃ አስተያየት የሚሰጡበት 2 ጥያቄዎች ቀርቦላቸዋል የሚከተሉትን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የመጀመሪያው ጥያቄ በፈተና ዝቅተኛ

ውጤት ሲያስመዘግቡ የሚሰማቸውን ስሜት እንዲገልፁ የሚያመለክት ሲሆን ለዚሁ ጥያቄ፡-

- በትምህርት ላይ የጠለቀ ዕውቀት እንደሌለኝ ይሰማኛል ›
- የተማርኩትን በፈተና ወቅት የተጠየቁሁት አለመዛመዱንም እረዳለሁ
- ፈተናው በአግባቡ ያለመዘጋጀቱን አስባለሁ
- በትምህርቱ ላይ ጥላቻ አሳድራለሁ
- ምንም እንዳልሰራሁ እገነዘባለሁ
- የአጠናን መንገዴ ትክክል ያለመሆኑን እገነዘባለሁ
- የመምህሩ አቀራረብ ትክክል ያለመሆኑን ወዘተ መገንዘብ ያስችለኛል

  በማለት አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ጥሩ ውጤት ቢያስመዘግቡ የሚሰማቸውን ስሜት እንዲገልፁ በቀረበላቸው ጥያቄ መሠረት ፡-

- ስለትምህርቱ በቂ ግንዛቤ እንዳለኝ አስባለሁ፣
- ስወደፊትም ለትምህርቱ ያለኝ አመለካከት ይዳብራል፣
- የትምህርቱን አቅራቢ መምህር አደንቀዋለሁ፣
- በቀጣይ ትምህርቶች ላይ የበለጠ እንድሰራ ይገፋፋኛል፣
- ጊዜዬን በአግባቡ እንደተጠቀምኩ እገነዘባለሁ፣

የሚሉትን ምላሻ ሰጥተዋል፡፡

እነዚህን ሁለት ጥያቄዎች በተመለከተ ጠቅላላ ተጠኚዎች ያሰፈሩትን ምላሽ እንዳለ ማቅረብ የማይታሰብ ነው፡፡ በመሆኑም በዋናነት በጥናቱ ላይ የሰፈሩት ምላሾች በአብዛኛው ተማሪዎች በድግግሞሻ የተመለሱትን ብቻ መሆኑን እናስገነዝባለን፡፡

ሰንጠረዥ አምስት፡- ተጠኝዎች ለሶስቱም የትምህርት ዓይነቶች ለቃለመጠይቁ የሰጡት ምላሽ

| ተራ ቁ | የጥያቄ አይነት | የተሰጠው ምላሽ | የትምህርት አይነት | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የአማርኛ ቋንቋ ቅኝት | | | | የሥነጽሁፍ መሠረታውያን | | | | የፎክሎር መግቢያ | | | |
| | | | ወ | ሴ | ድ | | ወ | ሴ | ድ | | ወ | ሴ | ድ | |
| 1 | መምህሩ ትምህርቱን የሚቀርቡት በየትኛውም መንገድ ነው | መምህር ተኮር | 6 | 8 | 14 | 70% | 3 | 6 | 9 | 45% | 9 | 9 | 18 | 90% |
| | | ተማሪ ተኮር | 1 | 1 | 2 | 1% | 3 | 6 | 9 | 45% | | | | |
| | | በሁሉም | 2 | 2 | 4 | 20% | 2 | | 2 | 10% | 1 | 1 | 2 | 10% |
| 2 | መምህሩ ትምህርቱን ተግባራዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ በቂ የመለማመጃ እድል ይፈጥሩልሀል | ይፈጥሩልኛል | 3 | 1 | 4 | 20% | 8 | 8 | 16 | 80% | 3 | 2 | 5 | 25% |
| | | አይፈጥሩልኝም | 9 | 7 | 16 | 80% | 3 | 1 | 4 | 20% | 8 | 7 | 15 | 75% |
| 3 | መምህሩ ትምህርቱን ከክፍል ውጭ ተጨማሪ ግንዛቤ የምታገኝበት /ኚበትን/ አቅጣጫና ቦታ ጠቁመሀል /ሻል/ | ይጠቁማል | 6 | 5 | 11 | 55% | 7 | 8 | 15 | 75% | 2 | 1 | 3 | 15% |
| | | አይጠቁምም | 4 | 5 | 9 | 45% | 4 | 1 | 5 | 25% | 9 | 8 | 17 | 85% |
| 4 | ለትምህርቱ የተሰጠው ሳምንታዊ የማሳተማሪያ ሰዓት /credit Hour/ ከይዘቱ ጋር ሲነፃፀር በቂ ነው፡፡ | በቂ ነው | 5 | 3 | 8 | 4% | 5 | 4 | 9 | 45% | 8 | 8 | 16 | 80% |
| | | በቂ አይደለም | 7 | 5 | 12 | 60% | 6 | 5 | 11 | 55% | 2 | 2 | 4 | 20% |
| 5 | ለትምህርቱ የምትሰጠው የጥናት ጊዜ መጠን ከሌሎች ተጓዳኝ ትምህርት ጋረር ሲነፃፀር ምን ያህል ነው | የበለጠ | 6 | 7 | 13 | 65% | 7 | 7 | 14 | 70% | 3 | 2 | 5 | 25% |
| | | ያነሰ | | 1 | 1 | 5% | 3 | 3 | 6 | 30% | 6 | 5 | 11 | 55% |
| | | እኩል | 2 | 4 | 6 | 3% | 3 | 3 | 6 | 30% | 3 | 1 | 4 | 20% |
| 6 | የትምህርት አቀራረብና አተገባበር ስለምታጠናው ትምህርት በቂ ግንዛቤ አስገኝቶልሀል /ሻል/ | አስገኝቷል | 4 | 5 | 9 | 45% | 6 | 8 | 14 | 70% | 2 | 1 | 3 | 15% |
| | | አላስገኘም | 5 | 6 | 11 | 55% | 4 | 2 | 6 | 30% | 9 | 8 | 17 | 85% |
| 7 | ስለ ተምህርቱ ያለህን /ሽን/ ግንዛቤ ለመረዳት ይቻል ዘንድ ይምትገመገምበት /ሚበት/ የፈተና አዘገጃጀት የአጠያየቅ ዘዴ ይስማማሻል /ሀል/ | ይስማማኛል | 7 | 8 | 15 | 75% | 54 | 3 | 8 | 40% | 4 | 2 | 6 | 30% |
| | | አይስማማኝም | 2 | 3 | 5 | 25% | 7 | 5 | 12 | 60% | 7 | 7 | 14 | 70% |
| 8 | መምህርህ ከፈተና በፊት ስለፈተናው አዘገጃጀትና ሚያጠቃልላቸውን ይዘቶችና አስቀድመው ይጠይቁሀል /ሻል/ | ይጠቀሙኛል | 5 | 8 | 13 | 65% | 2 | 3 | 5 | 25% | 3 | 3 | 6 | 30% |
| | | አይጠቀሙኝም | 4 | 3 | 7 | 35% | 7 | 8 | 12 | 75% | 9 | 5 | 14 | 70% |

በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለጥናቱ አላማ ግብ መምታት አስተዋጽዖ እንዳላቸው በመረዳት ተጠንዎቹም በሚማሩት ትምህርቶች ላይ መሰረት ያደረጉት አስር ጥያቄዎች በቃለ መጠይቅ ቀርበዋል የጥያቄዎቹም አደረጃጀት በትምህርቱም አቀራረብ ፣ በጊዜ ምጣኔ፣ በትምህርቱ አተገባበር ወዘተ በኩል የተወሰኑ መረጃዎች ከመፈለግ የተነሳ ነው። በዚህም የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑ ተማሪዎች መካከል ጾታን በማመጣጠን በኩል በቁጥር (ሃያ) 20 የሚሆኑትን በተራ እጣ ናሙና (simple random sampling) በመምረጥ ነው። ተጠኝዎቹ ከሶስቱ የትምህርት ዓይነቶች ማለትም የአምርኛ ቋንቋ ቅኝት በስነ ጽሁፍ መሰረታዊያን የፍክሎሮር መግቢያ አንጻር ለእያንዳንዱ ጥያቄ ምላሻቸውን ሰጥተዋል በጥያቄዎቹ ቅደም ተከተል መሰረት ለእያንዳንዱ ትምህርት የሰጡት ምላሽም እንደ አመቺነቱ በዘንጠረዥ ቀርቧል። ከቀረቡትም 10 ጥያቄዎች ምላሾቹን በሰንጠረዥና በቁጥር አስልቶ ለማቅረብ አመቺ የሆኑት ስምንቱ በመሆናቸው የቀሪዎቹ ሁለት ጥያቄዎች ደግሞ የተሰጡት ምላሾች በጽሁፍ ይብራራል።

ከሰንጠረዥ መረዳት እንዳተቻለው በቅደም ተከተሉ መሰረት ተማሪዎቹ ቅድሚያ ምላሻቸውን የሰጡት አማርኛ ቋንቋ ‹ን› በተመለከተ ነው። በመሆኑም ከጠቅላላ ተጠኝዎች አስራ አራት ያህሉ ወይም 70% የሚሆኑት የትምህርቱ የሚሰጣቸው መምህር ተኮር በሆነ ዘዴ መሆኑን ያመለክታል። እንዲሁም ተማሪዎቹ ትምህርቱን ተግባራዊ ማድረግ ይችሉ ዘንድ መምህሩ በቂ የመለማመጃ እድል በመፍጠር በኩል ያለው ተነሳሽነትን ለመረዳት ያስችልዘንድ ለቀረበላቸው ጥያቄ በቁጥር 16 ወይም 80% ያህሉ በቂ መለማመጃ እድል እንደሚያገኙ ተገልጻል። 20% ደግሞ እድሉ እነደሚያገኙ መረጃ ያመለክታል ይህም የሚያመለክተን አብዛኛው ተማሪ ተጠቃሚ እንደሆነ ነው። ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ከሚማሩበት ትምህርት በተጨማሪ ግንዛቤ የሚገኝበትን መንገድ ከማመልከቱም አንጻር 55% አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል።

ለትምህርቱ ማለትም ለአማርኛ ቋንቋ ቅኝት ተብሎ የተሰጠው ሳምንታዊ የማስተማሪያ ሰዓት (Credit hours) ከትምርቱ ይዘት ስፋትና ጥልቀት አንጻር ሲታይ አስራ ሁለቱ ወይም 60% በቂ ያለመሆኑን ሲመለከቱ ስምንቱ ደግሞ በቂ መሆኑን ከተሰጡት ምላሾች መረዳት ይቻላል። በዚህም ትምህርት የሚሰጡት የጥናት ጊዜ መጠን ከሌሎቹ ተጓዳኝ ትምህርቶች ጋር ሲነጻፀር የበለጠ ወይም ሰፋ ያለ ጊዜ እንደሚሰጡት አብዛኛዎቹ ማለትም 65% ያህሉ ምላሽ ሰጥተዋል። ከዚህም በተጨማሪ ትምህርቱ አቀራረብና አተገባበርን በተመለከተ ደግሞ ከተጠያቂዎቹ 9 ያህሉ ወይም 45% በቂ ግንዛቤ እንዳላስገኙላቸው። ሲያመለክቱ 11(55%) ግን በቂ ግንዛቤ

እንዳስገኙላቸው:: ገልፀዋል ተጠኝዋቹ ስለ ትምህቱ ያላቸውንክህሎት መረዳት ይቻል ዛንደ የሚገመገምበት የፈተና አዘገጃጀትና የአጠያየቅ ዘዴ እንደሚስማማችው አብዛኞቹ ማለትም 75%ቱ ይስማሙበታል:: 25% የሚሆኑት ደግሞ እነደማይመቻቸው ይገልፃሉ :: በመጨረሻም መምህሩ ስለፈተናው አዘገጃጀትና የሚያጠቃልላቸውን ይዘቶች ፈተናው ከመሰጠቱ በፊት እነደሚጠቁሟቸው አብዛኞቹ ይስማሙበታል::

በሁለቱኛ ደረጃ ምላሽ የሰጡበት ትምህርት ደግሞ የስነ ፁሁፍ መሠረታውያንን በተመለከተ ነበር መምህሩ ይህንኑ ትምህርት የሚያቀርቡበት መንገድ በሁለቱም መንገድ ማለትም መምህር ተኮርና ተማሪ ተኮር ነው በማለት አብዛኞቹ ምላሽ ሰጥተዋል:: 45% በሆነ እኩል መጠን ትምህርቱ መቅረቡን ሲያመለክቱ 10% ያህሉ ደግሞ በሁሉም መንገድ መሰጠቱን ይገልጻሉ ከሁሉም አስተያየትና ምላሽ መረዳት የሚቻለው መምህሩ የሁሉንም የትምህርት አቀራረብ እንደሚጠቀሙ ነው:: ቀጥሎም ተማሪዎቹ ትምህርቱን ተግባራዊ ያደረጉት ዘንድ በቂ መለማመጃ እድል ተፈጥሮላቸው እንደሆነና እንዳልሆነ ተጠይቀው ሲመልሱ የተወሰኑት ማለትም አራቱ (20%) ብቻ በቂ እድል እንዳማይፈጠርላቸው ሲያመለክቱ አብዛኞቹ ግን ማለትም አስራ ስድስቱ (80 %) በቂ እድል እንደሚፈጥርላቸው አመልክተዋል:: እንዲሁም በክፍል ከሚቀርብላቸው ትምህርት ውጪ በተጨማሪነት በቂ ግንዛቤ የሚያገኙበትን መንገድ ቦታና መረጃ መጻህፍትን እንደሚጠቁሟቸው በቁጥር አስራ አምስት ያህሉ(75%) ሲስማሙበት አምስቱ (25%) ያህሉ ደግሞ አይስማሙበትም ለትምህርቱ የተሰጠው ሳምንታዊ የማስተማሪያ ሰዓት (credit hour) ከይዘቱ ጋር ሲነፃፀር በቂ ያለመሆኑን አብዛኞቹ ተጠኝዎች ማለትም 55% ያህሉ ሲያመለክቱ ቀሪዎቹ 45% በቂ መሆኑን ምላሽ ሰጥተዋል:: ለዚህ ትምህርት ብለው የሚጠቀሙት የጥናት ጊዜ ከሌሎቹ ትምህርቶች የበለጠ መሆኑንም 70%ቱ ገልፀዋል:: በቁጥር አንድ ላይ የመለሱት የትምህርቱ አቀርረብ መንገድ ወይም ዘዴ ከውጤታቸው ጋር ሲዛመድ ውጤታማ እንዳደረጋቸው ብዙሀኑ ይስማሙበታል::

በመጨረሻም የሚገመገሙበት የፈተና አዘገጃጀትና የአጠያየቅ ዘዴውን በተመለከተ ከተጠያቂዎቹ አብላጫ ያላቸው ማለትም 60% የሚሆኑት የማይስማማቸው መሆኑን ሲያመለክቱ ስለፈተናው አዘገጃጀትና የሚያጠቃልላቸው ይዘቶች ግን መምህሩ አስቀድመው እንደሚጠቁሙአቸው 75% የሚሆኑት ይስማሙበታል::

በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ምላሽ የተሰጡት የፎክሎር መግቢያን በተመለከተ ነባር መምህሩ ትምህርቱን የሚያቀርበበት መንገድ መምህር-ተኮር መሆኑን 90% ያህል ተስማምተውበታል፡፡ እንዲሁም ትምህቱን ተግባራዊ ማድረግ ይችሉ ዘንድ ተጠይቀው አብዛኞቹ ማለትም 75% ያህሉ በቂ የመለማመጃ እድል እንደማይፈጥሩላቸው ሲያመለክቱ 25% የሚሆኑት ደግሞ ይፈጥሩልናል በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡ ቀጥሎም ተጠኝዎቹ በክፍል ከሚቀርብላቸው ትምህርት በተጨማሪ ግንዛቤ የሚያገኙበትን አቀጣጫ ወይም ሥፍራ ወይም መረጃ መፃህፍትን (Reference) እንደማይጠቀሙአቸው የመለሱት 85% ያህሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ለትምህርቱ የተሰጠው ሳምንታዊ የማስተማሪያ ሰዓት (Credit hour) በቂ መሆኑን ብዙሀኑ (80%) ይስማሙበታል፡፡ ለትምህርቱ የሚያውሉት የጥናት ጊዜ መጠንም የበለጠመሆኑን 25% ያነሰ መሆኑን ደግሞ 55% እንዲሁም እኩል መሆኑን 20% ያህሉ ምላሽ ሰጥተዋ፡፡ በመሆኑም ከጠቅላላ ተጠኝዎች ብልጫ ያላቸው ያነሰ ጊዜ እንዳሚጠቀሚ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በቁጥር አንድ ላይ ገየትምህቱን አቀራረብ በተመለከተ የሰጡት ምላሽ (መምህር ተኮር) መሆኑ ከውጤታቸው ጋር ሲዛመድ ውጤታማ እንዳላደረጋቸው ያመለክታሉ፡፡

በመጨረሻም ተማሪዎቹ ስለትምህርቱ ያላቸውን ግንዛቤ ወይም የመረዳት ብቃት ማወቅ ይቻል ዘንድ የሚገመገሙበት የፈተና አዘገጃጀት እና የአጠያየቅ ዘዴው የማይስማማቸው መሆኑን 70% የሚሆኑት ሲገልፁ 30% ደግሞ እነደሚስማማቸው ጠቁመዋል፡፡ መምህሩ ስለፈተናው አዘገጃጀትና የሚያጠቃልላቸውን ይዘቶች አስቀድመው እንደማይጠቁሙአቸው አብዛኞቹ ማለትም 70% የሚሆኑት ይስማሙበታል፡፡

በአጠቃላይ ተጠኝዎቹ ከሰጡት ምላሽ ለመገንዘብ እንደሚቻለው ተማሪዎቹ የሚማሩት ትምህርት በውል ለመገንዘብ የሚያስችለውን የመማር ብልሀት ወይም የአጠናን ዘዴ በበቂ ሁኔት እንደማያገኙና ይህም በውጤታቸው ላይ ተፅህኖ እንደማያገኙና ይንም በውጤታቸው ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር መረዳት ይቻላል፡፡

ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው ለቃሉ መጠይቅ ከቀረቡላቸው ጥያቄዎች ውስጥ ሁለቱ በሥነጠረዥ ላይ በአሀዝም ሆነ በመቶኛ አስልቶ ለማስቀመጥ አመቺ አለመሆናቸው ተጠኝዋቹ ለሁለቱም ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ በአመዛኙ ተመሳሳይነት ስላላቸው በሚከተለው መንገድ ቀርበዋል፡፡ በቅድሚያ ጥናትህን የምታዘወትርው/ሪው/ ጊዜና ቦታ መቼና የት ነው ይህንን ጊዜና ቦታ ለመወን መረጥሽው/ሽው/ ለሚላ ጥያቂ

- በቲ እንቅልፍ ካገኘሁ በኋላ ሌሊት ተነስቼ አጠናለሁ፣
- ማታ ማታ እራቴን ከበላሁ በኋላ ቤተመፃህፍት ውስጥ አጠናለሁ፣
- ጠዋት ጠዋት ለአንድ ሰዓት ያህል አጠናለሁ፣
- እስከ እንቅልፍ ሰዓተር በመማሪያ ክፍል ውስጥ አጠናለሁ
- ፀጥታ ባለበትን አመቺ በሆነ ሥፍራሁ አጠናለሁ፣ ወዘተ

በማለት ሲመልሱ ለሁለተኛው ጥያቄ ማለትም በፈትና ውጤታማ ለመሆን ይቻል ዘንድ ትኩረት ሚሹ ዋና ዋናዎቹ ጉዳቶች ምንድን ናቸው፡፡ ለሚለው ጥያቄ ደግሞ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

- ትምህርቱ ከተጀምረ ዕለት ጀምር ከሥር ከሥሩ ማጥናት፣
- ከጓደኞቹ ጋር በቡድን በመወያየት ማጥናት፣
- የመምህሩን የአጠያየቅ ዘዴ አስቀድሞ ለመረዳት መሞከርና ለፈተናው መዘጋጀት፣
- ጥያቄዎችን እራሰችን እያዘጋጀን መለማመድ፣
- ተማርነውን ትምህት ፍሬ ሀሳብ አሳጥረን በማዘጋጀት ማጥናት
- የማጣቀሻ መፃህፍትን በመጠቀም ትምህርቱን ማዳበር፣ወዘተ ሚሉት ናቸው፡፡

## 4.2 የውጤት ማብራሪያ

በጥናቱ ውጤት ትንተና ለማብራራት እንደተሞከረው ተጠኝዎች በሚማሩአቸው ትምህርቶች ማለትም የአማርኛ ቋንቋ ቅኝት የሥነ ጹሁፍ መሰረታዊያን እና የፍክሎሮ መግቢን ያጠናን ዘዴውን በተመለከተ በቀረቡላቸው መጠይቆቻ መሰረት ግልጽና በመረጃ የተደገፈ ምላሽ ሰጥተዋል በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ትምህርቶች ፈተና ከመድረሱ በፊትና ፈተና ሲደርስ ሚያረኑትን በቁጥርና በመቶኛ ነማስላት ለማቅረብ ተሞክሯል በተገነው መረጃ መሰረትም ጥናቱ ተተኳረ ከሆኑት ተማሪዎች መካከል ፈተናከመድረሱ በፊት የሚያጠኑት በቁጥር 77 ሲሆኑ፣ የሚየጠረኑት ዳግሞ 36 ሆነዋል፡ ይህም በተማሪዎችየጥናት ጊዜ ምርጫ መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያናል፡፡ ፈተና ከመድረሱ በፊት የሚያጠኑት ተማረዎች በቁጥራቸው በርከት ያሉ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ተማሪዎቹ በአብዛኛዉ ፈተና ከመድረሱ በፊት የሚያጠኑት ሳይጨነቁና ለጥናታቸዉም ሰፋ ያለ ጊዜን ለማግኘት ሲሉ ነዉ፡፡ ይህንን የጥናት ጊዜ ሲመርጡ

የቻሉበትን ምክንያት ተጠይቀዉ "ፈተናዉን በራሳቸዉ በመተማመንና ራሳቸዉን ለመመለስ ያስችለናል" ብለዋል። ይህም የጥናት ጊዜ ምርጫቸዉ ዉጤታማ እንዳደርጋቸዉ አክለው ገልጸዋል። ከዚህ ምላሻቸዉ እንጻር መረዳት ያለብን የጥናት ጊዜ ምርጫቸዉ ዉጤታማ ከመሆናቸዉ ጋር የተያያዘ ሆኖ መገኘቱንም ጭምር ነዉ። ይህም webb(1987)፣smith (1990)፣koln chan [1994]ተማሪዎች በትምህርት ዓለምእስካሉ ድረስ ጥናታቸውን ሳያስድለሱ ከወዲሁ ወይም አስቀድመው ማከናወን አለባቸው በማለት ከሰነዘሩት ሐሳብ ጋር ተዛምዶ አለው።

ተማሪዎች ጥናታቸውን የሚያከናውኑት በምን ዓይነት ዘዴ እንደሆነ ለማወቅ ከቀረበላቸው ጥያቄ አንዱ ፕሮግራምን በተመለከተ ነበር። ይሁንና አብዛኞቹ ተማሪዎች የጥናት ፕሮግራም በማውጣት እንደሚያጠኑና ዕቅዳቸውንም ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ በማድረጋቸው ተጠቃሚ መሆናቸውን አመልክተዋል። ይህም ከአቡሽ (1996፡ 16-20 ) እና ሊበን (1997፡ 64-67) ተማሪዎች ጊዜያቸውን በአግባቡ በመከፋፈል ሳይጨነቁና የተጣበበ የጊዜ ሁኔታ ሳይገጥማቸው እያዳንዱን ሰዓት በተግባር ላይ ማዋል ይኖርባቸዋል በማለት ከሰጡት አስተያየት ጋር ይስማማል።

ምንም እንኳን በቁጥር ከፍ ያሉት ተማሪዎች ፈተና ከመድረሱ በፊት አጥንተው ውጤታማ መሆናቸውን መረጃው ቢያመለክትም የተወሰኑት ማለትም 21% ያህሉ ደግሞ ፈተና ሲደርስ አትንተው ውጤታማ እደሆኑ መዘገንጋት የለብንም። Morgan (1968፡ 13-141) የማስታወስ ችሎት ይበልጥ የሚፋጠነው ለፈተና ጥቂት ቀናት ሲቀረው በሚደረግ ጥናት ነው ካለው ሀሳብ ግርተመሳሳይነት አለው። ተማሪዎች አስቀድመው ያጠኑትን በክለሳ መልክ የመመልከት ልምድ እንዳላቸው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ አብዛኛው ተማሪዎች ይህንን የአጠናን ዘዴ እንደሚጠቀሙበት ተገንዝበናል። እንዲሁም በክፍል ውስጥ ከሚማሩት በተጨማሪ የማጣቀሻ መፃህፍትን ተጠቃሚ የሆኑት አብዛኞቹ ወይም 65% ናቸው። ይህም ስለሚማሩት ትምህርት የላቀና የበለጠ እውቀት እንዲኖራቸው እገዛ እንደሚያዳርግላቸው አክለው ገልጸዋል። ይሁን እንጂ በትምህርቱ ድጋፍ ሰጭ የሆኑት መፃህፍት የተወሰኑ እንደሆኑም ጠቁመዋል።

ጥናታቸውነ የሚያከናውኑት ጊዜ ወይም ሰዓት መቼ እንደሆነ በምርጫ የቀረበላቸው ጥያቄ ጧት ጧት የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ሰዓት ቁጥራቸው 21 ያህል የሚሆኑት

እንደማይጠቀሙበት ያመለክታል። ይህም ፀሀፍት ተማሪዎች ሏት ሏት ማጥናታቸው አዕምሮአቸው በቂ እረፍት የሚያገኙበትና አጋጣሚ በተመለከተ የሰነዘሩትን ሀሳብ ይቃረናል።

በቡድን ወይም ከጓደኛ ጋር ሆኖ የማጥናት ልምድ ያላቸው ተማሪዎች ለማወቅ በቀረበላቸው ጥያቄ መሠረትም ከግማሽ በላይ የሆኑት ተማሪዎች ከጓደኞቻቸው ጋር በቡድን እንደሚያጠኑ መረጃ ቢያመለክትም ቁጥራቸው ወደግማሽ የሚጠጉት ደግሞ የቡድን ጥናትን እንደልምድ የማይጠቀሙበት መሆኑን ለመረዳት ይቻላል። በመሆኑም ከቡድን ጥናት ጠቀሚታ አንፃር ሲታይ ተማሪዎች እድሉን በበቂ ሁኔታ አግኝተዋል ለማለት ይቸግራል።

ተጠኝዎች ጥናታቸው የሚያከናውኑበት ቦታ ምን እንደሚመስል ለመረዳት ያስችል ዘንድ በሰጡት ምላሽ አብዛኞቹ ተማሪዎች ለጥናታቸው የተወሰ ቦታ እንዳላቸውና ይህም ቦታ ፀጥታ ያለበትና ምቹ ስፍራ መሆን እንዳለበት ሲያመለክቱ ብዙ ግዜ ግን በቤተመፃህፍትና በባዶ የመማሪያ ክፍሎች ጥናታቸውን እንደሚያከናውኑ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። እንዲሁም የሚሰጡት የጊዜ ሽፋን እንደየትምህርቱ ሲለያይ እንደሚችል በርካታ ተማሪዎች ምላሽ ሰጥተዋል።

ተማሪዎች ውጤታማ ለመሆን ከጥናታቸው ተጠቃሚ የሚሆንበትን ዘዴ እንዲገልጹ በቀረበላቸው ክፍት ጥያቄ መሰረት የሰጡት ምላሽ ፕሮግራም በማውጣትና ዘወትር ማጥናት ተገቢ እንደሆነና የህም የሚማሩት ትምህርት እየበዛ ወይም መጠኑ እየጨመረ በመጣ ቁጥር ከመርበትበትና ከመጨነቅ እንደሚያድናቸው በምክንያት እያስደገፉ ሀሳብ ሰጥተዋል። ጊዜውን በተመለከተ ደግሞ ሌሊት ሌሊትና ሏት ሏት እንደሚያጠኑና የተወሰኑትግን ባገኙትና በተመቻቸው ጊዜ ሁሉ ማጥናት እንዳለባቸው አብራርተዋል። ይህም ትክክለኛውን የጥናት ጊዜ ወይም ሰዓት በመምረጥ በኩል ወጥነት የሌለው ምርጫ እንዳላቸው ያመላክታል።እንዲሁም ጥቂት የሆኑት ተማሪዎች የማጣቀሻ መፅሀፍትን መጠቀም እንደሚችሉና በጥናት ጊዜ ያልገባቸውን ማስታወሻ በመያዝ መምህራቸውን ወይም ጓደኞቻቸውን በመጠየቅ ውጤታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ አመልክተዋል።

ውጤታማ ያደርገኛል ብለው የመረጡትን የጥናት ጊዜ ምርጫና ዘዴ እንዴት እንደመረጡት ለማወቅ ለቀረበላቸው ጥያቄ አብዛኞቹ ተማሪዎች በራሳቸው

እንደመረጡና ጥቂቶች ግን ሌሎች አካሎች ምክር እንደለገሷቸው ገልፀዋል፡፡ በመምህሮቻቸው መመከራቸውን የሚያመለክት ግን መረጃ ወይም ምላሽ አልተገኘም፡፡

ምንም እንኳን ተማሪዎች ከጥናታቸው ተጠቃሚ የሚሆኑበትን የጥናት ዘዴ እንዲጠቀሙ በምርጫ የቀረበላቸውን ምላሽ ቀደም ሲል ለማመልከት ቢቻልም ከአማራጮቹ የተለየ ምላሽ እንዳላቸው እንዲጠቁሙ በቀረበላቸው ክፍት ጥያቄ መሰረት የተለዩ ሆነው የተገኙት፡-

- ትምህርቱ (course) በተሰጠው ክፍለ ጊዜ ( credit hour) መጠን አጠናለሁ
- በቂ እረፍትና እንቅልፍ ካገኘሁ በኃላ በሚኖረኝ ጊዜ አጠናለሁ
- የምማረውን ትምህርት አጠቃላይ ይዘት አስቀድሜ ለማወት በመሞከር በተቻለ መጠን ቀድሜ ለማንበብ እሞክራለሁ
- የመምህሩን የአጠያየቅ ስልትና አስቀድሞ የተሰጡ ፈተናዎችን ለማወቅ በመሞከር ለፈተና መዘጋጀትና
- ከሰኞ እስከ ዓርብ የተማርኩትን ቅዳሜና እሁድ አጠናለሁ በማለት የሰጡት ምላሾች ናቸው፡፡

ቀደም ሲል በውጤት ትንተናው አማካይነት ተጠኝዎች ስለፈተና አሰራርና አዘገጃጀት ያላቸውን ልምዲ ለመረዳት እንዲያስቸውለን በክፍል ሁለት ተዘጋጅቶ ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የተሰጡት ምላሽ በሰንጠረዥ ለማመልከት ተሞክሯል፡፡ በዚሁ መሠረት የተገኘውን ውጤት በአጭሩ ለማብራራት ያህል እነደደሚከተለው ቀረበዋል፡፡

ከጠቅላላ ተጠኝዎች 41.6% የሆኑት ደግሞ በፈተና ወቅት መጨነቃቸውን ተረድተናል፡፡ ይህም እንደ አጠቃላይ ሲታይ ከፊሎቹ ሲጨነቁ ከፊሎቹ ደግሞ ያለመጨነቃቸውን በመሆኑ ተጽዕኖ እንዳለ መጀረጃው ያመለክታል፡፡ መጨነቅ ደግሞ ያለመረጋጋትንና መርበትበትን የሚፈጥርባቸው ዘመሆኑ በውጤታቸው ላይ አሉታዎ ጎን እንዳለው ያመለክታል፡፡ በመቀጠል በፈተና ዋዜማ ራስቸውን ሊያረጋጉ የሚችሉት የተማሪዎች ባዛት 63.3% የሚሆኑ እረጋጋለሁ ሲሉ መልሰዋል፡፡ ይህንን አሀዝ ከላይ ከተገኘው አሀዝ ጋር ሲነፃፀር መጠነኛ ተፋልሶ ይታይበታል፡፡ ምክንያቱም መረጋጋት ካለመጨነቅ የሚመነጭ ነው፡፡

ተማሪዎች ፈተናቸውን መስራት ከመጀመራቸው በፊት አስቀድመው መመሪያዎችንና የፈተናዎችና ብዛት የሚመለከቱት አብዛኞቹ ማለትም 9.8% ሆነው

ሲገኙ፣85% ያህሉ ደግሞ ለፈተናው የተሰጣቸውን ሰዓት በአግባቡ ተቆጣጥረው እንደሚጠቀሙበት መረጃው ያመለክታል፡፡ ይህም ትክክለኛ የአሠራር መንገድ ነው በማለት የተሰጠውን የምሁራን አስተያየት ያገናዘበ ነው፡፡ በፈተና ወቅት ሲመልሱት የማይችሉት ጥያቄ ሲፈጥማቸው የሚረበሹት በቁጥር 55 ያህሉ ናቸው ይህም አህዝ ወደ ግማሽ የሚጠጋ በመሆኑ ቀጥሎ በሚሰሩት ፈተና ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳርፍ ከወዲሁ መገመት ይቻላል፡፡ ከዚህ ችግር መላቀቅ የሚቻለው ደግሞ መመለስ የሚችሉትን ብቻ አስቀድመው እንዲሰሩ ምሁራን ይመክራሉ፡፡ ከዚህም ተጠቃሚ የሆኑት በቁጥር 100 የሚሆኑ ተማሪዎች መሆናቸውን መረጃው ያመለክታል፡፡

ፈተና እየተቃረበ በመጣ ቁጥር ጊዜያቸውን በአግባቡ የሚጠቀሙት ተማሪዎች በቁጥር 100 ያህሉ በመሆናቸውና ከዚህም ተጠቃሚ መሆናቸውን ስንረዳ Morgan (1968) የማስታወስ ችሎታ ይበልጥ የሚፋጠነው ለፈተና ጥቂት ቀናት ወይም ጊዜያት ሲቀረው ነው፡፡ ተማሪዎች መፈተኛ ሰዓታቸው እየተቃረበ በመጣ ቁጥር እያንዳንዱን ሴኮንድ በአግባቡ ስለሚጠቀሙበት ውጤታማ ይሆናሉ፡፡ በማለት ከሰነዘረው አስተያየት ጋር ይስማማል፡፡

በመጨረሻም ከዚሁ የፅሁፍ ጥያቄ ስር ቀረቡላቸው ነፃና አስተያየትን የሚሹ ሶስት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለነዚሁ ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ በአጭሩ ለማብራራት፡- በፈታናዎች ጥሩ ውጤት ሳያመጡ ቢቀሩ ወይም ወጡታማ ባይሆኑ ለሚሰማቸው ስሜት የሰጡት ምላሽ ለዚህ ምክንያቱ ስራሳቸው መሆናቸውንና ጥቂቶቹ ደግሞ በፈተናው አቀራረብና በመምህሩ ያመካኙ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ለምሳሌ «ምንም እንዳልሰራሁ እገነዘባለሁ የአጠናን መንገዴ ወይም ዘዴዬ ትክክል ያለመሆኑን እረዳለሁ፡፡» ያሉት እራሳቸውን ምክንያት ያደረጉ ሲሆን «የተማርኩትና በፈተና ወቅት የተጠየኩት ተዛማጂነት የላቸውምና ፈተናው በአግባቡ አልተዘጋጀም? በትምህርቱ ላይ ጥላቻ አሳድራለሁና መምህሩ በአግባቡ ትምህርቱን አላቀረበውም ወዘተ» የሚሉት ደግሞ የፈተናውን አዘገጃጀትና አቀራረብ እንዲሁም መምህሩን ጭምር የሚኮንኑ ናቸው፡፡ ያም ሆነ ይህ ተማሪዎች ውጤታማ ሲሆኑ ያልቻሉበት ምክንያት በውል ታውቆ መፍትሄ ቢበጅላቸው የተሻለ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ ጥያቄ በመቀጠል ጥሩ ውቤት ቢያስመዘግቡ የሚሰማቸውን ስሜት እንዲያብራሩ ተጠይቀው ከላይየሰጡትን ምላሽ በተቃራኒው አመላክተዋል፡፡ ለምሳሌ ስለትምህቱ በቂ ዕውቀት እንዳለኝ እገነዘባለሁ፣የበለጠ እንዲሰራ ይገፋፋኛል፣ ጊዜዬን በአግባቡ እንደተጠቀምኩ እቆጥራለሁ ወዘተ በማለት መልሰዋል በተጨማሪም ከዚህ ምላሻቸው፡፡

መገንዘብ የሚቻለው ትምህርት ሰጪው ወይም አቅራቢውም ሆነ ተቀባዩ ጉዳዩን በግልጽ በመነጋገር ችግሩን መቅረፍ እንደሚገባቸው ነው፡፡ ምክንያቱም የመማር ማስረማሩ ተግባር ውጤታማ ሆኖ መገኘት የመማርን ዓላማ ከግብ የሚያደርስ ተክክለኛ አቅጣጫ ስለሆነ ነው፡፡

ተማሪዎች በሚማሩት ትምህርቶች ማለትም የአማርኛ ቋንቋ ቅኝት፣የስነጹሁፍ መሰረታውያንና የፎክሎር መግቢያኮርሶች አንፃር የመማር ማስተማር ዘዴውን መሠረት ላደረጉ 10 የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች የተሰጡት ምላሾች እንደሚከተለው ያብራራሉ፡፡
አባዛኛው ተጠኝዎች የሰጡት ምላሽ በየትምህርቶቹ ላይ ተመሳሰሎ አለው፡፡ ለምሳሌ አማራኛ ቋንቋ ቅኝትን የፎክሎር መግቢያ ትምህርቶች በአብዛኛው አቀራረባቸው መምህር ተኮር በሆነ ዘዴ መሆኑን ሲገልፁ የስነጹሁፍ መሠረታውያንን ግን አልፎ አልፎ በጋራ ወይም በቡድን እንዲሰሩ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ እንደአጠቃላይ ሲታይ የትምህርቱ አቀራረብ መምህር ተኮር በሆነ መንገድ እንደሚሰጥ ነው፡፡ ይህ አካሄድ ደግሞ «የቋንቋ ዓላማ መርህ» ጋር በመጠኑ ይጋጫል፡፡
መምህሩን በክፍል ውስጥ ከሚያቀርቡት ትምህርት በተጨማሪ ተማሪዎች ስለትምህርቱ የጠለቀ ዕውቀት እንዲኖራቸው እገዛ የሚያደርግላቸውን የማጣቀሻ መፃህፍት እንዲጠቀሙ የመምከር ወይም የመጠቆም ልምዳቸው በመጠኑ እንዳለና መጻህፍቱም በቁጥር በጣም አናሳ እንደሆኑና እነሱም መምህሩ ከሚያስታምረው የተለየ ፍንጭ የሚሰጡ ያለመሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

በትምህርቶቹ በተሰጡት ክፍለጊዜያት ዙሪያ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች ለአማርኛ ቋንቋ ቅኝትና ለስነጽሁፍ መሰረታውያን ክፍለጊዜው እንደሚያንስ ሲያመለክቱ ለፎክሎር መግቢያ ግን በቂ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

የተማሪዎችን የመረዳት ችሎታ ወይም የማለፍና የመውደቅ ዕድላቸውን ለመወሰን ተዘጋጁተው በሚቀርቡላቸው ፈተናዎች ላይ አስተያየትእንዲሰጡ በተጠየቁት መሰረት በአብሰዛኛው የሚቀርቡት ፈተናዎች ድግግሞሽ የበዛባቸውና የአጠያየቅ ዘዴያቸው ግልፅ ያልሆነ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ ይንንንም ለመረዳት እንደ አጋጣሚ ቀደም ሲል የተሰጠ ፈተና ጥያቄዎች ቢገኙ ጥሩ ውጤት ለማምጣት የሚያስችላቸው መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ አልፎ አልፎ ደግሞ ፈተናዎቹ በክፍል ውስጥ ከቀረቡትና ከተዳሰሱት ይዘቶች የወጡ በመሆናቸው ለመመለስ መቸገራቸውን ጠቁመዋል፡፡ በፈተና አቅራረብ ዙሪያ የተሻለ ነው ብለው የጠቆሙት ቢኖር ጥያቄዎቹ ግልጽና ቀጥተኛ ቢሆኑ፣ የአተያየቅ ባልሀታቸው ደግሞ ዓይነት (variety) ያላቸው መሆን ይገባቸዋል፡፡ ፈተናው በትክክል ተማሪው የሚገመገምበት እንጂ የሚቸገርበት ሆኖ መቅረብ እንደሌለበት አብዛኞቹ ተማሪዎች አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

የፈተናው ዕለት ሲቃረብ መምህራን ፈተናው የሚያጠቃልላቸውንና የሚሸፍናቸውን ይዘቶች አስቀድመው የማይገልፁ መሆናቸውን ያመለክታሉ፡፡ ይህም በተማሪዎች ውጤት ላይ ተጽዕኖ እንዳለው ያመለክታሉ፡፡

በመጨረሻም ተማሪዎች ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ትኩረት ሊሰጥባቸው ይገባል ባለው የመለሱት ምላሽ

- በክፍል ውስት ስንማር በማስታወሻ መልክ የያዝነውን በአጭር በአጭር አንደገና በማቀናበርና ፍሬ ሀሳቡን ለቅሞበማውጣት ለማጥናት መሞከር
- ከያዘእነው ማስታወሻም ሆነ ካነበብነው አጠቃላይ የትምህርቱ ይዘቶች ራሳችንን በማዘጋጀትና እርስ በእርስ በመጠያየቅ ማጥናት የሚሉት ናቸው፡፡

## ምዕራፍ አምስት

# የጥናቱ ውጤት መዳምደሚያና የመፍትሄ ሀሳቦች

በዚህ ክፍል የጥናት ውጤት መደምደሚያና መፍትሄ ሀሳቦች በቅደም ተከተል ይቀርባል ::

### 5.1. የጥናቱ ውጤት

የጥናቱ አላም የጥናት ጊዜ ምርጫ ከውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ መመርመር ነው። በዚህም መሰረት ጥናቱ እንዲመልሶቸው በመጀመሪጀያ የተነሱት ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ፦

- ተማሪዎ የየራሳቸው የጥናት ጊዜ ምርጫ እዳላቸው እና እንደሌላቸው በመመርመር እንደመማር ብቃታቸው ትክክለኛው የጥናት ጊዜ ምርጫ እንዲከተሉ ለማድረግ
- የተማሪዎች የጥናር ጊዜ ምራጫ መለያለየት በውጤታቸው ላይ የሚያሳድርን ተፅእኖ በመረዳተ ውጤታቸው ን ከአጠናን ዘዴየቸው ጋር በማስማማት እነደዲጠቀሙበት ለማድረግ፣
- የተማሪዎችን የጥናት ጊዜ ምርጫ ከውጤታቸው ጋር ያላውን ተዛምዶ በመመርመርና ሳይንሳዊና ትክክለኛውን የአጠናን ዘዴ በመረዳት እንዲጠቀሙበት ለማድረግ፣
- የአጠናን ዘዴ ለተማሪዎች ውጤት ከፍተኛ ወይማ ዝቅተኝ መሆኑን ምክንያተ ሆኖ ከተግ ተገቢውን መንገድ እንዲከሉ ለማድግ
- ተማሪዎች ከጥናታቸው ተጠቃሚ የሚሆኑብትን መሰረታው ያጠናን ዘዴዎች እንዲከተሉ ለማድረግ እና
- የተጠቀሱት ቋንቋ ትምህርቶች ምሁራን ለአጠቃይ ትምርቶች የሰጡት የአጠናን ዘዴዎችን እንዲከተሉ ማድረግ

ከላይ ያሉትን ጥያቄዎች ለመመለስናየጥናቱን አላማ ለመተግበርይቻል ዘንድ የመጀመሪያ ተጠኝዎችንና የመረጃ ማሳሰቢያ መሳሪያዎት ተመርጠዋል ተጠኝዎችም በ1999 ዓ.ም በባህር ዳርዩኒቨርሲቲ ትምህርት ፋክልቲ የአማርኛ ቋንቋ ቅኝትን

የስነፅሁፍ መሰረታዊያንና የፎክሎር መግቢያን የሚማሩ ተማሪዎችን ነው። በዘመኑ ያሉትን ጠቅላላ ተማሪዎች ለፅሁፍ መጠይቁ ተሳታፊ በማድረግና ከመካከላቸውም በቁጥር 20 የሚሆኑ ተማሪዎች ቃለ መጠይ ቀርቦላቸው በየትምህርት አይነቶቹ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ተደርጓል አመራረጡመ ዓታን በመጣጠነ መልኩ በብድግ ብድግ የአመራረጥ ዘዴ ነው።

የፅሁፉ መጠይቆችና የቃለመጠይቆቹ ጥያቄዎች የተደራጁት የተጠኝዎችን ጥናት ጊዜ ምርጫና ውጤት ተዛምዶ ሊመላክቱ በሚችሊ መንገድና ከተዛማጅ ፅሁፎች አንፃርም ነው። በመሆኑም መረጃዎቹ ከተሰበሰቡ በኃላ አንደመልሶቻቸው ተመሳስሎ በጥንቃቂ ቆጠራ ተካሂዶ ውጤቱ በቁጥርና በመቶኛ ተሰልቶ በሰንጠረዥ ተመልክቷል።

በአጠቃላይ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑት መረዳዎች ከተሰበሰቡና በቂ ትንተናና ማብራሪያ ከተደረገባቸው በኃላ የሚከተሉትውጤቶች ተገኝተዋል።

- ከጠቅላላው ተጠኝዎች አብዛንቹ ማለትም 75% ያህሉ የጥናት ጊዜ ምርጫ አላቸው።
- የብዙዎቹ ማለትም 64% ያህሉ የጥናት ጊዜ ምርጫቸው ፈተና ከመድረሱ በፊት ነው።
- የጥናት ጊዜ ምራጨቸው ፈተና ከመድረሱ በፊትም ሆነ ፈተና ሲደርስ ሆነው የተገኙት አብዛኛው ተጠኝዎች የመረጡት የጥናት ጊዜ ምርጫ ወ/ጤታም አድርጓአቸዋል። ሆኖም በጥናት ጊዜ በምርጫና በውጤት መካከል ያለው ተዛምዶ ብዙም አስተማማኝ አልሆነም።
- የተማሪዎች የአጠናን ዘዴ ወጥነት የሌለውና ሳይንሳዊ የአጠናን ዘዴን የተከተለ ሆኖ አልተገኘው።
- ፈተና ከመድረሱ በፊት ማጥናትና ፈተና ሲደርስ ማጥናት ከቋንቋ ትምህርቶች ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ አያስተማምንም።

5.2. መደምደሚያ

የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ ከዚህ ቀጥሎ ባሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሶል፡፡

- በውጤቱ ላይ እንደተመለከተው ምንም እንኳን የአብዛኞቹ ተማሪዎች የጥናት ጊዜ ምርጫ ፈተና ከመድረሱ በፊት ቢሆንም ይህ ምርጫቸው ከትምህርት ውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ አስተማማኝ ቢመስልም ፈተና ሲደርስ የሚያጠኑት ደግሞ የጥናት ጊዜ ምርጫቸው ከውጤታቸ ጋር ተዛምዶ የለውም፡፡ ይህም የሚያመለክተን የጥናት ጊዜ ምርጫ ብቻውን በትምህርት ውጤት ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ መሆን በምክንያት ሊጠቀስ አለመቻሉን ነው፡፡
- በተማሪዎች መካከል የጥናት ጊዜ ምርጫ ልዩነት እንዳለውና ተጠኝዎችም የተለያዩ የመማር ብልሀቶች እንዳላቸው ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ ይሆነኛል ብለው የመረጡት የጥናት ጊዜ ምርጫ ባመዛኙ ከልምድ ያገኙት መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህም አዝማሚያቸው ተማሪዎች መቼና እንዴት ማጥናት እንዳለባቸው በቂ ግንዛቤ ያላቸው አይመስልም፡፡
- ተጠኝዎች የጥናት ጊዜ ምርጫቸውን ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ አስቀድሞ የማወቅ ዝንባሌ የላቸውም፡፡ ከዚህ ባሻገር የየራሳቸውን የመማር ብቃት ወይም ችሎታ አስቀድመው አልተገነዘቡም፡፡ መምህራንም የተማሪዎቻቸውን የመማር ደረጃ ለይተው አስፈላጊውን እገዛ ሲሰጡ አልታዩም፡፡ የተማሪዎችም የእውቀት ደረጃ ለመወሰን ወይም ለመረዳት በየጊዜው የሚቀርቡት የፈተን ጥያቄዎች አዘገጃጀትና አቀራረብ ብዙም ሳቢነት ያለው አይደለም፡፡ ይህም መምህራን ከምያስተምሩት የትምህርት አይነት ባህሪ አንጻር ተማሪዎች በቂ እውቀት ሊያገኙ የሚችሉበትን መንገድ እንደማያመላክቷቸው ከወዲሁ መገመት ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን ትምህርት በራሳቸው ጥረትና በሚመቻቸው መንገድ ማጥናታቸው ተረድተናል፡፡ ከዚሁ የመማር ብልሀታቸው ጋር ተዛማጅ የሆነ በቂ የልምምድ እድል ሲፈጥራላቸው አልተስተዋለም፡፡

ምክንያቱም እንደአጠቃላይ ስንመለከተው የቋንቋ ክህሎት ሊዳብር የሚችለው በአብዛኛው በመሞከርና በመለማመድ ስለሆነ ነው።

- የተማሪዎችን የግንዛቤ ደረጃ ለመወሰን ይቻል ዘንድ የፈተና አሰራርና ዝግጅትን አስመልክቶ አስፈላጊውን እገዛ ሲደረግላቸው አልተስተዋለም። ይህም የእያንዳንዱ ተማሪ ለፈተና የሚሰጠው ግምት የተለያየ በመሆኑና ውጤታቸው ስለትምህርቱ ያላቸውን ብቃት በእርግጠኝነት ያመላክታል ብሎ መገመት ስለማይቻልና ከፈተና አሰራር ብልሀት ማጣት የተነሳም ሊሆን ይችላል ብሎ ማሰቡም ተገቢነት ያለው ስለሆነ ነው።
- እያንዳንዱ የትምህርት አይነት የራሱ የሆነ የእድገት ደረጃ አለው ምክንያቱም በዘርፉ ያሉ ሙሁራን የማያቋርጥ የምርምር ጥናት ስራ ስለሚያካሂዱ ዓለም በሥልጣኔ እየበለፀገች በሄደች ቁጥር በየትምህርቱ ላይ የሚታያ ለውጥ የማይገታ ስለሆነ ነው። በዚሁ መሰረት መምህራን በየዘመኑ የሚያስተምሩት ትምህርት ያላቻው አቀራረብ ይህንኑ የተከተለና ከተማሪዎች በሚያገኙት ውጤት አንፃር በመነሳትም አስፋላጊውን የአቀራረብ ብልሀት ሲከተሉ አልተስተዋለም። ለዚህም በየ ዓመቱ ተመሳይነት ያላቸው ጥያቄዎቻ ወይም ፈተናዎች መቅረባቸው ብዙ አመት የቆዩ የመረጃ መፀሀፍት እንዲጠቀሙ ማድረጋቸው የትምህርት አቀራረባቸው መምህር ተኮር ሆኖ መገኘቱ ወዘተ. ተጠኝዎች በቃለ ምልልሱ ላይ ከሰጡት አስተያየት በመነሳት ነው።
- በመጨረሻም ተማሪዎች ከጥናታቸው ተጠቃሚ ይሆኑ ዘንድ የየትምህርቱ ባህሪ የተከተለ በቀላሉ ሊካኑ የሚችሉበት መንገድ ወይም ዘዴ ምሁራን በበቂ ሁኔት አለማዘጋጀታቸውን ለመረዳት ይቻላል። ምክንያቱም ከጥናቱ ውጤት እንደተረዳነው ለጠቅላላ የትምህርት አይነቶች እንጂ በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት የአጠናን ዘዴና የመማር ብልሀት ሲባል የተዘጋጀ ጥናትና ምርምር ስራ በአስተማማኝነት ሊገኝ ባለመቻሉ ነው።

## 5.3. የመፍትሔ ሀሳቦች

ከጥናቱ ውጤትና መደምደሚያ አንፃር በመነሳት አጥኝው ቀጥሎ ያሉትን የመፍትሔ ሐሳቦች ይጠቁመናል፡፡

- ተማሪዎች ይሆነኛል ብለው ከሚከተሉት የአጠናንና የመማር ብልሀታቸው በመነሳት መምህራን ይህንኑ ልዩነታቸውን ማለትም ነገሮችን የመረዳት አቅማቸውን አስቀድመው በመረዳት አስፈላጊውን እገዛ ቢያደርጉላቸው
- ተማሪዎች በየጊዜው ከሚያገኙት ውጤት (ከፍተኛም ሆነ ዝቅተኛ) በመነሳት የአጠናን ዘሬያቸውን በመገምገም በውጤቱ ተጠቃሚ የሆኑት እንዲያዳብሩትና ተጠቃሚ ያልሆኑት ግን ለውጤታቸው ዝቅተኛ መሆን የመማር ወይም የአጠናን ዘዴአቸውን በመለዋወጥ አስፈላጊውን ጥረትቢያደርጉ ይመረጣል፡፡ ይህም ዘወትር ያለአግባብ በመምህሩ ከማማረርና ከማሳበብ ነፃ ያደርጋቸዋል፡፡ መማረው ደግሞ ደጋግሞ ከመምከርና ሳይታክቱ በመስራትየሚዳብር መሆኑን እንድንገነዘብ ያደርገናል፡፡
- ለትምህርት ውጠየት ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛመሆን የጥናት ጊዜ ምርጫ ብቻውን ዋስትና ሊሆን እንደማይችል አስቀድሞ በመገንዘብ ሌሎች ተላውጦዎችም ማለትም የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ ዳራዊ ዓውቀት፣ ዕድሜ፣ ያታ ነገሮችን ለመቀበል ችሎታ፣ ዝንባሌ ወይም ተነሳሽነት፣ ወዘተ አንዳሉ በመገንዘብ ውጤታማ የሚሆኑበትን አቅም መፍጠር ይገባቸዋል፡፡
- መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ዘወትር ግልጽ ውይይት በማድረግ ችግሮችን እየፈቱ የመሄድ ልምድ ቢዳብርና ይህ ተግባቦትም በመጨረሻ በውጠየታቸው ላይ ለሚታየው ለውጥ ተጠያቂው ማን እንደሆነ ስለሚያመላክት ነው፡፡

## ዋቢ መጻሕፍት

Ball. Samuel. (1985). The world book encyclopedia V. 18 world book in

Curley, Rober G. and others (1987) " Relation ships between study activities and achievement as a function of grade level and course characteristics" Contemporary Educational Psychology V. 12 < 4 P324-343

Finkel Lawernces and Crawtz Ruth (1967) How to study 2nd. ed New York Ocean Publication inc.

Keevis, John P. (1992) Educational Research Methodology and Measurement. As international hand book. America paragon press.

Morgan. Tcliford (1969) Introduction to Psychology 5th ed. New York Mc Graw hill book company. Norman. Endiskass and Norman Max well H (1981) How to Reads Study for Success in College. 3rd Ed. New York . Hotl. Rinoh

Slavin, Robert E. (1997) Educational Psychology: Theory and Practices 5th ed. American allya and bocon.

Svaz Kevin (1982) Memory Training for Students and Executives 3rd ed New Delihi Vikas Publications House Pvt. Ltd

Tyler, A Burr and Others (1987) " Analitic frame work assessing Distinctive Course features with in an across grade leveles " Contemporary Educatioanl Psychology V. 12 N. 4 P. 280-302:

ሲበን በሽር /1997/ ለሁለተኛ ደረጃና ከኮሌጅ ተማሪዎች የጥናት ስራተኛ ዝግጅት ምክሮች አዲስ አበባ ማተሚያ ድርጅት ::

ማረወ ዓለሙ /1988/ የመማር ምርጫና የትምህርት ወጤት ተዛምዶ The Ethiopia Journal of Education X, X111

ኑሪያ ዮሱፍና ተስፋዬ ተሰማ:: /1993/ ሳየንሳዊ የጥናትና የፈተና አወሳሰድ ዘዴ አዲስ አበባ

አቡሽ አያሌው:: /1998/ ስኬታማ የጥናት ተግባራት አዲስ አበባ ብራና ማተሚያ ድርጅት ከድረ-ገጽ የተገኙ ምንጮች

WWW. Harvard west lake com. Lstudents /study skills

WWW. Iss stthomas edu/ ancadamic advising/

WWW. South Western edu/ academic/

WWW. Uga educ/ dae/ groups/

## አባሪ አንድ

ማሳሰቢያ:- የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በጥናት ጊዜና ዘዴ እንዲሁም በውጤት ተዛምዶ ለሚጠናው ጥናት የሚረዱ መረጃያችን ማግኘት ነው:: በመሆኑም የሚሰጡት ትክክለኛና የተማኑ መረጃዎች ለጥናቱ መሳካት ወሳኝ በመሆናቸው መጠይቁን በትግስትና በታማኝነት ትኩረት ተስጥታችሁ እንድትመልሱልኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ:: ስለትብብራችሁ በቅድሚያ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

መመሪያ:- የመጠይቁ አሞላል ለእያንዳንዱ ጥያቄ አራት አመራጮች ተሰጥተዋ:: ስለዚህ በአማራጮቻችሁ አንፃር የምትስማሙበትን የ "X" ምልክት በማድረግና በመጨረሻም የግል አስተያየታችሁን የሚጠይቁ ጥያቄዎች ስላሉ መልሳችሁን በአጭሩ በመግለፅ ይሆናል::

ዕድሜ. . . . . . . . . . . ፆታ. . . . . . . . . . . የአፍ መፍቻ ቋንቋ. . . . . . ሁለተኛ ቋንቋ. . . . .

ሌላ/ሌሎች ቋንቋዎች . . . . . . . የመጣህበት /ሽበት/ ክልል . . . . . . ዞን.. . . . . . .

ሀ. ጥናትን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን እቸገራለሁ | አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የጥናት ጊዜ ምርጫ አለኝ | | | | |
| 2 | ጥናቱን የምጀምረው ፈተና ከመድርሱ በፊት ነው | | | | |
| 3 | ጥናቴን የምጀምረው ፈተና ሲደርስ /ሲቃረብ/ ነው | | | | |
| 4 | የመረጥኩት የጥናት ጊዜ ውጤታማ አድርጎኛል | | | | |
| 5 | ጥናቴን የማጠናወ የግል ኘሮግራም በማውጣት ነው | | | | |
| 6 | የጥናት ኘሮግራሜን በአግባቡ እጠቀምበታለሁ | | | | |
| 7 | አስቀድሜ ያጠናሁትን በክለሳ መልክ አየዋለሁ | | | | |
| 8 | በክፍል ውስጥ ከምማረው ውጭ የማጣቀሻ መጽሐፍትንና አስቀድሞ የተሰጡ ፈተናዎችን እመለከታለሁ | | | | |
| 9 | ጥናቴን የማከናውነው ዘወትር ጧትጧት ነው | | | | |
| 10 | ከክፍል ትምህርት በኋላ ሁል ጊዜ የተማርኩትን እከልሳለሁ | | | | |
| 11 | በግል ከማጠናወ ውጭ በጓደኞቼ ጋር በቡድን አጠናለሁ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 12 | ጥናቴን የማከናውንበት የተወሰነ ቦታ አለኝ | | | | |
| 13 | ለሁሉን የትምህርት ዓይነቶች የምሰጠው የጥናተው ጊዜ እኩል ነው | | | | |
| 14 | ትምህርቱን ተግባራዊ ሊያደርጉ የሚችሉ በዚ. የማጣቀሻ መጽሐፍት አለኝ | | | | |

15. ውጤታማ ለመሆን እንዴትና መቼ ማጥናት ይኖርብሃል /ሻል/ በአጭሩ ይብራራ?

16. የመረጥከው /ሽው/ የጥናት ጊዜ እንድትወስን/ኚ ያደረገህ/ህ ሌላ አካል አለ?

17. ተማሪዎች ወጤታማ ለመሆን እንዴት ትምህርቱን ማጥናት አለባቻው ትላለህ /ትያለሽ/ ?

አባሪ ሁለት

## ለ. ፈተናን በተመለከተ የቀረቡ ጥየቄዎች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን እቸገራለሁ | አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጆተና ሲቃረብ እጨነቃለሁ | | | | |
| 2 | ከመፈተኔ በፊት ልጠየቅ የምችለው ጥያቄ | | | | |
| 3 | ፈተናውን የምሰራው ተረጋግቼና በራሴ በመተማመን ነው | | | | |
| 4 | ምፈተና ወቅት በራሳ መተማመንና መረጋጋት ውጤታማ ያደርጋል | | | | |
| 5 | ምፈተና ዋዜማ ራስን ከማስጨነቅ ይልቅ ዘና ማለትን እመርጣለሁ | | | | |
| 6 | ጆተናውን ከመጀመሬ በፊት መመሪያዎቹንና የጥያቄዎችን ብዛት እመለከታለሁ | | | | |
| 7 | ለፈተናው በተሰጠው ሰዓት በአግባቡ መጠቀም እችላለሁ | | | | |
| 8 | ጆተናውን ስሰራ ልመልሰው የማልችለው ጥያቄ ሲገጥመኝ እደነግጣለሁ ወይም እጨነቃለሁ | | | | |
| 9 | የሚቀሉኝን ጥያቄዎች አስቀድሜ እሰራለሁ | | | | |
| 10 | ፈተና እየተቃረበ በመጣ ቁጥር ጊዜዬን በአግባቡ እጠቀምበታለሁ | | | | |

11. በፈተናህ/ሽ/ ዝቅተኛ ወጤት ብታስመዘግብ/ቢ/ ምን ይሰማሀል /ሻል/ ለውጤቱ ዝቅተኛ መሆን የምትሰጠው /ጪው/ አስተያየት /መክንያት/ ምንድን ነው፡፡ አስተያየትህን /ሽን/ በአጭሩ ግለጽ /ግለጪ/

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

12. በፈተናህ/ሽ/ ጥሩ ውጤት ብታስመዘግብ/ ቢምን ይሰማሃል /ሻል/?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

### አባሪ ሶስት

ሐ. የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት ተማሪዎች /ጾታን ባመጣጠነ መንገድ መካከል በቁጥር ሀያ ለሚሆኑ ተማሪዎች የቀረቡ ቃለ-መጠይቆች/

1. መምህሩ በክፍል ውስጥ ትምህርቱን የሚያቀርቡበት መንገድ /ዘዴ/ የትኛው ነው ለምሳሌ መምህር ተኮር ተማሪተኮር በሁለቱም እንዲሁም ሌላ መንገድ ካለ ይግለጹ
2. መምህርህ /ሽ/ ትምህርቱን ተግባራዊ ማድረግ እንድትች /ችይ/ በቂ የመለማመጃ እድል ይፈጥሩልሀለ/ሻ/ በግል ወይስ በቡድን ?
3. መምህር /ሽ/ ትምህርቱን ከክፍል ውጪ ተጨማሪ ግንዛቤ ልታገኝ ወይም ልታገኚ የምትችልበትን አቅጣጫና ቦታ ይጠቁሙሀል /ሻል/?
4. ለትምህርቱ የተሰጠው ሰማንታዊ የማስተማሪያ ሰአት ( Credit hour) ከይዘቱ ጋር ሲነፃፀር በቂ ነው ትላለህ /ሽ/ ?
5. ለትምህርቱ የምታውለው /ይው/ ጥናት የጊዜ መጠን ከሌሎች ተጓዳኝ ትምህርቶች ጋር ሲነፃፀር የበለጠ ያነሰ ወይም እኩል ነው::?
6. የትምህርቱ አቀራረብና አተገባበር እንዲሁም የይዘት ሽፋኑ በቂ ግንዛቤ ያስገኝልሀል/ሽ/ ይመስልሀለ /ሻል/ ?
7. ስለትምህርቱ ያለህ /ሽ/ ግንዛቤ ለመረዳት ይቻል ዘንድ በምትገመግምበት /ሚበት/ የፈተና አዘገጃጀትና ያአጠያየቅ ዘዴ ይስማማሀል /ሻል/ ለምን ?
8. ጥናትህን የምታዘወትረው /ሪው/ ጊዜና ቦታ መቼና የት ነው ይህንንስ ጊዜና ቦታ ለምን መረጥከው /ሽው/ ?
9. መምህሩ ከፈተናው በፊት ስለፈተናው አዘገጃጀትና የሚያጠቃልላቸውን ይዘቶች አስቀድመው ይጠቁሙሀል /ሻል/
10. በፈተና ውጤታማ ለመሆን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ዋና ዋናዎች ምንድን ናቸው ትላለህ /ትያለሽ/ ?